ንዋያተ ቤተ ክርስቲያን

Mekrez Ze Tewahdo

1/ መላእክትን ‹‹ያድናሉ›› ማለት ስሕተት ነውን?

(በቀሲስ ኅብረት የሺጥላ)

ለመሆኑ መላእክት ማዳን ይችላሉ ማለት ስሕተት ነውን? ዛሬ ዛሬ ብዙዎች መናፍቃን መላእክትን ‹‹ያድናሉ›› ማለት እንደ ስሕተትና እንደ ክህደት ቆጥረውት ሲናገሩ መስማት የተለመደ ሆኗል። ለምን ሲባሉም መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹መዳን በሌላ በማንም የለም›› በማለት ያለ አገባቡ ጥቅስ ይጠቅሳሉ።

በእርግጥ መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹መዳን በሌላ በማንም የለም›› ይላል። ይሁን እንጂ ይህ መላእክት አያድኑም ማለት አይደለም። ይህ ምን ማለት እንደሆነ ዕድሜ ይስጠን እንጂ ራሱን በቻለ ርእስ በሌላ ጊዜ በሰፊው እንመለስበታለን። ለዛሬ የመላእክትን ማዳን ከመጽሐፍ ቅዱስ መረጃ እየጠቀስን እንመልከት።

ቅዱስ ዳዊት በግልጥ ‹‹የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል፤ ያድናቸውማል›› ይላል። (መዝ 33.7) ጥቅሱ ‹‹ያድናቸውማል›› ማለቱን ልብ በሉ። መላእክት የማያድኑ ቢሆኑ ኖሮ ቅዱስ ዳዊት በዚህ መልኩ ግልጥ አድርጎ ‹‹ያድናቸውማል›› ይል ነበር? መጽሐፍ ቅዱስ ከመሰከረው እውነት የሚበልጥ ዕውቀት አለንን? እርሱ ‹‹ያድናሉ›› እያለ እኛ ‹‹አያድኑም›› ብንል ምን ማለታችን ነው? ይህ ጥቅስ ውሸት ነውን? ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እንታዘዘዋለን?

እናምነዋለን? ወይስ ልናርመው እንወዳለን?

በሌላም የመጽሐፍ ቅዱስ ገጸ ንባብ ውስጥ ‹‹ከክፉ ነገር ሁሉ ያዳነኝ መልአክ እርሱ እነዚህን ልጆች ይባርክ›› በማለት ያዕቆብ የልጅ ልጆቹን እንደባረከ እናነባለን። (ዘፍ 48.16) በዚህ ጥቅስ ውስጥ መልአክ ‹‹ከክፉ ነገር ሁሉ›› እንደሚያድን በግልጽ ተጽፏል። መላእክት ‹‹ያድናሉ›› ላለማለት እነዚህን ግልጽ ቃላት መላእክት ይጠብቃሉ፤ ይራዳሉ፤ ያግዛሉ በማለት ማድበስበስ ይኖርብን ይሆን? ይህ ሁሉ ዝርዝሩ ሥራቸው ቢሆንም እንደሚድኑም ተጽፏልና ማመን ያስፈልጋል።

በዚህ መልኩ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ የተናገረውን ቃል እናቶችና አባቶች በስእለታቸው ‹‹ቅዱስ ሚካኤል አድነኝ፤ ቅዱስ ገብርኤል ድረስልኝ›› እያሉ በመድገማቸው የዋሃን ስለሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ስለማያውቁ ነው መባል አለባቸው? ቅዱስ ዳዊትና ቅዱስ ያዕቆብ የመላእክትን አዳኝነት በግልጽ ያወጁት መጽሐፍ ቅዱስን ወደ መንፈሳዊ ኮሌጅ ገብተው ስላልተማሩ ይሆን? ወይስ አንድ ሰባኪ የመላእክትን አዳኝነት ስላስተማረ ‹‹ገድል ጠቃሽ›› በሚል መጥላላት አለበት? ዘማርያኑስ በዚህ መልኩ መዘመራቸው ሊያስወቅሳቸው ይገባ ነበር?

መላእክት የእግዚአብሔር ናቸው። የፈጠራቸው እርሱ ነው። የሚፈጽሙትም የእርሱን ፈቃድ ነው። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ የእርሱ መሆናቸውን በሚያሳይ አገላለጥ ‹‹መልአኩ፣ የጌታ መልአክ፣ መላእክቱ›› እያለ ይጠራቸዋል። ‹‹የጌታ መልአክ በሕልም ታየው›› እንዲል። (ማቴ 1.20) መላእክት ሲያድኑ ፈጣሪ ሥራ አልሠራም ማለት አይደለም። መላእክት ያለ እርሱ ፈቃድ ምንም ሊያደርጉ አይችሉም። ሥራ

እንዲሠሩ የሚፈቅድላቸውና የሚያዛቸው እርሱ ነው። ስለዚህ እነርሱ የሠሩትን ይዘን ‹‹ፈጣሪ ይህን አደረገ ማለት እንችላለን›› እርሱ አዟቸውና ፈቅዶላቸው እስከሠሩት ድረስ እርሱ ሠራ ማለት ነውና። የሚቀጥሉት ሦስት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌዎች ይህን ሐሳብ የሚያስረዱ ናቸው።

ለምሳሌ፦ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት ጅራፍ እንዲሠሩ አዘዛቸው። ራሱ ግን ጅራፍ አልሠራም። ቢሆንም ግን መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ እንደሠራ አድርጎ ‹‹የገመድ ጅራፍ አበጅቶ›› ይላል። (ዮሐ 2.15) ዳግመኛም ኢየሱስ ክርስቶስ ማንንም አላጠመቀም ሐዋርያቱ ግን እንዲያጠምቁ አዟቸዋል። ያዘዛቸው እርሱ በመሆኑ ‹‹ያጠምቃል እጅግም ደቀመዛሙርት ያደርጋል›› የሚል ወሬ በፈሪሳውያን ዘንድ ተሰምቷል። ራሱ ግን ማንንም አላጠመቀም ነበር። (ዮሐ 4.1-3) ሌላ ምሳሌ ለመጨመር እነ ሐና እና ቀያፋ ራሳቸው ኢየሱስ ክርስቶስን አልሰቀሉትም። ነገር ግን ተባባሪዎችና ትእዛዝ ሰጪዎች ስለነበሩ ቅዱስ ጴጥሮስ ‹‹እናንተ በሰቀላችሁት›› ሲል ሰቃዮች መሆናቸውን ጠቅሶ ወቅሷቸዋል። (የሐዋ 4.10)

በአንጻሩ ደግሞ ሥልጣኑ የፈጣሪ ነው ማለት መላእክት ‹‹ይህን ሠሩ›› አይባልም ማለት አይደለም። ፈጣሪ በመላእክት ሲሠራ መላእክትን እንደ ቁስ ቆጥሮ ይሠራባቸዋል ማለት አይደለም። መላእክት ሕያዋን ናቸው። የማዘንና የመደሰት ስሜት አላቸው። ያ ባይሆን ኖሮ ንስሐ በሚገባ ኃጢአተኛ ደስ እንደሚላቸው አይጸፍም ነበር። ስለዚህ መላእክት ደስ እንደሚሰኙ ሁሉ ያዝናሉ ማለት ነው። ፈጣሪ ሲያዛቸው በፈቃደኝነት ይታዘዛሉ። ፈጣሪ በእነርሱ ይሠራል ማለት ያለፈቃዳቸው ይልካቸዋል ማለት አይደለም። እንደ ሰው ልጅ ነጻነት አላቸው። ቢሆንም በእርሱ ፈቃድ ደስ

ስለሚላቸው ከፈቃዱ ፈቀቅ አይሉም። ነጻ ፈቃድ ባይኖራቸው ኖሮ ሰይጣን በደለኛ ሆኖ አይገኝም ነበር። የሰይጣን ወደ ገዛ ፈቃዱ ማዘንበል ለመላእክት የተሰጣቸውን ነጻነት ያሳያል። ታዲያ ሥራቸውን ወደው የሚሠሩ ሆነው ሳለ ፈጣሪ ልኮአቸው መላእክት ቢያድኑ ‹‹አላዳኑም›› እንዴት እንላለን? ለማዳን ፈቃደኛ ሆነው እስካዳኑ ድረስ ‹‹አድነዋል፣ ያድናሉ›› ማለት የሚገባ አይደለምን?

መላእክት እግዚአብሔር ስለፈቀደላቸው የሠሩትን ሥራ እነርሱ አልሠሩትም ካልን ሰይጣን የፈጸመውን የጥፋት ተግባር ማን ሠራው ልንል ነው? መቼም እግዚአብሔር ሳይፈቅድለት ሰይጣንም ቢሆን ያሰበውን ማከናወን እንደማይችል የታወቀ ነው። ታዲያ ሰይጣን የሠራውን ፈቃጁ አካል እግዚአብሔር ስለሆነ ፈጣሪ ይህን አደረገ እንጂ ሰይጣን ይህን አልሠራውም እንላለንን? እንዲሁም ፈቃጁና አዛዙ ምንም ፈጣሪ ቢሆን ቅዱሳን መላእክት የሠሩትን እንደሠሩት ማመንና መመስከር ይገባል። ለክፉ ሥራው ሰይጣን ኃላፊነቱን እንደሚወስድ ሁሉ ቅዱሳን መላእክትም ለሥራቸው ኃላፊነቱን ይወስዳሉ። ስለዚህ ፈጣሪ ቅዱስ ገብርኤልን ልኮ ቂርቆስንና ኢየሉጣን ስላዳነ ‹‹ቅዱስ ገበርኤል አዳናቸው!›› የሚገባ ነው።

በቅዱሳን መላእክት ማዳንና ተራዳኢነት ውስጥ የእግዚአብሔር ሥልጣንና አዛዥነት በረቂቅ አለበት። እግዚአብሔር ሰዎችን ለማዳን በምንም መንገድ ቢሠራ በዛ ውስጥ የእርሱ ሥልጣንና ሥራ የማይጠረጠር ነው። መላእክት ያለ ፈጣሪ ትእዛዝና ፈቃድ አንዳች ሊሠሩ አይችሉም። ፈጣሪ ግን ያለ መላእክት አጋዥነት የፈለገውን የሚሠራ ሁሉን ቻይ አምላክ ነው። በሌላ አነጋገር ፈጣሪ ይህን ሠራ ስንል መላእክትን ላይጨምር ይችላል። መላእክት

ይህን አደረጉ ስንል ግን በምንም ተአምር ከፈጣሪ ውጭ ሊሆን አይችልም። ስለዚህ መናፍቃን ‹‹ጌታ፣ እግዚአብሔር ይህን አደረገ›› ብቻ እንድንል የሚፈልጉት ቅዱሳንን ላለማስገባት ነው። እኛ ኦርቶዶክሳዊያን ቅዱሳን መላእክትንና ቅዱሳን ሰዎችን ይህን አደረጉ የምንለው እግዚአብሔርን ከማመን ጋር ስለ ቅዱሳን ክብር ለመመስከር ነው።

እሳት በባሕርይው የሚፋጅ መሆኑ ይታወቃል። እንጨትና ብረት ግን ብቻቸውን ሳሉ ቢነኳቸው አያቃጥሉም። ነገር ግን ከእሳት ጋር ከተዋሐዱ /ከጋሉ/ በኋላ ቢነኳቸው ይፋጃሉ። እሳት የተዋሐደው ብረት የማያቃጥልበት ምንም ሁኔታ የለም። ካላቃጠለ ወይ እሳት አልተዋሐደውም ወይም ደግሞ እሳቱ ራሱ አያቃጥልም ማለት ነው። እንደዚሁም እግዚአብሔር በባሕርይው አዳኝ ነው። መላእክት አያድኑም ካልን ወይ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር አይደለም ማለት ነው ወይም ደግሞ እግዚአብሔር ራሱ አያድንም እንደማለት ይቆጠርብናል። ስለዚህ ‹‹መላእክት ያድናሉ›› ስንል የሚያድን እግዚአብሔር ከእነርሱ እንደማይለይ እየመሰከርን መሆኑን ልብ ማለት ያስፈልጋል።

የእግዚአብሔር ቸርነት

የመልአኩ የቅዱስ ሚካኤል ተራዳኢነት አይለየን!

Likd . Mieraf Laike

ስለዚህ መናፍቃን ‹‹ጌታ፣ እግዚአብሔር ይህን አደረገ›› ብቻ እንድንል የሚፈልጉት ቅዱሳንን ላለማስገባት ነው። እኛ ኦርቶዶክሳዊያን ቅዱሳን መላእክትንና ቅዱሳን ሰዎችን ይህን አደረጉ የምንለው እግዚአብሔርን ከማመን ጋር ስለ ቅዱሳን ክብር ለመመስከር ነው።

Mekrez Ze Tewahdo added 2 new photos .

2/ ነገረ መላእክት (Angelology)

ትርጉም

ጥሬ ቃሉን ስንመለከተው መልአክ የሚለው የግእዝ ቃል ኹለት ትርጉሞች አሉት። አንደኛው አለቃ፣ ሹም ማለት ነው። በዮሐንስ ራዕይ ላይ የምናገኛው ሰባቱ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች መላእክት ተብለው መጠራታቸውም ከዚኽ አንጻር ነው /ራዕ. 2 እና 3/። ኹለተኛውና ከተነሣንበት ርእስ አንጻር ስናየው ደግሞ መልክእተኛ፣ የተሰደደ፣ የተላከ የሚል ትርጉም አለው /ዕብ.1፡14/። ይኸውም የመላእክት ተግባር ምን እንደኾነ የሚያስረዳ ቃል ነው። መላእክት ከእግዚአብሔር ወደ ሰው፥ ከሰውም ወደ እግዚአብሔር የሚላላኩ መናፍስት ናቸውና። መላእክት በሌላ ስማቸው የሰማይ ሠራዊት ተብለው ይጠራሉ።

መላእክት ስንት ወገን ናቸው?

መላእክት ኹለት ወገን ናቸው። ብርሃናውያን መላእክትና የጨለማ አበጋዝ የኾነው የዲያብሎስ ሠራዊት የኾኑት እኩያን መላእክት። ስለዚኽ የእግዚአብሔርን መላእክት ከሌሎቹ መላእክት በአጠራር የምንለያቸው ቅዱስ በሚል ቅጽል ነው።

መላእክት መቼ ተፈጠሩ?

መላእክት የተፈጠሩት በመዠመሪያው ቀን ነው /ኩፋ.2፡7-8/። መዝሙረኛው ክቡር ዳዊትም ይኽን በማስመልከት፡- “በእግዚአብሔር ቃል ሰማያት ተፈጠሩ፤ የሰማይ ሠራዊትም ኹሉ በአፉ እስትንፋስ” ይላል /መዝ.32፡6/።

ምንም እንኳን በመዠመሪያው ቀን የተፈጠሩ ቢኾኑም ግን ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋና ከሰባቱ ሰማያት በኋላ በ9ኛው ሰዓተ ሌሊት ነው የተፈጠሩት። ይኽ ለምን እንደኾነ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ አክሲማሮስ በተባለ መጽሐፉ ላይ፡- “በፊት ፈጥሯቸው ቢኾን እኛም አብረነው ፈጠርን፤ ያዝንለት፤ ተራዳነው ባሉ ነበር። አንድም ርሱ ቢመሠርት እኛ ገነባን፤ ርሱ ቢገነባ እኛ መሠረትን ባሉ ነበር። ይኽም ሳጥናኤል በኋላ እኔ ፈጠርኳችኁ እንዳለው ማለት ነው” በማለት ያብራሯል /አክሲማሮስ ዘእሑድ፣ ገጽ 24/።

አንዳንድ ሊቃውንት መላእክት ከሰው በፊት ስለተፈጠሩ የሰው ታላላቅ ወንድሞች ናቸው ይሏቸዋል።

ተፈጥሮአቸውም ካለ መኖር ወደ መኖር ነው። መላዕክት እንደ እሳት የሚሞቁ፣ እንደ ነፋስ የሚረቁ ስለ ኾነ /ዝኒ ከማኁ/ አንድም እንደ እሳት እንደ ነፋስ ፈጣኖችና የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈጽሙ ኃያላን ስለኾነ ባሕርያቸውን ለመግለጥ ከነፋስና ከእሳት ተፈጠሩ ይባላሉ /መዝ.103፡4፣ መዝሙረ ዳዊት ንባቡ ከነትርጓሜው፣ ገጽ 489 /።

የመላእክት አሰፋፈራቸው እንዴት ነው?

የመላእክት ቁጥራቸው ከእግዚአብሔር በቀር ማንም አያውቀውም /ዳን.7፡

10/። በነገድ በነገድ ስናያቸው ግን ቅዱስ ኤጲፋንዮስ እንደሚነግረን 100 ነገዶች ናቸው። እያንዳንዱ ዐሥር ዐሥር ነገድ የሚይዙ ሲኾኑ ቅደም ተከተላቸውም ይኸው ነው፦ አጋዕዝት /አለቃቸው ሳጥናኤል (ሰማልያል) የእኹኑ ዲያብሎስ ነው/፣ ኪሩቤል /አለቃቸው ኪሩብ ነው፤ አራት ራስ አራት ገጽ አላቸው። ገጻቸውም ገጸ ሰብእ ገጸ አንበሳ ይመስላል። ሰውነታቸው ኹሉ በዓይን የተሸለመ ሲኾን ዓይናቸውም እንደ ነብር ቆዳ ዠንጉርጉር ነው /ሕዝ.1፡6-7፣ 18-19/። አገልግሎታቸው በቀሳውስት አምሳል የሥላሴን ዙፋን መሸከም ነው/፣ ሱራፌል /አለቃቸው ሱራፊ ነው፤ በዲያቆናት አምሳል ለጸሎት የሚተጉና የሚያተጉ የምስጋና መላዕክት ናቸው። ገጻቸው ገጸ ንስር ገጸ እንስሳ ይመስላል። ስድስት ስድስት ክንፍ አላቸው ኢሳ.6፡2-3/፣ ኃይላት /አለቃቸው ቅዱስ ሚካኤል ነው /ኄኖክ.10፡2-10/። የሥላሴ ሰይፍ ጃግሬዎች ናቸው/፣ አርባብ /አለቃቸው ቅዱስ ገብርኤል ነው። በሥላሴ ፊት በአጋፋሪ በአስተናጋጅ አምሳል የሚቆሙ ናቸው ኄኖክ 10፡7-8፣ ሉቃ.1፡19/፣ መናብርት /አለቃቸው ቅዱስ ሩፋኤል ነው። በጋሻ ጃግሬ አምሳል ያገለግላሉ። የመብረቅ ጋሻ የእሳት ጦር ይዘው ዘለዓለም እንደ ነፋስ ሲበሩ ይኖራሉ/፣ ሥልጣናት /አለቃቸው ቅዱስ ሱርያል ነው። የሥላሴ አዋጅ ነጋሪዎችና መላዕክትን በየጊዜው ለጸሎትና ለምስጋና የሚያተጉ ናቸው/፣ መኳንንት /አለቃቸው ሰዳካኤል ይባላል። የሥላሴ ቀስተኞች ናቸው። ተራራ የሚንድ፣ ድንጋይ የሚሰነጥቅ፣ የእሳት ፍላፃ የእሳት ቀስት ይዘው ሰውን ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ ሲጠብቁ ይኖራሉ። በትንሣኤ ዘጕባኤ ጊዜ የሰውን ኹሉ አጥንት ሰብስበው ለትንሣኤ የሚያበቁ እንዚኽ ናቸው ማቴ.24፡31-

42/፣ ሊቃናት /አለቃቸው ሰላታኤል ይባላል። የሥላሴ ፈረስ ባልደራስ ናቸው። የእንስሳት ጠባቂ መላዕክት ናቸው/፣ መላዕክት /አለቃቸው አናንኤል ይባላል። እንደ ብረት የጸና የእሳት ነጐድጓድን ወደ ምድር የሚወነጭፉ፣ ፀሐይን ጨረቃን ከዋክብትን አዝርዕትን አትክልትን ዕፅዋትን ከምድር በላይ ከሰማይ በታች የተፈጠሩትን የሚጠብቁ ናቸው ኩፋሌ 2፡6-8/።

እነዚኽ ቅዱሳን መላእክት የሚኖሩባቸው ቦታዎች ሦስት ሲኾኑ ኢዮር ራማ እና ኤረር ይባላሉ። የመዠመሪያዎቹ 40 ነገድ በኢዮር፣ ቀጣዮቹ 30 በራማ፣ የመጨረሻዎቹ 30 ም በኤረር የሰፈሩ ናቸው።

ዲያብሎስ በትዕቢቱ ከተዋረደ በኋላ ግን የነገደ መላእክቱ ቁጥር ከ 100 ወደ 99 የአለቆች ቁጥርም ከ 10 ወደ 9 ተቀንሷል።

እነዚኽ መላዕክት ለተልዕኮ ፈጣሪ ካላዘዛቸው በቀር ከስፍራቸው አይለቁም። ሲያዛቸው ግን ወደ ላይ እስከ ጽርሐ አርያም ወደ ታች እስከ በርባሮስ ድረስ ከብርሃን ፍጥነት በላይ በኾነ ቅጽበት ይወጣሉ፤ ይወርዳሉ።

ማስፈንጠሪያውን በመጫን ሙሉውን ያንብቡት (http://www.mekrezetewahdo.org/2014/12/angelology.html#more)

ማስፈንጠሪያውን በመጫን ሙሉውን ያንብቡት

ይድረስ ለኢትዮጵያ ህዝብ

3/ ሁለት መላእክት በገነት ይኖሩ ነበር። አንደኛው መልኣክ

ሁልጊዜም እንዳረፈ ነው። ሌላኛው መላእክ ደግሞ ሁሌም ከፈጣሪ ወደ ምድር ያለእረፍት ይመላለስ ነበር። ሁሌም የሚያርፈው መላእክ አንድ ቀን ሁሌም በስራ የሚወጠረውን መላእክ ይጠይቀዋል።

፦ ለምንድን ነው ሁልጊዜ ከዚህ ወደ ምድር ያለ ምንም እረፍት የምትመላለሰው መላእኩም ቀበል አርጎ.....

፦ 'ምክንያቱማ የተለያዩ መልዕክቶችን ተቀብዬ ከሰው ልጅ ወደ ፈጣሪ ስለማመላልስ ነው::'

፦ 'ምን አይነት መልዕክት?'

፦ ''ፈጣሪያችን ሆይ እባክህን እርዳን''....እያለ የሚዘረዝር መልእክት ነው ከምድር ወደ ገነት የማመላልሰው...አንተስ ለምንድን ነው ሁሌም ከዚህ ሳትነቃነቅ የማይህ?'

፦ 'ምክንያቱማ የኔ ስራ ''ፈጣሪያችን ሆይ እናመሰግንሃለን'' የሚል መልእክትን ማመላለስ ነበር።

እስካሁን የመጣ መልእክት የለም።' .....

.....

..... መቀበልን ብቻ ሳይሆን ማመስገንንም ባህላችን እናድርግ።

Miko ZE Ethiopia

4/ ነገረ መላእክት (Angelology)

(መቅረዝ ዘተዋሕዶ፣ ቅዳሜ ታኅሳስ 18 ቀን፣ 2007 ዓ.ም.)፦ በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!!!

ትርጉም

ጥሬ ቃሉን ስንመለከተው መልአክ የሚለው የግእዝ ቃል ኹለት ትርጉሞች አሉት። አንደኛው አለቃ፣ ሹም ማለት ነው። በዮሐንስ ራዕይ ላይ የምናገኛው ሰባቱ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች መላእክት ተብለው መጠራታቸውም ከዚኽ አንጻር ነው /ራዕ. 2 እና 3/። ኹለተኛውና ከተነሣንበት ርእስ አንጻር ስናየው ደግሞ መልክእተኛ፣ የተሰደደ፣ የተላከ የሚል ትርጉም አለው /ዕብ.1፡14/። ይኸውም የመላእክት ተግባር ምን እንደኾነ የሚያስረዳ ቃል ነው። መላእክት ከእግዚአብሔር ወደ ሰው፥ ከሰውም ወደ እግዚአብሔር የሚላላኩ መናፍስት ናቸውና። መላእክት በሌላ ስማቸው የሰማይ ሠራዊት ተብለው ይጠራሉ።

መላእክት ስንት ወገን ናቸው?

መላእክት ኹለት ወገን ናቸው። ብርሃናውያን መላእክትና የጨለማ አበጋዝ የኾነው የዲያብሎስ ሠራዊት የኾኑት እኩያን መላእክት። ስለዚኽ የእግዚአብሔርን መላእክት ከሌሎቹ መላእክት በአጠራር የምንለያቸው ቅዱስ በሚል ቅጽል ነው።

መላእክት መቼ ተፈጠሩ?

መላእክት የተፈጠሩት በመዠመሪያው ቀን ነው /ኩፋ.2፡7-8/።

መዝሙረኛው ክቡር ዳዊትም ይኽን በማስመልከት፦ “በእግዚአብሔር ቃል ሰማያት ተፈጠሩ፤ የሰማይ ሠራዊትም ኹሉ በአፉ እስትንፋስ” ይላል /መዝ.32፡6/።

ምንም እንኳን በመዠመሪያው ቀን የተፈጠሩ ቢኾኑም ግን ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋና ከሰባቱ ሰማያት በኋላ በ9ኛው ሰዓተ ሌሊት ነው የተፈጠሩት። ይኽ ለምን እንደኾነ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ አክሲማሮስ በተባለ መጽሐፉ ላይ፦ “በፊት ፈጥሯቸው ቢኾን እኛም አብረነው ፈጠርን፤ ያዝንለት፤ ተራዳነው ባሉ ነበር። አንድም ርሱ ቢመሠርት እኛ ገነባን፤ ርሱ ቢገነባ እኛ መሠረትን ባሉ ነበር። ይኽም ሳጥናኤል በኋላ እኔ ፈጠርኳችኁ እንዳለው ማለት ነው” በማለት ያብራሯል /አክሲማሮስ ዘእሑድ፣ ገጽ 24/።

አንዳንድ ሊቃውንት መላእክት ከሰው በፊት ስለተፈጠሩ የሰው ታላላቅ ወንድሞች ናቸው ይሏቸዋል።

ተፈጥሮአቸውም ካለ መኖር ወደ መኖር ነው። መላዕክት እንደ እሳት የሚሞቁ፣ እንደ ነፋስ የሚረቁ ስለ ኾነ /ዝኒ ከማኁ/ አንድም እንደ እሳት እንደ ነፋስ ፈጣኖችና የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈጽሙ ኃያላን ስለኾነ ባሕርያቸውን ለመግለጥ ከነፋስና ከእሳት ተፈጠሩ ይባላሉ /መዝ.103፡4፣ መዝሙረ ዳዊት ንባቡ ከነትርጓሜው፣ ገጽ 489 /።

የመላእክት አሰፋፈራቸው እንዴት ነው?

የመላእክት ቁጥራቸው ከእግዚአብሔር በቀር ማንም አያውቀውም /ዳን.7፡10/። በነገድ በነገድ ስናያቸው ግን ቅዱስ ኤጲፋንዮስ እንደሚነግረን 100 ነገዶች ናቸው። እያንዳንዱ ዐሥር ዐሥር ነገድ የሚይዙ ሲኾኑ ቅደም

ተከተላቸውም ይኸው ነው፦ አጋዕዝት /አለቃቸው ሳጥናኤል (ሰማልያል) የአኹኑ ዲያብሎስ ነው/፣ ኪሩቤል /አለቃቸው ኪሩብ ነው፤ አራት ራስ አራት ገጽ አላቸው። ገጻቸውም ገጸ ሰብእ ገጸ አንበሳ ይመስላል። ሰውነታቸው ኹሉ በዓይን የተሸለመ ሲኾን ዓይናቸውም እንደ ነብር ቆዳ ዝንጕርጕር ነው /ሕዝ.1፡6-7፣ 18-19/። አገልግሎታቸው በቀሳውስት አምሳል የሥላሴን ዙፋን መሸከም ነው/፣ ሱራፌል /አለቃቸው ሱራፊ ነው፤ በዲያቆናት አምሳል ለጸሎት የሚተጉና የሚያተጉ የምስጋና መላዕክት ናቸው። ገጻቸው ገጸ ንስር ገጸ እንስሳ ይመስላል። ስድስት ስድስት ክንፍ አላቸው ኢሳ.6፡2-3/፣ ኃይላት /አለቃቸው ቅዱስ ሚካኤል ነው /ኄኖክ.10፡2-10/። የሥላሴ ሰይፍ ጃግሬዎች ናቸው/፣ አርባብ /አለቃቸው ቅዱስ ገብርኤል ነው። በሥላሴ ፊት በአጋፋሪ በአስተናጋጅ አምሳል የሚቆሙ ናቸው ኄኖክ 10፡7-8፣ ሉቃ.1፡19/፣ መናብርት /አለቃቸው ቅዱስ ሩፋኤል ነው። በጋሻ ጃግሬ አምሳል ያገለግላሉ። የመብረቅ ጋሻ የእሳት ጦር ይዘው ዘለዓለም እንደ ነፋስ ሲበሩ ይኖራሉ/፣ ሥልጣናት /አለቃቸው ቅዱስ ሱርያል ነው። የሥላሴ አዋጅ ነጋሪዎችና መላዕክትን በየጊዜው ለጸሎትና ለምስጋና የሚያተጉ ናቸው/፣ መኳንንት /አለቃቸው ሰዳካኤል ይባላል። የሥላሴ ቀስተኞች ናቸው። ተራራ የሚንድ፣ ድንጋይ የሚሰነጥቅ፣ የእሳት ፍላፃ የእሳት ቀስት ይዘው ሰውን ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ ሲጠብቁ ይኖራሉ። በትንሣኤ ዘጕባኤ ጊዜ የሰውን ኹሉ አጥንት ሰብስበው ለትንሣኤ የሚያበቁ እንዚኽ ናቸው ማቴ.24፡31-42/፣ ሊቃናት /አለቃቸው ሰላታኤል ይባላል። የሥላሴ ፈረስ ባልደራስ ናቸው። የእንስሳት ጠባቂ መላዕክት ናቸው/፣ መላዕክት /አለቃቸው

አናንኤል ይባላል። እንደ ብረት የጸና የእሳት ነጐድጓድን ወደ ምድር የሚወነጭፉ፣ ፀሐይን ጨረቃን ከዋክብትን አዝርዕትን አትክልትን ዕፅዋትን ከምድር በላይ ከሰማይ በታች የተፈጠሩትን የሚጠብቁ ናቸው ኩፋሌ 2፡6-8/።

እነዚኽ ቅዱሳን መላእክት የሚኖሩባቸው ቦታዎች ሦስት ሲኾኑ ኢዮር ራማ እና ኤረር ይባላሉ። የመዠመሪያዎቹ 40 ነገድ በኢዮር፣ ቀጣዮቹ 30 በራማ፣ የመጨረሻዎቹ 30 ም በኤረር የሰፈሩ ናቸው።

ዲያብሎስ በትዕቢቱ ከተዋረደ በኋላ ግን የነገደ መላእክቱ ቁጥር ከ 100 ወደ 99 የአለቆች ቁጥርም ከ 10 ወደ 9 ተቀንሷል።

እነዚኽ መላዕክት ለተልዕኮ ፈጣሪ ካላዘዛቸው በቀር ከስፍራቸው አይለቁም። ሲያዛቸው ግን ወደ ላይ እስከ ጽርሐ አርያም ወደ ታች እስከ በርባሮስ ድረስ ከብርሃን ፍጥነት በላይ በኾነ ቅጽበት ይወጣሉ፤ ይወርዳሉ።

የመላእክት ባሕርይ እንዴት ነው?

የመላእክት ባሕርይ ከሰው ጋር የሚያመሳስለውም የሚያለያየውም ነጥብ አለው። ከሰው በምን ይለያሉ ቢሉ መላእክት፡-

· ረቂቃን ናቸው። ከነፋስ ነፍስ ትረቃለች፤ ከነፍስ መላእክት ይረቃሉ፤ ከመላእክት ደግሞ ሥላሴ ይረቃሉ።

· እንደ ሰው አይራቡም፤ አይጠሙም። ልብስ፣ መጠለያ አይፈልጉም። “እኔም ተገለጥኩላችኁ፤ ነገር ግን እይታን አያችኁ እንጂ ከእናንተ ጋር አልበላኹም፤ አልጠጣኹምም” /ጦቢት 12፡19/።

· የመላዕክት ምግባቸው የእግዚአብሔር ምስጋና መጠጣቸውም የመለኮት ፍቅር ነው።

· መላዕክት ፆታ የላቸውም /ማቴ.22፡30-31/። በመኾኑም አይጋቡም፤ አይዋለዱም።

· ስለ ነገ አይጨነቁም።

· መላዕክት ከዘንጋዔ የራቁ፣ ባለ አዕምሮ የኾኑ፣ ዕውቀት ያላቸው፣ ይዋኄንና ትዕግሥትን ገንዘብ ያደረጉ፣ ለዘለዓለም የማይነጥፍና የማያቋርጥ ይልቁንም ዘወትር እንደ ዝረት ውኃ የሚወርድ ምስጋና ያላቸው ናቸው /ሥነ ፍጥረት፣ በቀሲስ ስንታየኑና በዲ/ን ብርሃኑ አድማስ የተዘጋጀ፣ ገጽ 34/።

· ምንም እንኳን ከሰው በፊት ቢፈጠሩም አያረጁም። ዘወትር ውቦች፣ ብርቱዎችና ውርዙዋን ናቸው።

· ኢ-መዋትያን ናቸው (አይሞቱም) /ሉቃ.20፡36/። ይኸውም ልክ እንደ እኛ ነፍስ በእግዚአብሔር ፈቃድ የተደረገ ነው።

· እንደ ሰው አንድ ጊዜ ደግ ሌላ ጊዜ ክፉ በመሥራት አይዋልሉም።

ከሰው ምን ያመሳስላቸዋል ስንል ደግሞ፡-

Ü ምንም ረቂቃን ቢኾኑም ሕልውና ከአካል ጋር አላቸው። ዮሐንስ ዘደማስቆ የተባለ አባት ይኽን ሲያብራራው፡- “መላእክት ረቂቃን ናቸው የምንላቸው ከእኛ አንጻር ነው። ከማንም ጋር ከማይነጻጸረው ከእግዚአብሔር አንጻር ሲታዩ ግን ግዙፋን ናቸው። ፍጹም ረቂቅ እግዚአብሔር ብቻ ነውና” ብሏል።

Ü ምንም ረቂቃን ቢኾኑም ውሱናን ናቸው። እንደ ሰው በቦታ የሚገቱ ባይኾኑም መጠን አላቸው። መጠናቸውና አርዐያቸውም የተለያየ ነው። ቁመታቸው ከምድር እስከ ሰማይ የሚደርስ መላዕክት አሉ። በክንፋቸው

ብቻ አንድ አገር የሚያለብሱ መላዕክት አሉ። ራሳቸው ብቻ ተራራ የሚያክሉ መላዕክት አሉ። በዓይን የተቀረፀ የተሸለሙ ኹለንተናቸው ዓይን የኾነ መላዕክት አሉ። ስድስት ክንፍ ያላቸው መላዕክት አሉ። መብረቅ ለብሰው መብረቅ ተጐናጽፈው የሚኖሩ መላዕክት አሉ። ነፋስ ለብሰው ነፋስ ተጐናጽፈው የሚኖሩ መላዕክት አሉ። ብሩህ ደመና ጠምጥመው የሚኖሩ መላዕክት አሉ። እግራቸው ዓምደ እሳት የሚመስል መላዕክት አሉ። የእነዚኽን መላዕክት አርዓያቸውን መጠናቸውን ከእግዚአብሔር በቀር የሚያውቀው የለም /ኩፋ.2፡7-8/።

Ü ዐዋቂዎች ናቸው። ዕውቀታቸው ግን ሐዋርያው ጴጥሮስ እንደተናገረው ከሰው እጅግ ከፍ ያለ ነው /2ኛ ጴጥ.2፡11/። ምንም ከሰው እጅግ ከፍ ያለ ቢኾንም ግን ዕውቀታቸው መጠን አለው። ከእግዚአብሔርን በቀር ፍጹም ዕውቀት ያለው የለምና። እኛ ዕውቀታችን እንደ መላእክት የሚኾነው ከትንሣኤ ዘጕባኤ በኋላ ነው /1ኛ ቆሮ.13፡12/።

Ü ነጻ ፈቃድ አላቸው።

Ü እንደ ሰው ባሕርያቸውን የሚገልጽ ስም አላቸው።

ሰው ከመበደሉ በፊት ልክ እንደ መላእክት ንጹሕ፣ ውብና ብርቱ ነበር። በፍጥረታት ላይ ሥልጣን ነበረው። ርሱ ሲበድል ግን ከሥልጣን የወረደ ሰው እንደ ድሮ የሚያከብረው እንደሌለ ኹሉ ፍጥረታቱ አዳምን አልታዘዝ አሉት። እንደዉም ተበረታቱበት። ክብር ይግባውና ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣውም ወደ ቀድሞ ክብራችን ወደ ልጅነት ወደ ቀድሞ ቦታችን ወደ ገነት ከዚያም በላይ ወደ መንግሥተ ሰማያት ሊመልሰን ነው። በመኾኑም ሰው ምንም እንኳን በዚኽ ዓለም ሳለ ብዙ ውጣ

ውረዶችን ቢያሳልፍም በመጨረሻ መላእክትን ይመስላል። ለዚኽም ነው ቅዱሳን መላእክት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በዕብ.1፡14 ላይ እንደገለጸው ታናሽ ወንድማቸውን ሰውን በማገልገል ላይ ያሉት።

የመላእክት ትክክለኛ ስም ይታወቃልን?

ምንም እንኳን በስም በስም ብንጠራቸውም ስማቸው ነገረ እግዚአብሔርን የሚያስረዳ እንደኾነ እንጂ በቅጥነተ ጎሊና ስናስተውለው ማን ማን እንደሚባሉ አይታወቁም፤ ስም የሌላቸው ኾኖ ሳይኾን የሰው አዕምሮ ሊረዳው አይችልም። ለምሳሌ ገብርኤል ማለት አምላክ ወሰብእ ማለት ነው። ይኽም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ማንነትን የሚገልጽ እንጂ የመልአኩ ትክክለኛ ስም አይደለም። ሚካኤል ማለት መኑ ከመ እግዚአብሔር ማለት እንጂ የመልአኩ ስም አይደለም። በነገራችን ላይ የእግዚአብሔር ትክክለኛ ስሙም አይታወቅም፤ የለውም ማለት ሳይኾን ኹለንተናውን የሚገልጽ ስም በሰው ቋንቋ መግለጽ አይቻልም።

መላእክት መልክ አላቸውን?

በመጽሐፍ ቅዱስ ቅዱሳን መላእክት በተለያየ መልክ እንደተገለጹ እናነባለን። ለምሳሌ፡-

V በእሳት አምሳል /ዘጸ.3፡2-4/፤ ለሙሴ፤

V በዓምደ ብርሃንና ደመና አምሳል /ዘጸ.13፡21፣ 23፡20-21፣ ዘኁ.20፡16/፤ ለሕዝበ እስራኤል፤

V በተራ ሰው አምሳል /መሳ.6፡12-23/፤ ለጌድዮንና ለጦቢት፤

V በነቢይ አምሳል /መሳ.13፡6/፤ ለማኑሄ ሚስት፤

V በእሳት ፈረስና ሰረገላ አምሳል /2 ኛ ነገ.6፡16-17/፤ ለኤልሳዕ ሎሌ፤

V በእሳት አምሳል /ሕዝ.8፡2/፤ ለነቢዩ ሕዝቅኤል፤

V በፍታ እንደ ለበሰ፣ ወገቡም በወርቅ እንደታጠቀ ሰው /ዳን.10፡5/፤ ለነቢዩ ዳንኤል፤

V ልክ እንደ ትሑት ሰው /ሉቃ.1፡12-13/፤ ለዘካርያስና ለእመቤታችን፤

V የጌታ ክብር በዙርያቸው ኾኖ /ሉቃ.29-30/፤ ለእረኞች፤

ይኽም ማለት መላእክቱ ሰው እንዲገባው በሰው አእምሮ መጠን ተገለጡ ማለት እንጂ መልካቸው ተለዋዋጭ ነው፤ የራሳቸው የኾነ ቋሚ መልክም የላቸውም ማለት አይደለም።

የመላእክት ተግባር ምንድነው?

የመላእክት ተግባር እንደሚከተለው ማየት ይቻላል፡-

Ø ያለማቋረጥ እግዚአብሔርን “ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ” እያሉ ያመሰግናሉ /ኢሳ.6/፤

Ø የእግዚአብሔርን መልካም ዜና ወደ ሰው ያመጣሉ። ይኸውም ለአጋር፣ ለአብርሃም፣ ለሐና እመ ሳሙኤል፣ ለካህኑ ዘካርያስ ለእመቤታችን እንዳመጡላቸው ማለት ነው።

Ø ማስተዋልንና ጥበብን ለሰው ልጆች ያድላሉ። ይኸውም ቅዱስ ገብርኤል ለነቢዩ ዳንኤል፣ ቅዱስ ዑራኤልም ለዕዝራ እንዳደረጉት ማለት ነው።

Ø ሰውን ከጥፋት ያድናሉ። ይኸውም ሎጥን ከሰዶምና ገመራ ሰዎች ጋር እንዳይጠፋ /ዘፍ.19/፣ ሠለስቱ ደቂቅን ከሚነድ እሳት እንዳዳኗቸው ማለት ነው /ዳን.3፡12-30/። መዝሙረኛው ክቡር ዳዊት፡- “የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙርያ ይሰፍራል፤ ያድናቸውማል” /መዝ.34፡7/፤ በሌላ ቦታም “ክፉ ነገር ወደ አንተ

አይቀርብም መቅሰፍትም ወደ ቤትህ አይገባም። በመንገድህ ኹሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና። እግርህም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሱኻል” ያለውም ስለዚኹ ነው /መዝ.91፡ 10-12/።

Ø የሰውንም መልእክት ወደ እግዚአብሔር ያደርሳሉ። የሰውን መልእክት ወደ እግዚአብሔር ያደርሳሉ ሲባል ምን ማለት እንደኾነ የቆጵረሱ ሊቀ ጳጳስ ሊቁ ኤጲፋንዮስ በአክሲማሮስ መጽሐፉ ላይ፡-“ (የካህናተ ሰማይ ማዕጠንት) የጻድቃን ጸሎት፤ የሰማዕታት ገድል፤ የደጋግ ሰዎች ምግባር ነው” ብሎ ያብራሯል /መጽሐፈ አክሲማሮስ፣ ገጽ 51/።

Ø የእግዚአብሔርን ቁጣ ወደ ሰዎች ያመጣሉ። እነርሱም የመዓት መላእክት የሚባሉ ሲኾኑ በትዕቢቱና በክፋቱ ከሥልጣኑ የወረደው የዲያብሎስ ሠራዊት የነበሩና በኋላ ግን አለቃቸው ሲክድ ያልካዱ በእምነታቸው የፀኑ ከሣጥናኤል ሠራዊትነት ተለይተው ከነቅዱስ ሚካኤልና ከነቅዱስ ገብርኤል ጋር የተደመሩት ናቸው። እነዚኽ የመዓት መላእክት እጅግ ቁጡዎችና ቀናተኞች ናቸው።

ጠባቂ መልአክ

ከቡር ዳዊት “ክፉ ነገር ወደ አንተ አይቀርብም መቅሰፍትም ወደ ቤትህ አይገባም። በመንገድህ ኹሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና። እግርህም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሱኻል” እንዳለው /መዝ.91፡10-12/ እያንዳንዱ ሰው ጠባቂ መላእክት እንዳሉት ያስረዳል። እስራኤል ዘሥጋን የጠበቃቸው መልአክ ቅዱስ ሚካኤል ነው። ይኽንንም ለኢያሱ በኢያሪኮ አጠገብ ነግሮታል /ኢያ.5፡

14-15/። ይሁዳም የመልእኩ ስም ማን እንደኾነ በግልጽ ነግሮናል /ይሁዳ ቁ.9/።

አስቀድመን እንደተመለከትነው ለእያንዳንዱ ሰው ብቻ ሳይኾን ለእንስሳት፣ ለዕፅዋት፣ ለምድር፣ ለፀሐይ፣ ለጨረቃ፣ ለከዋክብት፣ ከምድርም በታች ለተፈጠሩ ፍጥረታት በሙሉ ጠባቂ መላእክት አሏቸው። ለምሳሌ እንስሳትን የሚጠብቀው መልአክ ሰላታኤል ይባላል። አናንኤል የሚባለው ነገደ መላእክት ደግሞ እንደ ብረት የጸና የእሳት ነጐድጓድን ወደ ምድር የሚወነጭፉ፣ ፀሐይን ጨረቃን ከዋክብትን አዝርዕትን አትክልትን ዕፅዋትን ከምድር በላይ ከሰማይ በታች የተፈጠሩትን የሚጠብቁ ናቸው /ኩፋሌ 2፡ 6-8/።

ቅዱስ ባሲልዮስ ዘቂሳርያ ሰውን ስለሚጠብቁ መላእክት ሲናገር፡- “ክፉ ሥራ ካልሠራን በቀር ጠባቂ መልአካችን ከእኛ አይለይም። ጭስ ንብን ከቀፎው እንዲወጣ እንደሚያደርገው ኹሉ የእኛ ኃጢአትም ጠባቂ መልአካችን ከእኛ እንዲለይ ያደርጓል” ብሏል።

መላእክት - የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ናቸው!!!

ቅዱሳን መላእክት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ናቸው። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ ብልት ናትና መላእክትም ቤተ ክርስቲያንን ያገለግላሉ። የጌታችንን ሰው መኾን ያበሰሩን መላእክት ናቸው። በቤተ ልሔም ግርግም ሲወለድ እጅግ ደስ ብሏቸው ያመሰገኑት መላእክት ናቸው። ስለ ልደቱ ለእረኞች የነገሯቸው መላእክት ናቸው። ወደ ግብጽ ሲሰደድ አብረዉት የሔዱ መላእክት ናቸው። በፈለገ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ ተጠምቆ ወደ ገዳመ ቆሮንቶስ በሔደ ጊዜ ያገለገሉት መላእክት ናቸው። ጌታችን

በጌተሴማኒ የአታክልት ስፍራ ሲጸልይ ሲያበረቱት የነበሩት መላእክት ናቸው። አይሁድ ሊሰቅሉት ሲሉ ቸርነቱ ከልክሏቸው እንጂ አይሁድን ለማጥፋት የተዘጋጁት መላእክት ናቸው። ደሙን ወደ ዓለም ኹሉ የረጨት መላእክት ናቸው። ትንሣኤውን ያበሠሩን መላእክት ናቸው። ሲያርግ ደግሞም ዳግም እንደሚመጣ የነገሩን እነዚኽ መላእክት ናቸው። ዳግም ሲመጣ አብረዉት የሚመጡትና ሙታንን የሚቀሰቅሱትም እነዚኽ ቅዱሳን መላእክት ናቸው።

ይኽ አገልግሎታቸው በሐዋርያትም የተመለከትነው ነው። ሊቀ ካህኑ ሐዋርያቱን ሲያስራቸው ሰንሰለታቸውን የፈቱላቸው መላእክት ናቸው /ሐዋ.5፡17-20፣ 12፡7-10/። የገሊላው ንጉሥ ይሁዳ ሐዋርያው ያዕቆብን ከገደለው በኋላ ጴጥሮስንም ሊገድለው ሲል በትል ተበልቶ እንዲሞት ያደረጉት መላእክት ናቸው /ሐዋ.12፡23/። ፊሊጶስ በሰማርያ እያስተማረ ሳለ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባን አስተምሮ እንዲያጠምቀው የነገሩት ቅዱሳን መላእክት ናቸው /ሐዋ.8፡26/። ሐዋርያትን እየመሩ፣ አሕዛብንም እያዘጋጁ ወንጌል በአሕዛብ አገር እንዲስፋፋ ያደረጉት ቅዱሳን መላእክት ናቸው /ሐዋ.10/። እነ ቅዱስ ጳውሎስ መርከብ በአውሎ ነፋስ ቀንና ሌሊት ስትናወጥ አንዲት ነፍስ እንኳን እንደማትጠፋ ያጽናኗቸው ቅዱሳን መላእክት ናቸው /ሐዋ.27፡20-25/። በአጠቃላይ ቅዱሳን መላእክት ከክርስቶስ ደግሞም ብልቱ ከምትኾን ከቤተ ክርስቲያን (ይኸውም ከእኛ ከምእመናን) አይለዩም። ክብር ይግባውና ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውን እጅግ አድርጎ ይወዳል። እነዚኽ ቅዱሳን መላእክትንም ጠባቂ አድርጎ ይልክላቸዋል፤ ይልክልናል።

በሥራችን ኹሉ ለሚጠብቁን፣ ዘወትር በኃጢአት ስንወድቅ ደግፈው ለሚያነሡን፣ በኃጢአት ስንጨማለቅ “ለዛሬ ተዋት” እያሉ ስለ እኛ መዳን ፈጣሪን ለሚማልዱልን /ሉቃ.13፡7-9/፣ በእኛ ንስሐ መግባት ስለ እኛ በሰማያት ድል ያለ ምስጋና ለሚያቀርቡ /ሉቃ.15፡7/፣ እንቅፋት እንዳይመታን ለሚጠብቁን፣ በርኩሳን መናፍስት አንድም በፈቃደ ሥጋችን ላይ እንድንሠለጥን ለሚራዱን ለእነዚኽ ቅዱሳን መላእክት ውለታ ታድያ እንዴት መክፈል ይቻለናል? እነዚኽን ጠበቃዊቻችን ለሰጠን እግዚአብሔርስ ተመስገን ከማለት በቀር ምን ማለት እንችላለን?

በረከትና ክብር ጥበብም ምስጋናም ውዳሴም ኃይልም ብርታትም ለዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ ለአምላካችን ይኹን አሜን /ራዕ.7፡12/።

Kesis Dibekulu Belay

ዘና ብላችሁ ተቀመጡና አንድ አሪፍ ታሪክ ልንገራችኹ!

5/ የተከበሩት አባት እንዲህ ብለው ጠየቁ፤

መላእክት እንደ ሰው የሚታጠፍ እና የሚዘረጋ እግረ ሥጋ የላቸውም፤ ታዲያ መላኩ ቅ/

ገብርኤል እኔ በእግዚአብሔር ፊት “የምቆመው” ገብርኤል ነኝ ሲል ምን ማለቱ ነው??

ሉቃስ [1: 19]

ይህች ጥያቄ ያለንበትን ክፍል ዝም አስባለች። ኹላችንም በልባችን ለምን

ይኾን? እያልን

መጠየቅ ጀመርን።

የተከበሩት አባት መልሱን እንዲኽ እያሉ አስረዱን፤ በእርግጥ ግሩም ጥያቄ ነው፤

መላእክት መንፈስ ናቸውና እግረ ሥጋ የላቸውም፤ አይቀመጡም አይነሱም አይቆሙምም! ሊቀ መላእክት ቅ/ገብርኤል እኔ በእግዚአብሔር ፊት "የምቆመው"

ገብርኤል ነኝ ማለቱ ምህረትን ጠያቂ አማላጅ ነኝ ሲል ነው አሉን።

በክፍላችን ውስጥ የነበሩ የሌላ እምነት ተከታዮች ነበሩና "አሁን ማን ይሙት ይኼ

ከአማላጅነት ጋር በምን ይገናኛል?" አሉ በልባቸው። ይኽን ሐሳባቸውን የተከበሩት አባት

ስለገባቸው ፍግግ አሉ። እንዴት ማለት ጥሩ ነውና እንዴት? እንበል አሉን። እንዴት አልን

በልባችን። እንዲህ ብለው ቀጠሉ፦

ይህን እንድንረዳ ልበ አምላክ ዳዊት የዘመረውን አብረን እንይ፤ የተመረጠው ሙሴ

በእግዚአብሔር ፊት "ባይቆም" ኖሮ ሕዝበ እሥራኤላዊያን በቅጽበት በጠፉ ነበር ይለናል

መዝ. [105:23] ሙሴ ቀጥ ብሎ ስለ ቆመ አይደለም እስራኤላዊያን ምሕረት ያገኙት፤

ሕዝቡን ከምታጠፋ ሥሜን ከሕይወት መጽሐፍ ላይ ደምስስ!!! እያለ

የለመነው ልመና

ነው እስራኤላዊያንን ያስማራቸው ዘፀአት [32:32]

ስለዚህም “መቆም” ማለት ቀጥ ብሎ መቆም ብቻ ሳይሆን መለመን ፣ ማማለድ እንደሆነ

ባህረ ጥበብ የሆነች ቤተክርስቲያናችን እንዲህ ከመጽሐፍ ቅዱስ እያበሰለች ትመግበናለች!

የተከበሩት አባት በግርማ ሞገሳቸው ጎርደድ እያሉ “እስኪ በአንድምት እንምጣ” አሉ።

አንድም ስለ ሕዝቡ “የሚቆመው” ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሳል ዳንኤል [12:1] ቅ/

ሚካኤል እግረ ሥጋ የለውም፤ ስለ እኛ ምህረትን ይለምናል እንጂ። አንድም መላዕክትም

በእግዚአብሔር ፊት “ለመቆም” መጡ፤ ሰይጣንም በመካከላቸው ነበር። ኢዮብ [1:6]

ሰይጣን ከሳሽ ስለሆነ ቆመ አልተባለም መላዕክቱም ቆሙ የተባሉት ቀጥ ብለው ቆሙ

ለማለት አይደለም፤ ሊለምኑ መጡ ለማለት ነው እንጂ። አንድም እግርህ በድንጋይ

እንዳይመታ “በእጆቻቸው ያነሱሃል” ይላል፤ መዝ. [90: 11] መላዕክት እንደ ሰው እጅ

የላቸውም መንፈስ ናቸውና፤ ነገር ግን ሎጥን ከሰዶም እሣት እጁን ይዘው እንደወጡ

ፈጥነው ደራሽ መሆናቸውን ሲያስረዳን ነው።

አንድም መላዕክት እንደ ሰው የሚያዩበት ዓይነ ሥጋ የላቸውም፤ መንፈስ ናቸውና፤

በወንጌል ግን ጌታችን እንዲህ አለ፦ ከታናናሾቻችሁ ማንንም እንዳትንቁ ተጠንቀቁ ጠባቂ

መላእክቶቻቸው ዘወትር የአባቴን ፊት “ያያሉና” ማቴ. [18:10] “ያያሉና” ማለት መላዕክት

በዓይናቸው እግዚአብሔርን ያያሉ ለማለት አይደለም; መላዕክት ዓይነ ሥጋ የላቸውም

ተብሏልና፤ “ያያሉ ማለት ይለምናሉ” ለማለት ነው፤ አንድም እግዚአብሔርን ያየ ከቶ

ማንም የለም ይለናል፤ 1ኛዮሐ.[4: 12] “ያያሉ” ማለት ይለምናሉ ማለት እንደሆነ

አየህን?

አንድም “ጠባቂ መላእክቶቻቸው” የሚለውን ስንመለከት “ጠባቂ” የሚለው ቃል መላዕክት

ጠባቂ እንደሆኑ አይነግረንምን? አንድም “መላእክቶቻቸው” የሚለው ቃል እያንዳንዱ ሰው

፪ ውቃቢ መልአክ /ጠባቂ መልአክ/ እንዳሉት አይነግርህምን? ፭ዱ በቀን ሲጠብቅህ ፭ዱ

በለሊት እንደሚጠብቅህ አታውቅምን? አሉ የተከበሩት አባት በማይጠገብ ፈገግታቸው

እያዩን። ይህችንም ማስታወሻ ሰጡን፦ “የጥቅስ ጥናት ዘዴ”

የቅ/ሚካኤል በዓል የሚውለው በ 12 ነው ስለዚህ ዳንኤል [12:1]

የቅ/ገብርኤል በዓል የሚውለው በ 19 ነው ስለዚህ ሉቃስ [1: 19]

የተከበሩት አባት ውድ ልጆቼ ሆይ ይህን ሁሉ ባሕረ ጥበብ ቤተክርስቲያን ታስተምረናለችና “ይህች ቤተክርስቲያን ግሩም ድንቅ ናት!” አሉን። ይህን ሲሉ ለመጻፍ

የማይቻል አንዳች የመንፈስ ደስታ ይታይባቸው ነበር።

“ይህች ቤተክርስቲያን ግሩም ድንቅ ናት!” አሉ በድጋሚ፤ እኛም “ይህች ቤተክርስቲያን

ግሩም ድንቅ ናት!” አልን በልባችን።

Miko ZE Ethiopia

6/ ስለ 99ኙ ነገደ መላእክት ምስጢር ከመጽሐፈ ሰዓታት ትርጓሜ መጽሐፌ የተወሰደ

ከመጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ

መላእክት በነገድ 100 ሲኾኑ ስመ ነገዳቸው አጋዕዝት፣ ኪሩቤል፣ ሱራፌል፣ ጎይላት፤ አርባብ፣ መናብርት፣ ሥልጣናት፤ ሊቃናት፣ መላእክት ይባላሉ። ነገደ አጋእዝት ያላቸው አስቀድመው አለቃቸው ሳጥናኤል የነበረ ሲኾን ርሱ በካደ ጊዜ ከርሱ ነገድ ተከፍለው ከነገደ ሚካኤል የተደረቡ አንድ ክፍል ሲኾኑ በመጽሐፈ ኪዳንም “አጋዕዝት በመሐልይ ይሴብሑከ” (አጋዕዝት በማሕሌት ያመሰግኑኻል) የተባሉት እነዚኽ ናቸው።

ነገደ ኪሩቤል የሚላቸው ገጸ ብእሲ እና ገጸ አንበሳ ሲኾኑ አለቃቸው ኪሩብ የተባለው መልእክ ነው።

ነገደ ሱራፌል የሚላቸው ገጸ ላሕም እና ገጸ ንስር ሲኾኑ አለቃቸው ሱራፊ የተባለው መልአክ ነው።

ዮሐንስም በራእዩ ላይ በፍርሀት ኾነው ዙፋኑን ስለሚሸከሙት ስለ አርባእቱ እንስሳ ሲገልጽ "በዙፋኑም ፊት ብርሌ የሚመስል የብርጭቆ ባሕር ነበረ፤ በዙፋኑም መኻከል በዙፋኑም ዙሪያ በፊትና በኋላ ዐይኖች የመሏቸው አራት እንስሶች ነበሩ፤ ፊተኛውም እንስሳ አንበሳን ይመስላል፤ ኹለተኛውም እንስሳ ጥጃን ይመስላል፤ ሦስተኛውም እንስሳ እንደ ሰው ፊት ነበረው፤ አራተኛውም እንስሳ የሚበርረውን ንስር ይመስላል፤ አራቱም እንስሶች እያንዳንዳቸው ስድስት ስድስት ክንፎች አሏቸው በዙሪያቸውና በውስጣቸውም ዐይኖች መልተውባቸዋል፤ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ የነበረውና ያለ የሚመጣውም ኹሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ እያሉ ቀንና ሌሊት አያርፉም" በማለት የኪሩቤልን የማያቋርጥ ምስጋናቸውን ተናግሯል (ራእ 4፥6-7)።

ሊቁ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ የሥነ ፍጥረት ነገር ተገልጾለት በጻፈው መጽሐፍ ላይ "ወለዳግም ጸታ ዐሠርቱ ስሞሙ ኪሩቤል ካህናተ ቅዳሴ ወውዳሴ እምታሕተ ሐቌሆሙ አሐዱ ወእምላዕለ ሐቌሆሙ አርባዕቱ እለ ግሉፋን በአዕይንት" ብሎ እንደገለጸው ኹለተኛውን አመስጋኞች የኾኑት ዐሥሩን ነገድ ስማቸውን ኪሩቤል ሲላቸው ከወገባቸው በታች አንድ ከወገባቸው በላይ አራት አድርጎ ሲፈጥራቸው ዐይናቸው ብዙ ነው፤ ይኽም ጎላፍያትን መጻእያትን በማወቃቸው ይተረጐማል፤ አለቃቸው ኪሩብ ሲኾን የሰው

መልክና የአንበሳ መልክ ያለው ነው። ሦስተኛውን ዐሥራን ነገድ ስማቸውን ሱራፌል ሲላቸው የእነዚኽ አለቃቸው የንስር መልክና የእንስሳ መልክ ያለው ሲኾን ሱራፊ ሲባል ሲፈጥራቸውም ስድስት ስድስት ክንፍ አድርጎ ፈጥሯቸዋል (ሕዝ 1፥4-11)

ሊቁ ኤጲፋንዮስም የሥነ ፍጥረትን ነገር በሚናገረው መጽሐፉ ላይ አኗኗራቸውን በጥልቀት ሲተነትነው “ወነሥአ እግዚአብሔር እምሰራዊተ ኪሩቤል ክልኤተ አርእስተ ዘውእቶሙ ገጸ ሰብእ ወገጸ አንበሳ ወዓዲ ነሥአ እግዚአብሔር እምሰራዊተ ሱራፌል ክልኤተ ክልኤተ አርእስተ ዘውእቶሙ ገጸ ንስር ወገጸ እንስሳ ወለክኦሙ መልዕልተ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት በማእዘንተ መርሕባ ለአርያም ወሰፍሐ ዲበ ዘባናቲሆሙ ሰማየ ዘሕብሩ በረድ” ይላል ከነገደ ኪሩቤል ኹለት ገጸ ሰብእ እና ገጸ አንበሳን ከሱራፌል ኹለት ገጸ ንስርና ገጸ እንስሳን አንሥቶ ከኢየሩሳሌም ሰማያዊት በላይ ከሰማይ ውዱድ በታች አቁሞ በነርሱ ላይ ሰማይ ውዱድን እንደ መረሻት ጫነባቸው፤ በላይም ሕብሩ በረድ የመሰለውን ዙፋን እንደ ሠረገላ ጭኖባቸዋል፤ እነዚኽንም በምሥራቅ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን፣ በደቡብ በአራቱ መኣዝን ዠርባቸውን ወደ ውስጥ ፊታቸውን ወደ ውጪ እያደረገ አቁሟቸዋል፤ ነቢዩ ሕዝቅኤል ስለዚኽ ነገር በምዕ ፩፥፲፪ ላይ “እያንዳንዱም ወደ ፊት ቀጥ ብሎ ይኼድ ነበር መንፈስም ወደሚኼድበት ኹሉ ይኼዱ ነበር፥ ሲኼዱም አይገላመጡም ነበር” በማለት እንደተናገረ ገጽ ለገጽ ሳይተያዩ ሥላሴ በፈቀዱት ፍኖት አንዱ በኼደበት ሦስቱ እየተከታተሉ ይኼዳሉ።

እነዚኽንም እንደ ነቢዩ ሕዝቅኤል ገለጻ 16 ሲኾኑ የቀሩት ከውስጥ

ስለኾኑ ስለማይታዩ አራቱ ግን ብቅ ብቅ ብለው ስለሚታዩ ዮሐንስ አራት ብሏቸዋል እንጂ እንደ ሕዝቅኤል ገጻቸው ፲፮ ነው። ሊቁ "እምርእሶሙ እስከ ሐቌሆሙ አርባዕቱ ወእምሐቌሆሙ እስከ እግሮሙ አሐዱ ከመ ርእየተ እለ ቄጥሩ ዘውእቱ ዖፍ ዘይነብር በሀገረ ፋርስ" እንዲላቸው፤ ሊቁ ቅዱስ ያሬድም "ከመ ርእየተ እለቄጥሩ ገጸ በገጽ ኢይትናጸሩ" ብሎ እንደገለጻቸው በፋርስ ሀገር የሚኖረው እለቄጥሩ የተባለውን ዖፍ ከወገቡ በታች አንድ ከወገቡ በላይ አራት እንደኾነ እነዚኽንም ከወገባቸው በታች አንድ ከወገባቸው በላይ አራት አድርጎ ፈጥሯቸዋል፤ የገጸ ሰብእ አቋቋሙ በምሥራቅ አተያዩ ወደ ምዕራብ ነው፤ የገጸ አንበሳ አቋቋሙ በምዕራብ አተያዩ ወደ ምሥራቅ፤ የገጸ ላሕም አቋቋሙ በሰሜን አተያዩ ወደ ደቡብ፤ የገጸ ንስር አቋቋሙ በደቡብ አተያዩ ወደ ሰሜን ሲኾን ገጽ ለገጽ አይተያዩም ።

እነዚኽ አርባዕቱ እንስሳ ያላቸው የመልክ ገጽታ በአራቱ ወንጌላውያን ተመሳስሎ ሲመሰጠር ዳግመኛም ከምስጢረ ሥጋዌ ጋር አገናኝተው የተረጐሙ ቀደምት ሊቃውንት አሉ፤ ይኸውም የሰው መልክ ያለው በገጹ የጌታን ሰው መኾን የሚያመላክት መኾኑን፤ የላም መልክ ያለው በገጹ የጌታን በቀራንዮ ሥጋዉን መቁረስና ክቡር ደሙን ማፍሰስ (የመሥዋዕትነቱን)፤ የአንበሳ መልክ ያለው መልአክ በገጹ የይሁዳ አንበሳ የተባለ የጌታ የትንሣኤውን፤ የንስር መልክ ያለው መልአክ የክርስቶስን ዕርገቱን አመላካች ናቸው በማለት መተርጕማን ያመሰጥራሉና፤ ሊቁ ይኽነን ኹሉ ምስጢር እንደ ወርቅ አንከብልሎ እንደ ሸማ ጠቅልሎ፦-

"ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ዘይፈርህዎ ኪሩቤል ወእምግርማሁ

ይርዕዱ ሱራፌል”

“ኪሩቤል የሚፈሩትና ሱራፌልም ከግርማው የተነሣ የሚርዱለት እግዚአብሔር ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ ተብሎ በአንድነት በሦስትነት ይመሰገናል (ንጹሕ፣ ጽኑዕ፣ ክቡር፣ ልዩ ነው)” በማለት አመስግኖታል።

ነገደ ኀይላት ያላቸው ቅዱስ ሚካኤል የሚመራቸው በኢዮር ሰማይ የሚኖሩ ናቸው፤ ሊቁ ቅዱስ ኤጲፋንዮስም በሥነ ፍጥረት መጽሐፉ ላይ “ወለራብዕ ጸታ ዐሠርቱ ስሞሙ ኀይላት ወሊቆሙ ሚካኤል ወአንበሮሙ በራብዕ ሰማይ” ይላል አራተኛው ዐሥሩን ነገድ ስማቸውን ኀይላት ሲላቸው እነዚኽም ባለሰይፍ ሲኾኑ የእግዚአብሔርን ወዳጆች ሲጠብቁ ጠላቶቹን ይቀጣሉ፤ የእነዚኽ ነገደ መላእክት አለቃቸው ቅዱስ ሚካኤል ሲኾን በኢዮር በአራተኛው ከተማ አስፍሯቸዋል።

ነገደ አርባብ ያላቸው ቅዱስ ገብርኤል የሚመራቸው በራማ ሰማይ የሚኖሩ ናቸው ሊቁ በመጽሐፈ አክሲማሮስ ላይ “ለቀዳሚ ጸታ ዐሠርቱ ስሞሙ አርባብ ወሊቆሙ ገብርኤል መልአክ ታዕካሁ ለሕያው ዘለዓለም ወአንበሮሙ በቀዳሚት ሰማይ” እንዲላቸው በራማ ያሉትን መላእክት ሦስት አለቃ ሠላሳ ነገድ አድርጎ ሲከፍላቸው የመዠመሪያዎቹን ዐሥሩን ነገድ ስማቸውን አርባብ ሲላቸው ነገዱን በአለቃነት የሚመራው ቅዱስ ገብርኤል ነው።

ነገደ መናብርት ያላቸው ቅዱስ ሩፋኤል የሚመራቸው በራማ ሰማይ የሚኖሩ ነገደ መላእክት ናቸው። ቅዱስ ኤጲፋንዮስም በሥነ ፍጥረት መጽሐፉ ላይ “ወለዳግም ጸታ ዐሠርቱ ስሞሙ መናብርት ወሊቆሙ ሩፋኤል እሉ እሙንቱ እለ ይቀልል ሩጸቶሙ እምነፋስ ወእለ ይጸውሩ ወላትወ መብረቅ

ወኩናተ እሳት ዘይነድድ ወአንበሮሙ በዳግሚት ሰማይ" ይላል በራማ ሰማይ የሚገኘውን ኹለተኛውን ዐሥሩን ነገድ መናብርት ሲላቸው አለቃቸው ቅዱስ ሩፋኤል ነው፤ እነዚኽም ረቂቅ የኾነ የመብረቅ ጋሻ የእሳት ጦር ይዘው ከነፋስ ይልቅ የፈጠኑ ሲኾኑ በራማ በኹለተኛው ክፍል ላይ አስፍሯቸዋል።

ሥልጣናት፡- ይኸውም ሊቁ የጠቀሳቸው መላእክት ከሚኖሩባቸው ከሦስቱ ሰማያት ከኢዮር፣ ከራማ፣ ከኤረር መኻከል በኹለተኛዋ በራማ ውስጥ ከሚኖሩት ከዅው ነገድ ውስጥ ሲኾኑ የመጨረሻው ነገድ "ሥልጣናት" ይባላል፤ ስለነዚኽ ነገደ መላእክት ሊቁ ኤጲፋንዮስ በአክሲማሮስ ላይ ሲገልጽ "ወለሣልስ ጾታ ዐሠርቱ ስሞሙ ሥልጣናት ወሊቆሙ ሱርያል መልአክ ወአንበሮሙ በሣልስ ሰማይ እሉ እሙንቱ እለ ይጸውሩ አብዋቀ ብርሃን ወያደምፁ ለመላእክት በጊዜ ቅዳሴሁ ወስባሔሁ ለእግዚአብሔር ለዘክሮቱ ይደሉ ሰጊድ" ይላል ለስም አጠራሩ ስግደት ይግባውና ልዑል እግዚአብሔር ሦስተኛ ዐሥሩን ነገድ ሥልጣናት ሲላቸው አለቃቸው መልአኩ ሱርያል ይባላል፤ እነዚኽም የብርሃን ነጋሪት የሚይዙ ሲኾኑ መላእክትን ለስባሔ ሲያነቁ ሲያተጉ የሚኖሩ እነዚኽ መላእክት ሲኾኑ፤ በራማ በሦስተኛው ከተማ አስፍሯቸዋል ።

ሊቃናት፡- ያላቸው ቅዱስ ሰላትያል የሚመራቸው ነገደ መላእክት ናቸው ቅዱስ ኤጲፋንዮስም በመጽሐፉ ላይ "ወለዳግም ጾታ ዐሠርቱ ስሞሙ ሊቃናት ወሊቆሙ ሰላትኤል እለ ይጼአኑ በአፍራሰ እሳት ወድሩዓን በነደ እሳት ወውኩላን ለዐቂበ ኩሉ ዘሥጋ ወአንበሮሙ በዳግሚት ሰማይ" ይላል ኹለተኛው ዐሥሩን ነገድ ስማቸውን ሊቃናት ሲላቸው አለቃቸውም ሰላትኤል ይባላል፤ ረቂቅ በኾነ በአፍራሰ እሳት ተቀምጠው የእሳት

መጐናጸፊያን ተጐናጽፈው በከዋክብት አምሳል የብርሃን ሰላጤን ይዘው በልባቸው የሚሳቡ፣ በእግራቸው የሚሽከረከሩ፣ በክንፍ የሚበሩ በደመ ነፍስ ሕይወት ሕያዋን ኹነው ጸንተው የሚኖሩ የባሕር ፍጥረታትን የሚጠብቁ መላእክት ሲኾኑ እነዚኽንም ከነአለቃቸው በኤረር ሰማይ በኹለተኛው ከተማ አስፍሯቸዋል።

መኳንንት፡- ያላቸው ቅዱስ ሰዳክያል የሚመራቸው ነገደ መላእክት ናቸው፤ ሊቁ በሥነ ፍጥረት መጽሐፉ ላይ "ለቀዳሚ ጾታ ዐሠርቱ ስሞሙ መኳንንት ወሊቆሙ ሰዳክኤል እሉ እሙንቱ እለ ይነድፉ በሐጸ እሳት ወነፋስ ዘይሰጥቅ ዕብነ ወቀላያተ አድባረ ወአውግረ ወውኩላት ለዐቂበ ዕጓለ እመ ሕያው ወያስተጋብዑ አዕጽምተ ሰብእ አመ ትንሣኤ ሙታን በዳግም ምጽአቱ ወአንበሮሙ በቀዳሚት ሰማይ" ይላል ኤረር የተባለችውን የብርሃን ሰማይ ለሦስት ከፍሎ የመዠመሪያውን ዐሥሩን ነገድ ስማቸውን መኳንንት ሲላቸው አለቃቸው ቅዱስ ሰዳክኤል የተባለ መልአክ ነው፤ እነዚኽም ተራራ የሚንድ ድንጋይ የሚሠነጥቅ የእሳት ፍላጻ፣ የእሳት ቀስት ይዘው ሰውን ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ ሲጠብቁ የሚኖሩ ቅዱሳን መላእክት ሲኾኑ ኋላም በትንሣኤ ዘጉባኤ የባሕርይ አምላክ ክርስቶስ ዓለምን ለማሳለፍ ለፍርድ ሲመጣ የሰውን ኹሉ ዐጥንት ሰብስበው ለትንሣኤ የሚያበቁ መላእክት ሲኾኑ እነዚኽንም በኤረር ሰማይ በላይኛው ከተማ ከነአለቃቸው አስፍሯቸዋል፤ ጌታም ስለ ኀልቀተ ዓለም ሲያስተምር "የሰማያትም ኀይላት ይናወጣሉ በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል በዚያን ጊዜም የምድር ወገኖች ኹሉ ዋይ ዋይ ይላሉ የሰው ልጅንም በኀይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል፤ መላእክቱንም ከታላቅ መለከት ድምፅ ጋር

ይልካቸዋል ከሰማያትም ዳርቻ እስከ ዳርቻው ከአራቱ ነፋሳት ለርሱ የተመረጡትን ይሰበስባሉ" በማለት ተናግሮላቸዋል (ማቴ ፳፬፥፴-፴፩)።

ዳግመኛም በኹሉም ነገድ የሚኖሩት ስማቸው መላእክት ቢባልም፤ ነገር ግን ሊቁ የጠቀሳቸው በኤረር ከሚኖሩት ከሷው ነገድ የመጨረሻውን ነገድ ነው፤ ስለነዚኽ ነገድ ሊቁ ኤጲፋንዮስ ሲገልጽ "ወለሣልስ ጾታ ዐሠርቱ ስሞሙ መላእክት ወሊቆሙ አናንያል እሉ እሙንቱ እለ ይዌጽፉ በሞጸፍተ ነጐድጓድ አዕባነ እሳት ዘነጺን ወውኩላን ለዐቂበ ኩሉ ፍጥረት ፀሓይ ወወርኀ ወከዋክብት ዘእምታሕተ ሰማይ ወእምላዕለ ምድር ዘየዐቅብዎ መላእክት ወአንበሮሙ በሣልስ ሰማይ" ይላል በኤረር የሚኖሩትን ሦስተኛውን ዐሥራን ነገድ ስማቸውን መላእክት ሲል አለቃቸውም መልአኩ አናንያል ይባላል፤ እነዚኽም ረቂቅ የኾኑ የብረት ወገን የሚኾኑ የእሳት ደንጋዮችን በምድረ ነጐድ ወንጭፎች የሚወነጭፉ፤ ፀሓይን፣ ጨረቃን፣ ከዋክብትን ከሰማይ በታች ከምድር በላይ ያለውን የሚጠብቁ ጠባቂ መላእክት ሲኾኑ፤ እነዚኽን ዐሥር ነገድ ኤረር በተባለው ሰማይ በሦስተኛው ከተማ አስፍሯቸዋል (ኩፋ ፪፥፯)።

ሞትን ድል አድርጎ የተነሣው በአብ ዕሪና የተቀመጠው አምላካችን በነዚኽ ነገደ መላእክት የሚመሰገን ስለመኾኑ ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ፪ጴጥ ፪፥፲፪ ላይ "ርሱም መላእክትና ሥልጣናት ኀይላትም ከተገዙለት በኋላ ወደ ሰማይ ኼዶ በእግዚአብሔር ቀኝ አለ"

በማለት ነገዳቸውን ጠቅሶ አስተምሯል።

እነዚኽ መላእክት ሰው የጸለየውን ጸሎት ያቀረበውን መሥዋዕት ቅድመ እግዚአብሔር በማድረስ የእግዚአብሔርን ምሕረት ወደ ሰው በማምጣት

ሰውን ከአምላካቸው ጋር በማማለድ ጸንተው ያሉ እንደኾኑ በብዙ ሥፍራ ላይ ተዘርዝሯል፦ ለምሳሌ ያኽል ዘፍ 48፥15፤ ዘጸ 23፥20፤ መሳ 6፥11፤ ኢዮ 33፥23፤ መዝ 33፥7፤ 88፥6፤ 90፥11፤ 1ነገ 19፥5፤ 2ነገ 6፥15፤ ዳን 3፥17፤ 4፥13፤ 8፥15-19፤ ዘካ 1፥12፤ ማቴ 18፥10፤ ሉቃ 1፥19፤ 13፥6-9፤ 15፥7፤ ዮሐ 20፥11፤ የሐዋ 12፥6፤ ዕብ 1፥14፤ ራእ 8፥3-4ን ይመልከቱ)።

ከመጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ

ከመጽሐፈ ሰዓታት ንባብና ትርጓሜው መጽሐፌ የተወሰደ

7/ ነገረ መላእክት (Angelology)

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!!!

ትርጉም

ጥሬ ቃሉን ስንመለከተው መልአክ የሚለው የግእዝ ቃል ኹለት ትርጉሞች አሉት።አንደኛው አለቃ፣ ሹም ማለት ነው። በዮሐንስ ራዕይ ላይ የምናገኛው ሰባቱ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች መላእክት ተብለው መጠራታቸውምከዚኽ አንጻር ነው /ራዕ. 2 እና 3/። ኹለተኛውና ከተነሣንበት ርእስ አንጻር ስናየው ደግሞ መልክእተኛ፣ የተሰደደ፣ የተላከየሚል ትርጉም አለው /ዕብ.1፥14/። ይኸውም የመላእክት ተግባር ምን እንደኾነ የሚያስረዳ ቃል ነው። መላእክት ከእግዚአብሔርወደ ሰው፥

ከሰውም ወደ እግዚአብሔር የሚላላኩ መናፍስት ናቸውና። መላእክት በሌላ ስማቸው የሰማይ ሠራዊት ተብለው ይጠራሉ።

መላእክትስንት ወገን ናቸው?

መላእክት ዥስት ወገን ናቸው። ብርሃናውያን መላእክትና የጨለማ አበጋዝ የኾነው የዲያብሎስ ሠራዊት የኾኑት እኩያን መላእክት። ስለዚኽ የእግዚአብሔርን መላእክት ከሌሎቹ መላእክት በአጠራር የምንለያቸው ቅዱስ በሚል ቅጽል ነው።

መላእክት መቼ ተፈጠሩ?

መላእክት የተፈጠሩት በመዠመሪያው ቀን ነው/ኩፋ.2፡7-8/። መዝሙረኛው ክቡር ዳዊትም ይኽን በማስመልከት፡- “በእግዚአብሔር ቃል ሰማያት ተፈጠሩ፤ የሰማይ ሠራዊትም ዥሉበአፉ እስትንፋስ” ይላል /መዝ.32፡6/።

ምንም እንኳን በመዠመሪያው ቀን የተፈጠሩ ቢኾኑም ግን ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋናከሰባቱ ሰማያት በኋላ በ9ኛው ሰዓተ ሌሊት ነው የተፈጠሩት። ይኽ ለምን እንደኾነ ቅዱስ ኤጲፋንዮስ አክሲማሮስ በተባለ መጽሐፉላይ፡- “በፊት ፈጥሯቸው ቢኾን እኛም አብረነው ፈጠርን፤ ያዘንለት፤ ተራዳነው ባሉ ነበር። አንድም ርሱ ቢመሠርት እኛ ገነባን፤ርሱ ቢገነባ እኛ መሠረትን ባሉ ነበር። ይኽም ሳጥናኤል በኋላ እኔ ፈጠርኳችኁ እንዳለው ማለት ነው” በማለት ያብራሯል /አክሲማሮስዘእሑድ፣ ገጽ 24 / ።

አንዳንድ ሊቃውንት መላእክት ከሰው በፊት ስለተፈጠሩ የሰው ታላላቅ ወንድሞችናቸው ይሏቸዋል።

ተፈጥሮአቸውም ካለ መኖር ወደ መኖር ነው። መላዕክት እንደ እሳት የሚሞቁ፣እንደ ነፋስ የሚረቁ ስለ ኾነ /ዝኒ ከማኑ/ አንድም እንደ እሳት እንደ ነፋስ ፈጣኖችና የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈጽሙ ኃያላንስለኾነ ባሕርያቸውን ለመግለጥ ከነፋስና ከእሳት ተፈጠሩ ይባላሉ /መዝ.103፡4፣ መዝሙረ ዳዊት ንባቡ ከነትርጓሜው፣ ገጽ 489/።

የመላእክት አሰፋፈራቸው እንዴት ነው?

የመላእክት ቁጥራቸውከእግዚአብሔር በቀር ማንም አያውቀውም /ዳን.7፡ 10/። በነገድ በነገድ ስናያቸው ግን ቅዱስ ኤጲፋንዮስ እንደሚነግረን 100 ነገዶችናቸው። እያንዳንዱ ዐሥር ዐሥር ነገድ የሚይዙ ሲኾኑ ቅደም ተከተላቸውም ይኸው ነው፡- አጋዕዝት /አለቃቸው ሳጥናኤል (ሰማልያል)የአኹኑ ዲያብሎስ ነው/፣ ኪሩቤል /አለቃቸው ኪሩብ ነው፤ አራት ራስ አራት ገጽ አላቸው። ገጻቸውም ገጸ ሰብእ ገጸ አንበሳ ይመስላል።ሰውነታቸው ኹሉ በዓይን የተሸለመ ሲኾን ዓይናቸውም እንደ ነብር ቆዳ ዝንጕርጕር ነው /ሕዝ.1፡6-7፣ 18-19/። አገልግሎታቸውበቀሳውስት አምሳል የሥላሴን ዙፋን መሸከም ነው/፣ ሱራፌል /አለቃቸው ሱራፊ ነው፤ በዲያቆናት አምሳል ለጸሎት የሚተጉና የሚያተጉየምስጋና መላዕክት ናቸው። ገጻቸው ገጽ ንስር ገጸ እንስሳ ይመስላል። ስድስት ስድስት ክንፍ አላቸው ኢሳ.6፡2-3/፣ ኃይላት/አለቃቸው ቅዱስ ሚካኤል ነው /ሄኖክ.10፡2-10/። የሥላሴ ሰይፍ ጃግሬዎች ናቸው/፣ አርባብ /አለቃቸው ቅዱስ ገብርኤል ነው። በሥላሴ ፊት በአጋፋሪ በአስተናጋጅ አምሳል የሚቆሙ ናቸው ሄኖክ 10፡ 7-8፣ ሉቃ.1፡19/፣ መናብርት /አለቃቸው ቅዱስ ሩፋኤልነው። በጋሻ

ጀግሬ አምሳል ያገለግላሉ። የመብረቅ ጋሻ የእሳት ጦር ይዘው ዘለዓለም እንደ ነፋስ ሲበሩ ይኖራሉ/፣ ሥልጣናት/አለቃቸው ቅዱስ ሱርያል ነው። የሥላሴ አዋጅ ነጋሪዎችና መላዕክትን በየጊዜው ለጸሎትና ለምስጋና የሚያተጉ ናቸው/፣ መኳንንት/አለቃቸው ሰዳካኤል ይባላል። የሥላሴ ቀስተኞች ናቸው። ተራራ የሚንድ፣ ድንጋይ የሚሰነጥቅ፣ የእሳት ፍላፃ የእሳት ቀስት ይዘውሰውን ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ ሲጠብቁ ይኖራሉ። በትንሣኤ ዘጉባኤ ጊዜ የሰውን ኹሉ አጥንት ሰብስበው ለትንሣኤ የሚያበቁ እንዚኽናቸው ማቴ.24፡31-42/፣ ሊቃናት /አለቃቸው ሰላታኤል ይባላል። የሥላሴ ፈረስ ባልደራስ ናቸው። የእንስሳት ጠባቂ መላዕክትናቸው/፣ መላዕክት /አለቃቸው አናንኤል ይባላል። እንደ ብረት የጸና የእሳት ነጐድጓድን ወደ ምድር የሚወነጭፉ፣ ፀሐይን ጨረቃንከዋክብትን አዝርዕትን አትክልትን ዕፅዋትን ከምድር በላይ ከሰማይ በታች የተፈጠሩትን የሚጠብቁ ናቸው ኩፋሌ 2፡6-8/።

እነዚኽ ቅዱሳን መላእክት የሚኖሩባቸው ቦታዎች ሦስት ሲኾኑ ኢዮር ራማእና ኤረር ይባላሉ። የመዝመሪያዎቹ 40 ነገድ በኢዮር፣ ቀጣዮቹ 30 በራማ፣ የመጨረሻዎቹ 30 ም በኤረር የሰፈሩ ናቸው።

ዲያብሎስ በትዕቢቱ ከተዋረደ በኋላ ግን የነገደ መላእክቱ ቁጥር ከ 100 ወደ 99 የአለቆች ቁጥርም ከ 10 ወደ 9 ተቀንሷል።

እነዚኽመላዕክት ለተልዕኮ ፈጣሪ ካላዘዛቸው በቀር ከስፍራቸው አይለቁም። ሲያዛቸው ግን ወደ ላይ እስከ ጽርሐ አርያም ወደ ታች እስከበርባሮስ ድረስ ከብርሃን ፍጥነት በላይ በኾነ ቅጽበት ይወጣሉ፤ ይወርዳሉ።

የመላእክትባሕርይ እንዴት ነው?

የመላእክት ባሕርይ ከሰው ጋር የሚያመሳስለውምየሚያለያየውም ነጥብ አለው። ከሰው በምን ይለያሉ ቢሉ መላእክት፦

· ረቂቃን ናቸው። ከነፋስ ነፍስ ትረቃለች፤ ከነፍስ መላእክት ይረቃሉ፤ ከመላእክትደግሞ ሥላሴ ይረቃሉ።

· እንደ ሰው አይራቡም፤ አይጠሙም። ልብስ፣ መጠለያ አይፈልጉም። “እኔምተገለጥኩላችሁ፤ ነገር ግን እይታን አያችሁ እንጂ ከእናንተ ጋር አልበላኹም፤ አልጠጣኹምም” /ጦቢት 12፡19/።

· የመላዕክት ምግባቸው የእግዚአብሔር ምስጋና መጠጣቸውም የመለኮት ፍቅር ነው።

· መላዕክት ዕታ የላቸውም /ማቴ.22፡30-31/። በመኾኑም አይጋቡም፤ አይዋለዱም።

· ስለ ነገ አይጨነቁም።

· መላዕክት ከዝንጋዔ የራቁ፣ ባለ አዕምሮ የኾኑ፣ ዕውቀት ያላቸው፣ ይዋኔንናትዕግሥትን ገንዘብ ያደረጉ፣ ለዘለዓለም የማይነጥፍና የማያቋርጥ ይልቁንም ዘወትር እንደ ዥረት ውኃ የሚወርድ ምስጋና ያላቸው ናቸው/ሥነ ፍጥረት፣ በቀሲስ ስንታየኁና በዲ/ን ብርሃኑ አድማስ የተዘጋጀ፣ ገጽ 34/።

· ምንም እንኳን ከሰው በፊት ቢፈጠሩም አያረጁም። ዘወትር ውቦች፣ ብርቱዎችናውርዙዋን ናቸው።

· ኢ-መዋትያን ናቸው (አይሞቱም) /ሉቃ.20፡36/። ይኸውም ልክ እንደእኛ ነፍስ በእግዚአብሔር ፈቃድ የተደረገ ነው።

· እንደ ሰው አንድ ጊዜ ደግ ሌላ ጊዜ ክፉ በመሥራት አይዋልሉም።

ከሰው ምን ያመሳስላቸዋል ስንል ደግሞ፦

Ü ምንምረቂቃን ቢኾኑም ሕልውና ከአካል ጋር አላቸው። ዮሐንስ ዘደማስቆ የተባለ አባት ይኽን ሲያብራራው፦ “መላእክት ረቂቃን ናቸው የምንላቸውከእኛ አንጻር ነው። ከማንም ጋር ከማይነጻተረው ከእግዚአብሔር አንጻር ሲታዩ ግን ግዙፋን ናቸው። ፍጹም ረቂቅ እግዚአብሔር ብቻነውና” ብሏል።

Ü ምንምረቂቃን ቢኾኑም ውሱናን ናቸው። እንደ ሰው በቦታ የሚገቱ ባይኾኑም መጠን አላቸው። መጠናቸውና አርዐያቸውም የተለያየ ነው። ቁመታቸው ከምድር እስከ ሰማይ የሚደርስ መላዕክት አሉ። በክንፋቸው ብቻ አንድ አገር የሚያለብሱ መላዕክት አሉ። ራሳቸው ብቻተራራ የሚያክሉ መላዕክት አሉ። በዓይን የተቀረፁ የተሸለሙ ኹለንተናቸው ዓይን የኾነ መላዕክት አሉ። ስድስት ክንፍ ያላቸው መላዕክትአሉ። መብረቅ ለብሰው መብረቅ ተጐናጽፈው የሚኖሩ መላዕክት አሉ። ነፋስ ለብሰው ነፋስ ተጐናጽፈው የሚኖሩ መላዕክት አሉ። ብሩህደመና ጠምጥመው የሚኖሩ መላዕክት አሉ። እግራቸው ዓምደ እሳት የሚመስል መላዕክት አሉ። የእነዚኽን መላዕክት አርዓያቸውን መጠናቸውንከእግዚአብሔር በቀር የሚያውቀው የለም /ኩፋ.2፡7-8/።

Ü ዐዋቂዎችናቸው። ዕውቀታቸው ግን ሐዋርያው ጴጥሮስ እንደተናገረው ከሰው እጅግ ከፍ ያለ ነው /2ኛ ጴጥ.2፡11/። ምንም ከሰው እጅግከፍ ያለ ቢኾንም ግን ዕውቀታቸው መጠን አለው። ከእግዚአብሔርን በቀር ፍጹም ዕውቀት ያለው የለምና። እኛ ዕውቀታችንእንደ መላእክት የሚኾነው ከትንሣኤ ዘጕባኤ በኋላ ነው /1ኛ ቆሮ.13፡12/።

Ü ነጻ ፈቃድአላቸው።

Ü እንደሰው ባሕርያቸውን የሚገልጽ ስም አላቸው።

ሰው ከመበደሉ በፊት ልክ እንደ መላእክት ንጹሕ፣ ውብና ብርቱ ነበር። በፍጥረታትላይ ሥልጣን ነበረው። ርሱ ሲበድል ግን ከሥልጣን የወረደ ሰው እንደ ድሮ የሚያከብረው እንደሌለ ኹሉ ፍጥረታቱ አዳምን አልታዘዝአሉት። እንደዉም ተበረታቱበት። ክብር ይግባውና ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣውም ወደ ቀድሞ ክብራችን ወደ ልጅነትወደ ቀድሞ ቦታችን ወደ ገነት ከዚያም በላይ ወደ መንግሥተ ሰማያት ሊመልሰን ነው። በመኾኑም ሰው ምንም እንኳን በዚኽ ዓለም ሳለብዙ ውጣ ውረዶችን ቢያሳልፍም በመጨረሻ መላእክትን ይመስላል። ለዚኽም ነው ቅዱሳን መላእክት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በዕብ.1፡14 ላይ እንደገለጸው ታናሽ ወንድማቸውን ሰውን በማገልገል ላይ ያሉት።

የመላእክትትክክለኛ ስም ይታወቃልን?

ምንም እንኳን በስም በስም ብንጠራቸውም ስማቸውንገረ እግዚአብሔርን የሚያስረዳ እንደኾነ እንጂ በቅጥነተ ኅሊና ስናስተውለው ማን ማን እንደሚባሉ አይታወቁም፤ ስም የሌላቸው ኾኖሳይኾን የሰው አዕምሮ ሊረዳው አይችልም። ለምሳሌ ገብርኤል ማለት አምላክ ወሰብእ ማለት ነው። ይኽም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስማንነትን የሚገልጽ እንጂ የመልአኩ ትክክለኛ ስም አይደለም። ሚካኤል ማለት መኑ ከመ እግዚአብሔር ማለት እንጂ የመልአኩ ስም አይደለም።በነገራችን ላይ የእግዚአብሔር ትክክለኛ ስሙም አይታወቅም፤ የለውም ማለት ሳይኾን ኹለንተናውን የሚገልጽ ስም በሰው ቋንቋ መግለጽአይቻልም።

መላእክትመልክ አላቸውን?

በመጽሐፍ ቅዱስ ቅዱሳን መላእክት በተለያየ መልክ እንደተገለጹ እናነባለን።ለምሳሌ፦

V በእሳትአምሳል /ዘጸ.3፡2-4/፤ ለሙሴ፤

V በዓምደብርሃንና ደመና አምሳል /ዘጸ.13፡21፣ 23፡20-21፣ ዘኁ.20፡16/፤ ለሕዝበ እስራኤል፤

V በተራሰው አምሳል /መሳ.6፡12-23/፤ ለጌድዮንና ለጦቢት፤

V በነቢይአምሳል /መሳ.13፡6/፤ ለማኑሄ ሚስት፤

V በእሳትፈረስና ሰረገላ አምሳል /2 ኛ ነገ.6፡16-17/፤ ለኤልሳዕ ሎሌ፤

V በእሳትአምሳል /ሕዝ.8፡2/፤ ለነቢዩ ሕዝቅኤል፤

V በፍታእንደ ለበሰ፣ ወገቡም በወርቅ እንደታጠቀ ሰው /ዳን.10፡5/፤ ለነቢዩ ዳንኤል፤

V ልክ እንደትሑት ሰው /ሉቃ.1፡12-13/፤ ለዘካርያስና ለእመቤታችን፤

V የጌታክብር በዙርያቸው ኾኖ /ሉቃ.29-30/፤ ለእረኞች፤

ይኽም ማለት መላእክቱ ሰው እንዲገባው በሰው አእምሮ መጠን ተገለጡ ማለት እንጂመልካቸው ተለዋዋጭ ነው፤ የራሳቸው የኾነ ቋሚ መልክም የላቸውም ማለት አይደለም።

የመላእክትተግባር ምንድነው?

የመላእክት ተግባር እንደሚከተለው ማየት ይቻላል፦

Ø ያለማቋረጥእግዚአብሔርን “ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ” እያሉ ያመሰግናሉ /ኢሳ.6/፤

Ø የእግዚአብሔርንመልካም ዜና ወደ ሰው ያመጣሉ። ይኸውም ለአጋር፣ ለአብርሃም፣ ለሐና እመ ሳሙኤል፣ ለካህኑ ዘካርያስ ለእመቤታችን

እንዳመጡላቸውማለት ነው።

Ø ማስተዋልንናጥበብን ለሰው ልጆች ያድላሉ። ይኸውም ቅዱስ ገብርኤል ለነቢዩ ዳንኤል፣ ቅዱስ ዑራኤልም ለዕዝራ እንዳደረጉት ማለት ነው።

Ø ሰውንከጥፋት ያድናሉ። ይኸውም ሎጥን ከሰዶምና ገመራ ሰዎች ጋር እንዳይጠፋ /ዘፍ.19/፣ ሠለስቱ ደቂቅን ከሚነድ እሳት እንዳዳኗቸውማለት ነው /ዳን.3፡12-30/። መዝሙረኛው ክቡር ዳዊት፡- “የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙርያ ይሰፍራልና ያድናቸውማል”/መዝ.34፡7/፤ በሌላ ቦታም “ክፉ ነገር ወደ አንተ አይቀርብም መቅሰፍትም ወደ ቤትህ አይገባም። በመንገድህ ኹሉ ይጠብቁህ ዘንድመላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና። እግርህም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሱኻል” ያለውም ስለዚኹ ነው /መዝ.91፡10-12/።

Ø የሰውንም መልእክት ወደ እግዚአብሔር ያደርሳሉ። የሰውን መልእክትወደ እግዚአብሔር ያደርሳሉ ሲባል ምን ማለት እንደኾነ የቆጵረሱ ሊቀ ጳጳስ ሊቁ ኤጲፋንዮስ በአክሲማሮስ መጽሐፉ ላይ፡-“ (የካህናተሰማይ ማዕጠንት) የጻድቃን ጸሎትን፤ የሰማዕታት ገድልን፤ የደጋግ ሰዎች ምግባር ነው” ብሎ ያብራሯል /መጽሐፈ አክሲማሮስ፣ ገጽ 51/።

Ø የእግዚአብሔርንቁጣ ወደ ሰዎች ያመጣሉ። እነርሱም የመዓት መላእክት የሚባሉ ሲኾኑ በትዕቢቱና በክፋቱ ከሥልጣኑ የወረደው የዲያብሎስ ሠራዊት የነበሩናበኋላ ግን አለቃቸው ሲክድ ያልካዱ በእምነታቸው የፀኑ ከሣጥናኤል ሠራዊትነት ተለይተው ከነቅዱስ ሚካኤልና ከነቅዱስ ገብርኤል ጋርየተደመሩት ናቸው። እነዚኽ የመዓት መላእክት እጅግ ቁጡዎችና ቀናተኞች ናቸው።

ጠባቂመልአክ

ክቡር ዳዊት “ክፉ ነገር ወደ አንተ አይቀርብም መቅሰፍትም ወደ ቤትህ አይገባም።በመንገድህ ኹሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና። እግርህም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሱኻል” እንዳለው/መዝ.91፡10-12/ እያንዳንዱ ሰው ጠባቂ መላእክት እንዳሉት ያስረዳል። እስራኤል ዘሥጋን የጠበቃቸው መልአክ ቅዱስ ሚካኤልነው። ይኽንንም ለኢያሱ በኢያሪኮ አጠገብ ነግሮታል /ኢያ.5፡ 14-15/። ይሁዳም የመልአኩ ስም ማን እንደኾነ በግልጽ ነግሮናል/ይሁዳ ቁ.9/።

አስቀድመን እንደተመለከትነው ለእያንዳንዱ ሰው ብቻ ሳይኾን ለእንስሳት፣ ለዕፅዋት፣ለምድር፣ ለፀሐይ፣ ለጨረቃ፣ ለከዋክብት፣ ከምድርም በታች ለተፈጠሩ ፍጥረታት በሙሉ ጠባቂ መላእክት አሏቸው። ለምሳሌ እንስሳትንየሚጠብቀው መልአክ ሰላታኤል ይባላል። አናንኤል የሚባለው ነገደ መላእክት ደግሞ እንደ ብረት የጸና የእሳት ነጐድጓድን ወደ ምድርየሚወነጭፉ፣ ፀሐይን ጨረቃን ከዋክብትን አዝርዕትን አትክልትን ዕፅዋትን ከምድር በላይ ከሰማይ በታች የተፈጠሩትን የሚጠብቁ ናቸው/ኩፋሌ 2፡6-8/።

ቅዱስ ባሲልዮስ ዘቂሳርያ ሰውን ስለሚጠብቁ መላእክት ሲናገር፡- “ክፉ ሥራካልሠራን በቀር ጠባቂ መልአካችን ከእኛ አይለይም። ጭስ ንብን ከቀፎው እንዲወጣ እንደሚያደርገው ኹሉ የእኛ ኃጢአትም ጠባቂ መልአካችንከእኛ እንዲለይ ያደርጓል” ብሏል።

መላእክት- የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ናቸው!!!

ቅዱሳን መላእክት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ናቸው። ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስብልት ናትና መላእክትም ቤተ ክርስቲያንን ያገለግላሉ። የጌታችንን ሰው መኾን ያበሰሩን መላእክት ናቸው። በቤተ ልሔም ግርግምሲወለድ እጅግ ደስ ብሏቸው ያመሰገኑት መላእክት ናቸው። ስለ ልደቱ ለእረኞች የነገሯቸው መላእክት ናቸው። ወደ ግብጽ ሲሰደድአብረዉት የሔዱ መላእክት ናቸው። በፈለገ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ ተጠምቆ ወደ ገዳመ ቆሮንቶስ በሔደ ጊዜ ያገለገሉት መላእክትናቸው። ጌታችን በጌቴሴማኒ የአታክልት ስፍራ ሲጸልይ ሲያበረቱት የነበሩት መላእክት ናቸው። አይሁድ ሊሰቅሉት ሲሉ ቸርነቱ ከልክሏቸውእንጂ አይሁድን ለማጥፋት የተዘጋጁት መላእክት ናቸው። ደሙን ወደ ዓለም ኹሉ የረጨት መላእክት ናቸው። ትንሣኤውን ያበሠሩን መላእክትናቸው። ሲያርግ ደግሞም ዳግም እንደሚመጣ የነገሩን እነዚኽ መላእክት ናቸው። ዳግም ሲመጣ አብረዉት የሚመጡትና ሙታንን የሚቀሰቅሱትምእነዚኽ ቅዱሳን መላእክት ናቸው።

ይኽ አገልግሎታቸው በሐዋርያትም የተመለከትነው ነው። ሊቀ ካህኑ ሐዋርያቱንሲያስራቸው ሰንሰለታቸውን የፈቱላቸው መላእክት ናቸው /ሐዋ.5፡17-20፣ 12፡7-10/። የገሊላው ንጉሥ ይሁዳ ሐዋርያው ያዕቆብንከገደለው በኋላ ጴጥሮስንም ሊገድለው ሲል በትል ተበልቶ እንዲሞት ያደረጉት መላእክት ናቸው /ሐዋ.12፡23/። ፊሊጶስ በሰማርያእያስተማረ ሳለ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባን አስተምሮ እንዲያጠምቀው የነገሩት ቅዱሳን መላእክት ናቸው /ሐዋ.8፡26/። ሐዋርያትንእየመሩ፣ አሕዛብንም እያዘጋጁ ወንጌል በአሕዛብ አገር እንዲስፋፉ ያደረጉት ቅዱሳን መላእክት ናቸው /ሐዋ.10/። እነ ቅዱስ

ጳውሎስመርከብ በአውሎ ነፋስ ቀንና ሌሊት ስትናወጥ አንዲት ነፍስ እንኳን እንደማትጠፋ ያጽናኗቸው ቅዱሳን መላእክት ናቸው /ሐዋ.27፡20-25/።በአጠቃላይ ቅዱሳን መላእክት ከክርስቶስ ደግሞም ብልቱ ከምትኾን ከቤተ ክርስቲያን (ይኸውም ከእኛ ከምእመናን) አይለዩም። ክብርይግባውና ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውን እጅግ አድርጐ ይወዳል። እነዚኽ ቅዱሳን መላእክትንም ጠባቂ አድርጐ ይልክላቸዋል፤ይልክልናል።

በሥራችን ኹሉ ለሚጠብቁን፣ ዘወትር በኃጢአት ስንወድቅ ደግፈው ለሚያነሡን፣በኃጢአት ስንጨማለቅ “ለዛሬ ተዋት” እያሉ ስለ እኛ መዳን ፈጣሪን ለሚማልዱልን /ሉቃ.13፡7-9/፣ በእኛ ንስሐ መግባት ስለ እኛበሰማያት ድል ያለ ምስጋና ለሚያቀርቡ /ሉቃ.15፡7/፣ እንቅፋት እንዳይመታን ለሚጠብቁን፣ በርኩሳን መናፍስት አንድም በፈቃደ ሥጋችንላይ እንድንሠለጥን ለሚራዱን ለእነዚኽ ቅዱሳን መላእክት ውለታ ታድያ እንዴት መክፈል ይቻለናል? እነዚኽን ጠበቃዊቻችን ለሰጠን እግዚአብሔርስተመስገን ከማለት በቀር ምን ማለት እንችላለን?

በረከትና ክብር ጥበብም ምስጋናም ውዳሴም ኃይልምብርታትም ለዘለዓለም እስከ ዘለዓለም ድረስ ለአምላካችን ይኹን አሜን /ራዕ.7፡12/።

December 27, 2014 at 1:59p

Miko ZE Ethiopia

8/ የእግዚአብሔር መልአክ ሃያሉ ቅዱስ ገብርዔል

እግዚአብሔርን የሚያመለኩና የሚገዙ እንዲሁም ለእርሱ ክብርን በመስጠት ያሉ ሁሉ

ከነገር እንኳን አንዳች እንደማይጎድላቸው በዘመናት መካከል ተመልክተናል። ይህም

ደግሞ እውነት ነው። ደግሞም እግዚአብሔር ለሚወዱትየሚሆን ጠባቂ በዙሪያቸው

ያቆማል።

እስራኤልላውያን በምርኮ ወደ ባቢሎን ምድር ወረዱ በዚያም በግዞት ኑሮዋቸውን ሲገፉ

ሰነበቱ። የባቢሎንም ምድር ንጉስ የነበረው ናቡ ከደነጸር ቁመቱ ስድሳ ክንድ ወርዱም

ስድሳ ክንደ የሆነ ጣዖትን አሰርቶ ዱራ በሚባል ሜዳ ላይ አስቆመው በዚያም አንድ

ትህዛዝን አዘዘ በእርሱ ግዛት ስር የሚተዳደሩትን በሙሉ እንደዚህ አላቸው የመለከት

ድምጽ በሰማችሁ ጊዜ ለዚህ እኔ ላቆምኩት ምስል ስገዱ የማይሰግድ ግን በዚህ

በሚነደው እቶን እሳት ስር ይጣላል አለ።

እንደተባለውም የመለከቱ ድምጽ በተሰማ ጊዜ ሁሉም በግባሩ ተደፍቶ ለቆመው ምስል

ሰገደ። ነገር ግን ከሕዝቡ ምካከል ዎስች ሳይሰግዱ ዝም ብለው ቆሙ።

አስተናባሪዎቹ

ግን እንዲሰግዱ ለመኑዋቸው ልጆቹ ግን እንቢ አሏዋቸው። ይህን ባለማድረጋቸው ወደ

ሚነደውና ድምጽም ወደሚያስፈራ እሳት ያማላከቷዋቸው ነገር ግን ጸንተው ቆሙ ልጆቹ

‹‹አምላኩን የሚያውቅ ሕዝብ ይቃወሙታል›› ይላል መጽሐፍ ቅዱስ።

በመሆኑም ልጆቹ ይህን በጽናት ተቃወሙት። አንሰግድም ብለውም በጽናጽ ቆሙ።

‹‹የምናመልከው አምላክ ከዚህ ከሚነደው እሳት ያድነናል ባያድነን እንኳን አንተ

ላቆምከው ምስል አንሰግድም›› አሉት።

ይህ ዓይነት ነገር ታላቅ እምነት ነው በዚህም ደግሞ ወንጌልን በኦሪት ያስተምሩናል።

ይህም ማለት ‹‹ሳያዩ የሚያምኑ ብጹአን ናቸው›› እነዚህም ልጆች ሳያዩ አመኑ ድግሞም

ቁርጥ ያለ መለስ መለሱ። በቅዱሱ አምላክ መታመን ማለት የእርሱን ጥበቃ የሚሆነውን

ታላቅ ድህነት እናገኛለን ማለት ነው። ቅዱስ ዳዊት እንዲህ ይላል ‹‹የእግዚአብሔር

መላክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል ያድናቸውማል›› መዝ.33፡7። ይህም በመሆኑ

ታዳጊው አምላክ እነርሱን ለመታደግ ሲል መላዕክትን ይልካል።

በዚህም ሁኔታ ንጉሱ ናቡ ከደነጸር በቁጣ እንዲህ አለ ወደ እሳቱ ጨምሩዋቸው አለ።

ወስደውም ወደ እሳቱ ጨመሩዋቸው ነገር ግን በዚህ መሀላል አንድ ትልቅ ነገር ተከሰተ

ከሚጣሉት ሶስቱ ልጆች ጋራ ቀድሙ የተገኘው አራተኛው እግዚአብሔር መልአክ ነበር።

እሳቱም መካከል በዝማሬ ተሞሉ። በዚያም የነበሩት ሁሉ በሆነው ነገር ተገረሙ። ንጉሱም

እንዲህ አለ ‹‹እኔ የተፈቱ በእሳቱ ውስጥ የሚመላለሱ አራት ሰዎች አያለው ›› አለ

አራተኛውንም ሲገልጸው ‹‹የአምላክን መልክ ይመስላል›› አለ።

ከሊቃነ መላእክት መካከል አንዱ የሆነው ቅዱስ ገብረኤል በገነት አበቦች መካከል

የተሾመው የአምላክ ባለሙዋል ነበር መ.ሔኖክ 10፡14። ከእሳቱ ውስጥ የነበርው።

ለአምላካቸው የሚታመኑትን የሚረዱና የሚያገለግሉ የአምላካችን የእግዚአብሔር

አገልጋዮች ቅዱሳን መላእክት ሁሌም ቢሆን እኛን ለመርዳት ይፈጥናሉ። በመሆኑም

መላእክት ፈጣንና ሰውን ለመታደግ የሚተጉ ናቸው። ‹‹ቅዱሳን መላእክት አፈጣጠራቸው

እም ኀበ አልቦ ኀበ ቦ (ካለመኖር ወደ መኖር) አምጥቶ ነው፡ ነገር ግን

በግበራቸው

በእሳትና በነፋስ ተመስለዋል። ይህውም እሳት ረቂቅ ነው መላእክትም እንደዚሁ ረቂቃን

ናቸው፣ ነፋስ ፈጣን ነው እንደዚሁ መላእክት ፈጣን ናቸው ለተልእኮና እኛን ለመርዳት

ፈጣን ናቸው›› (አክሲማሮስ) መዝ. ‹‹መላእክቱን መንፈስ የሚያደርግ አገልጋዮቹን እሳት

ነበልባል›› ይላል በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ መላእክት ተፈጥሮ ሲነግረን እንዲሁም በአዲስ

ኪዳን ሐዋሪያው ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ እንዲህ ይለናል፦‹‹ሁሉ መዳንን ይወረሱ ዘንድ

ስላላቸው ላመገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም መናፍስት አይደሉምን ›› ዕብራውያን 1፣

14። አምላካችን ሁላችንንም ከዚህ ረድኤት በረከት ይክፈለን። ቅዱስ ገብርኤል

ሁላችንንም ይጠብቀን።

Miko ZE Ethiopia

9/ የሰው ልጅ በገነት እንደ ቅዱሳን መላእክት በቅድስና አምላኩን በማመስገን በደስታ ይኖር ነበር። ነገር ግን “ክፉና ደጉን ከምታሳውቀው ዕፀ

በለስ እንዳትበላ" ተብሎ የተሰጠውን ትእዛዝ በመተላለፉ ምክንያት ከአምላኩ ተለየ(ዘፍ.3፡6)።እግዚአብሔር በአርአያውና በአምሳሉ የፈጠረው ሰው ክብሩን አጣ፣ ጸጋው ተገፈፈ፣ ፈጣሪውንም አሳዘነ። ቅዱሳን መላእክትም በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ የተፈጠረው ሰው ከክብሩ ተዋርዶ ሲመለከቱ ተከዙ።

የሰው ልጅ ጠፍቶ እንዲቀር ያልወደደው እግዚአብሔር ወልድ ሰውን ለማዳን ራሱን ዝቅ አድርጎ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሱዋ ነፍስ ነስቶ ተወለደ።ቅዱሳን መላእክትም ከላይ ከአርያም ከአባቱ ሳይለይ እግዚአብሔር ወልድ ሰውን ለማዳን ሲል በግዕዘ ሕፃናት ተወልዶ፣ በእናቱም እቅፍ ሆኖ፤ እንስሳት እስትንፋሳቸውን እያሟሟቁት በማየታቸው ተደነቁ። ሰውን ለማዳን ሲል ራሱን ዝቅ በማድረግ የባርያውን አርአያ እንደነሣ አስተውለው "ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት፣ ወሰላም በምድር ሥምረቱ ለሰብእ" (ሉቃ.2፡14) ብለው አመሰገኑት።

ጌታችንም በመስቀሉ የማዳን ሥራውን ሲፈጽም ተጎሳቁሎ የነበረውን የሰው ባሕርይ ወደ ቀድሞ ክብሩ መለሰው። ስለዚህም እንደ ቅዱሳን መላእክት አምላኩን ለማመስገን እድሉን አገኘ። (ዮሐ.4፡23) ነገር ግን ከእነርሱ ጋር በመሆን ሙሉ ለሙሉ በምስጋና የሚሳተፈው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ሙታንስ በሚነሡበት ጊዜ በሰማያት እንደ እግዚአብሔር መልአክት ሆነው ይኖራሉ....." (ማቴ.22፡30) እንዳለው በትንሣኤ ዘጉባኤ ነው። እስከዚያ ድረስ ግን በዚህ ምድር ሳለን ከእኛ የሚጠበቅብንን ፣ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቃል

ያስተማረንን፣ በሥራም ያሳየንን ተግባር ተግብረን፣ እንደ ቅዱሳን መላእክት ለአምላካችን በመንፈስና በእውነት በመሆን አምልኮታችንን እንድንፈጽም የእነርሱ ተራዳኢነት በእጅጉ ያስፈልገናል። ስለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ “መላእክት ሁሉ መናፍስት አይደሉም? የዘለዓለም ሕይወትን ይወርሱ ዘንድ ስለ አላቸው ሰዎችስ ለአገልግሎት ይላኩ የለምን?” (ዕብ.1፡14) ማለቱ። “የዘለዓለም ሕይወትን ይወርሱ ዘንድ” የተባልነው ጌታችን መድኅኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌሉ “እነርሱ በእውነት ቅዱሳን ይሆኑ ዘንድ ስለእነርሱ ራሴን እቀድሳለሁ። የምለምንህም ስለ እነዚህ ብቻ አይደለም፤ በቃላቸው ስለሚያምኑብኝ ሁሉ ነው እንጂ” (ዮሐ.17፡19-20)እንዳለው በክርስቶስ አምነን ለተጠመቅነው ክርስቲያኖች ነው።

mikeale እናት ልጁዋን እንድትንከባከብና እንድታገለግል ሁሉ ቅዱሳን መላእክትም የዘለዓለም ሕይወትን እንድንወርስ ይራዱናል። (ሉቃ.13፡6-9) ያለ እነርሱ እርዳታና ድጋፍ በቅድስና ሕይወት አድገን የመንግሥቱ ወራሾች መሆን አይቻለንም። እንዲህም በመሆኑ በመንፈስ ቅዱስ የልጅነት ጸጋን ከማግኘታችን በተጨማሪ ቅዱሳን መላእክት እኛን ይራዱን ዘንድ ጠባቂ ተደርገው ተሰጥተውናል። (ማቴ.18፡10)

ቅዱስ ጳውሎስ “እናንተ ግን የሕያው እግዚአብሔር ከተማ ወደምትሆን ወደ ጽዮን ተራራ በሰማያት ወደ አለችው ኢየሩሳሌም ደስ ብሎአቸው ወደሚኖሩ አእላፍ መላእክትም ደርሳችኋል” (ዕብ.12፡22) በማለት እንደተናገረው በክርስቶስ የማዳን ሥራ ከቅዱሳን መላእክት ጋር አንድ ቤተሰብ መሆንን አግኝተናል። ስለዚህም ጉዞአችንን ጨርሰን ገድላችንን ፈጸመን ለክብር እንድንበቃ ይራዱናል። በመሆኑም የእኛ ሕይወት

በኃጢአት ውስጥ መገኘት ሲያሳዝናቸው፣ በንስሐ ወደ አባታችን መመለሳችን ደግሞ በእጅጉ ያስደስታቸዋል። (ሉቃ.15፡7) ስለዚህ ስለእኛ በቅድስና ሕይወት ይተጋሉ።ቅዱስ ጳውሎስ "ለራሱ ስለ ሆኑት፥ ይልቁንም ስለ ቤተ ሰዎቹ የማያስብ፥ ማንም ቢሆን ሃይማኖቱን የካደ፥ ከማያምንም ይልቅ የከፋ ነው" ይላል። (1 ጢሞ.5፡8) ስለዚህ እኛ የእነርሱ ቤተሰብ ሆነናልና ቤተሰባዊ ግዴታቸውን ለመወጣት ሲሉ፣ ደካማው ብርቱን እንዲረዳ ቅዱሳን መላእክትም እኛን ለመርዳት ይተጋሉ። ነገር ግን የእነርሱ እርዳታ ለእኛ የሚፈጸምልን ተራዳኢነታቸውንና ምክራቸውን የተቀበልን እንደሆን ብቻ ነው። ምክንያቱም እነርሱም እንደ አምላካቸው በእኛ ነጻ ፈቃድ ውስጥ ጣልቃ አይገቡምና። እንዲህም ስለሆነ የሎጥ ሚስት ምንም እንኳ በመልአኩ እጅ ብትያዝም ለመልአኩ ቃል ባለመታዘዙዋና ለመዳን ባለመፍቀዱዋ የጨው ሐውልት ሆና ቀርታለች (ዘፍ.19፡26)። በእርግጥ ቅዱስ ጳውሎስ “በመላእክት የተነገረው ቃል ጽኑ ከሆነ መተላለፍና አለመታዘዝ የጽድቅን ብድራት ከተቀበለ..” (ዕብ.2፡2) በማለት እንደገለጠልን እግዚአብሔር ለላከው መልአክ አለመታዘዝ ታላቅ የሆነ ቅጣትን ማምጣቱ የማይቀር ነው። ስለዚህም ቤተ ክርስቲያን ልጆቹዋ የመላእክትን ተራዳኢነት አውቀው እንዲጠቀሙና የመንግሥቱ ወራሾች ለመሆን እንዲበቁ ስትል ለቅዱሳን መላእክት የመታሰቢያ ቀን በመስጠት በእነርሱ የምናገኛቸውን እርዳታዎች እንዲታወሱ ታደርጋለች።

በዚህም መሠረት በህዳር ወር በዐሥራ ሁለተኛው ቀን ቤተ ክርስቲያናችን የታላቁ መልአክ የቅዱስ ሚካኤልን በዓለ ሲመት በታላቅ ድምቀት ታከብረዋለች። እንደ ቅዱሳን አባቶቻችን አስተምህሮ ህዳር 12 ቀን ታላቁ

መልአክ ቅዱስ ሚካኤል በኢዮር ባለችው በአራተኛይቷ ከተማ በሚኖሩት ኃይላት እና በአሥሩ ነገደ መላእክት ላይ አለቃ ሆኖ የተሾመበት ቀን ነው። እግዚአብሔር ሳጥናኤልን በትዕቢቱ ምክንያት ከሥልጣኑ ገፍፎ ወደ ምድር ሲጥለው ቅዱስ ሚካኤል በእርሱ ቦታ በዐሥሩ ከተማ በመቶውም ነገደ መላእክት ላይ ተሹሟል።(ይህን ሁለተኛውን ሹመት ያገኘው በሚያዚያ 2 እንደሆነ አክሲማሮስ በሚባለው የቤተክርስቲያናችን መጽሐፍ ላይ ሰፍሮ አናገኛለን።)

የቅዱስ ሚካኤል ሹመት በነገደ መላእክት ላይ ብቻ ግን አይደለም ፤ ነገር ግን የእግዚአብሔር ሕዝብ በሆኑት ላይም ጭምር ነው ። ይህም እንደሆነ እንድንረዳ በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ የተባለውን እስራኤል ዘሥጋን ሲራዳና ሲጠብቅ እንደነበረ ተጽፎልን እናገኛለን። ለምሳሌ መጽሐፍ ቅዱስ መልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ለኢያሱ በኢያሪኮ ምድረ በዳ እንደተገለጠለት “... ዐይኑን አንሥቶ ተመለከተ እነሆም የተመዘዘ ሰይፍ የያዘ ሰው በፊቱ ቆመ፤ ኢያሱም ወደ እርሱ ቀርቦ “ከእኛ ወገን ወይስ ከጠላቶቻችን ወገን ነህ? አለው። እርሱም “እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ሆኜ አሁንም ወደ አንተ መጥቼአለሁ” (ኢያ.5፡13) ይለናል።

st.mickeale

እግዚአብሔር አምላክ ሕዝበ እስራኤልን ከግብጽ ባርነት ነፃ ሲያወጣቸው ይመራቸው የነበረ መልአክ ቅዱስ ሚካኤል ነበር። ሹመቱ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይም በመሆኑ ስለ እነርሱ ዲያብሎስ ይዋጋው፣ በጸሎትም ይራዳቸው ነበር። ነገር ግን ኃጢአት ሠርተው ሲያገኛቸው ለእግዚአብሔር አድልቶ ኃጢአተኞችን ስለሚቀጣ እግዚአብሔር ሕዝቡን “በፊቱ ተጠንቀቁ

ቃሉንም አድምጡ ስሜም በእርሱ ስለሆነ ኃጢአት ብትሠሩ ይቅር አይልምና አታስመርሩት” (ዘጸ.23፡21)ብሎ አስጠንቅቋቸው ነበር። ይህም ቅዱስ ሚካኤል በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ መሾሙን ያስረዳናል። ነገር ግን ከላይ የተጠቀሱት ጥቅሶች ሕዝበ እስራኤልን ይራዳቸው የነበረው ቅዱስ ሚካኤል ስለመሆኑ አያረጋግጥም የሚል ካለ “መልአክ” የተባለው ቅዱስ ሚካኤል ስለመሆኑ ቅዱስ ገብርኤል ወደ ነቢዩ ዳንኤል በተላከ ጊዜ ገልጦልን እናገኛለን፡- ቅዱስ ገብርኤል በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ቅዱስ ሚካኤል ስለመሾሙ ሲመሰክር “በእውነት በመጽሐፍ የተጻፈውን እነግርሃለሁ፤ በዚህም ነገር ከአለቃችሁ ከሚካኤል በቀር የሚረዳኝ ማንም የለም”(ዳን.10፡21)ብሎአል። ስለዚህም ለኢያሱ የተገለጠውና እስራኤላውያንንም የመራው መልአክ ቅዱስ ሚካኤል መሆኑን እንረዳለን። የቅዱስ ሚካኤል አለቅነት በሐዲስ ኪዳንም አንደሚቀጥል ይህ ነቢይ በትንቢቱ “በዚያ ዘመን ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ ሚካኤል ይነሣል..” (ዳን.12፡1) በማለት ተናግሮለታል። ስለዚህም ቅዱስ ሚካኤል እኛን ከሰይጣን አሽክላና ወጥመድ ይጠብቀንና በጸሎቱ በእግዚአብሔር ፊት ይቆምልን ዘንድ በእኛም ላይ ሹም ነው። ምክንያቱም እኛ የእግዚአብሔር ሕዝቦችና የርስቱ ወራሾች ነንና።

እግዚአብሔር ነቢዩ ሙሴን የሕዝቡ መሪ አድርጎ መሾሙ እጅግ ትሑትና ስለመንጎቹ ነፍሱን እንኳ አሳልፎ እስከመስጠት ደርሶ ስለሚወዳቸው ነበር።(ዘኁል.12፡3፤ዘጸአ.32፡32) በሕዝቡም ላይ እርሱን መሾሙ እንዲሠለጥንባቸው ወይም እንዲገዛቸው ሳይሆን በትምህርቱና በጸሎቱ እነርሱን እንዲቤዣቸው ነው። እንዲህም ስለሆነ ቅዱስ እስጢፋኖስ

ስለሙሴ ሲመሰክር “እግዚአብሔር ሾምና ቤዛ አድርጎ ላከው”አለ። (የሐዋ.7፡35) እንዲሁ ቅዱስ ሚካኤል ነው። ቅዱስ ሚካኤል እጅግ ትሑትና ለሠራዊቱ ተቆርቋሪ የሆነ መልአክ በመሆኑ በመላእክትና በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ተሾመ። በመላእክትና በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ መሾሙ ልክ እንደ ሙሴ በእነርሱ ላይ ሊሠለጥንባቸው ወይም ሊገዛቸው ሳይሆን መላእክትን ሊመራ ፣ እኛን ደግሞ ከሰይጣን ጥቃት ሊጠብቀንና በጸሎቱ ሊራዳን ነው (ይሁዳ.12) ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ቅዱሳን መላእክት እኛን እንደሚጠብቁና እንደሚራዱ እንዲሁም ስለእኛ በፊቱ እንደሚቆሙ ሲያስተምረን“ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን ስንኳ እንዳትንቁ ተጠንቀቁ፤ መላእክቶቻቸው በሰማያት ሁል ጊዜ በሰማይ ያለውን የአባቴን ፊት ያያሉ እላችኋለሁ” (ማቴ.18፡10) ብሎናል። እኛን ይጠብቁ ዘንድ የተሰጡን ቅዱሳን መላእክት ስለእኛ እንዲህ የሚቆረቆሩና ስለመዳናችን የሚተጉ ከሆነ በቅድስናው ልቆ የመላእክት አለቃ ሆኖ የተሾመው ቅዱስ ሚካኤል እንዴት ስለእኛ በእግዚአብሔር ፊት ይበልጥ አይቆም? (ሉቃ.13፡6-9) እንዴትስ በተሰጠው ሥልጣንና ኃይል አይረዳን? (መዝ.33፡7) እርሱ “ስለሕዝብህ ልጆች የሚቆመው”መባሉም እኛን በጸሎቱና በተራዳኢነቱ የጽድቅ ሕይወታችንን በሚገባ እንድናከናውን እንደሚራዳን የሚያሳይ ኃይለ ቃል ነው። የመልአኩ የቅዱስ ሚካኤል ጸሎቱና በረከቱ በእኛ ላይ ለዘለዓለሙ ይደርብን አሜን።

Miko ZE Ethiopia

††† በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን !

10/ ድርሳን ዘቅዱስ ሚካኤል(እም ቅዱስ መጽሐፍ)

ቅዱስ ማለት ልዩ፥ ክቡር ማለት ነው፤ ሚካኤል ማለት ደግሞ «መኑ ከመ አምላክ፥ እንደ እግዚአብሔር ያለ ማነው?» ማለት ነው። ሚካኤል የሚለው ስም ቃሉ የዕብራይስጥ ነው፤ ሚ - የሚለው «መኑ» ማለት ነው፥ ካ - የሚለው «ከመ» ማለት ሲሆን፥ ኤል - ማለት ደግሞ «አምላክ» ማለት ነው። ይህን ማለትም የቅዱስ ሚካኤልን ስም በጠራን ቍጥር የምንመሰክረው ስለ እግዚአብሔር ነው፤ በመሆኑም እግዚአብሔርን በባሕርይ የሚመስለው፥ በሥልጣንም የሚተካከለው፥ በምድርም በሰማይም እንደሌለ የሚናገር ልዩ፥ ክቡር ስም ነው። የነቢያት አለቃ ሙሴ ባሕረ ኤርትራን ለሁለት ከፍሎ ሕዝቡን ያሻገረለትንና ፈርዖንን ከነሠራዊቱ ያሰጠመለትን አምላክ እግዚአብሔርን በመዝሙር ሲያመሰግን፥ «አቤቱ በአማልክት መካከል (በስም አማልክት ከሚባሉ፥ በስመ አማልክት ከሚጠሩ፥ አንድም አማልክት ዘበጸጋ ከተባሉ ከነቢያት ከካህናት መካከል) አንተን የሚመስል ማነው? በቅዱሳንም ዘንድ እንደ አንተ የከበረ ማነው?» ብሏል። ዘጸ ፲፭፥፲፩። ቅዱስ ዳዊትም፦ «አቤቱ፥ ከአማልክት የሚመስልህ የለም፤» ብሏል። መዝ ፹፭፥፰።

፩፥፩፦ «ስሜ ድንቅ ነውና ለምን ትጠይቃለህ?» መሳ ፲፫፥፲፯

የእስራኤል ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ክፉ በመሥራታቸው፥ እግዚአብሔር

በፍልስጥኤማውያን እጅ ለአርባ ዓመት አሳልፎ ሰጥቷቸው ነበር.። በዚህ ዘመን ከዳን ወገን ማኑሄ የሚባል አንድ ሰው ነበረ፥ ሚስቱም መካን ስለነበረች ልጅ አልወለደችም ነበር። የእግዚአብሔር መልአክ ተገልጦ እንደምትፀንስ፥ ወንድ ልጅም እንደምትወልድ፥ ልጁም ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ለእግዚአብሔር የተለየ ናዝራዊ እንደሚሆን ነገራት። የሚያሰክር መጠጥ እንዳትጠጣ፥ የረከሰም ነገር እንዳትበላ፥ በልጁም ራስ ላይ ምላጭ እንዳይደርስ (ፀጉሩን እንዳትላጨው) አስጠነቀቃት። እርሷም ተመልሳ የሆነውን ሁሉ ለባሏ ነገረችው፤ «የእግዚአብሔር ሰው ወደ እኔ መጣ፥ መልኩም እንደ እግዚአብሔር መልአክ እጅግ የሚያስደነግጥ ነበረ፤ ከወዴትም እንደመጣ ጠየቅሁት፥ እርሱም ስሙን አልነገረኝም፤» አለችው።

ማኑሄም፥ «ጌታ ሆይ፥ ወደ እኛ የላክኸው የእግዚአብሔር ሰው እባክህ እንደገና ወደ እኛ ይምጣ፤ ለሚወለደውም ልጅ ምን እንደምናደርግ ያስገንዝበን፤» ብሎ ወደ እግዚአብሔር ለመነ። እግዚአብሔርም የማኑሄን ቃል ሰማ፤ የእግዚአብሔርም መልአክ በእርሻ ውስጥ ሳለች እንደገና ወደ ሴቲቱ መጣ፥ እርሷም ፈጥና ባሏን ጠራችው፥ «እነሆ፥ አስቀድሞ ወደ እኔ የመጣው ያ ሰው ደግሞ ተገለጠልኝ፤» ብላ ነገረችው። እርሱም፦ «ከሚስቴ ጋር የተነጋገርህ አንተ ነህን?» ብሎ ቢጠይቀው «እኔ ነኝ፤» ሲል መለሰለት። ማኑሄም፦ «እነሆ ቃልህ በደረሰ ጊዜ የልጁ ነገር፥ ግብሩስ ምንድነው?» ብሎ ዳግመኛ ጠየቀ። መልአኩም ለሴቲቱ ነግሯት የነበረውን ሁሉ መልሶ ነገረው። ማኑሄ ለመልአኩ የፍየል ጠቦት ለማዘጋጀት ቢፈልግም፦ «አንተ የግድ ብትለኝ እህልህን አልበላም፥ የሚቃጠለውንም

መሥዋዕት ብታደርግ ለእግዚአብሔር አቅርብ፤» አለው። ምክንያቱም ቅዱሳን መላእክት ቅድሚያ የሚሰጡት ለእግዚአብሔር ክብር ነው። እነርሱን ግን እግዚአብሔር ራሱ እንደሚያከብራቸው እንደሚያስከብራቸውም ያውቃሉ።

ማኑሄ የተገለጠላቸው የእግዚአብሔር መልአክ እንደሆነ አላወቀም፥ ሚስቱም አላወቀችም። በመሆኑም፦ «ነገርህ በደረሰ ጊዜ እንድናከብርህ ስምህ ማን ነው?» በማለት ጠየቀው። የእግዚአብሔርም መልአክ፥ «ስሜ ድንቅ ነው፥ ለምን ትጠይቃለህ?» ብሎታል። ማኑሄም የፍየሉን ጠቦትና የእህሉን ቍርባን በድንጋይ ላይ ለእግዚአብሔር አቀረበ። መልአኩም ተአምራት አደረገ፥ ማኑሄና ሚስቱም ይመለከቱ ነበር። ነበልባሉም ከመሠዊያው ላይ ወደ ሰማይ በወጣ ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ በመሠዊያው ነበልባል ውስጥ ወደ ሰማይ ዐረገ፥ ማኑሄና ሚስቱም ተመለከቱ፥ በምድርም በግንባራቸው ወደቁ። (ሰገዱለት)። ይህ መልካም የምሥራችን የተናገረ፥ የተለያዩ ተአምራትን ያደረገ፥ መሥዋዕታቸውንም ወደ ሰማይ ያሳረገ፥ የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ሚካኤል ነው። ሚካኤል ማለት በሁለተኛ ትርጉሙ «የእግዚአብሔር ነገሩ ዕፁብ ድንቅ ነው፤» ማለት ነውና። መሳ ፲፫፥፭-፳። በዚህም የስሙ ትርጓሜ ነገረ እግዚአብሔር መሆኑን እንረዳለን።

፭፥፪፦ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ፤ ኢያ ፭፥፲፬

ከነቢያት አለቃ ከሙሴ በኋላ በእርሱ እግር ተተክቶ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የመራው ኢያሱ ነው። የመረጠውም ሰው ሳይሆን እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔርም፦ «በሕይወትህ ዘመን ሁሉ የሚቋቋምህ የለም፤

ከሙሴ ጋር እንደነበርሁ እንዲሁ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፥ አልጥልህም፥ ቸልም አልልህም፤» ብሎታል። ኢያ ፩፥፭። ይህ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የሆነለት ታላቅ ሰው ኢያሱ የቅዱሳን መላእክት ተራዳኢነት አስፈልጐታል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ለመሆኑ ምልክቱ ቅዱሳን መላእክት ናቸውና። እግዚአብሔር ባለበት ቅዱሳን መላእክት አሉ፥ ቅዱሳን መላእክትም ባሉበት እግዚአብሔር አለ። ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደባት ሌሊት የምሥራቹን «እነሆ፥ ለእናንተና ለሕዝቡ ሁሉ ደስታ የሚሆን ታላቅ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ፤ እነሆ፥ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት ተወልዶላችኋልና፤ ይኸውም ቡሩክ ጌታ ክርስቶስ ነው።» በማለት ለእረኞች የነገሯቸው ቅዱሳን መላእክት ናቸው። እረኞቹም፦ «እስከ ቤተልሔም እንሂድ፥ እግዚአብሔርም የገለጠልንን ይህን ነገር እንወቅ፥ አሉ።» ሉቃ ፪፥፮-፲፭። በዚህም ቅዱሳን መላእክት የገለጡላቸውን ምሥጢር እግዚአብሔር ገለጠልን ብለዋል።

ኢያሱ ወልደ ነዌ፥ ሕዝቡን እየመራ በኢያሪኮ አጠገብ ሳለ ዐይኑን አንሥቶ ቢመለከት እነሆም የተመዘዘ ሰይፍ በእጁ የያዘ ሰው በፊቱ ቆሞ አየ። ወደ እርሱም ቀርቦ «ከእኛ ወገን ወይስ ከጠላቶቻችን ወገን ነህን?» አለው። እርሱም «እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ነኝ፤ አሁንም ወደ አንተ መጥቻለሁ፤» ብሎታል። ኢያ ፭፥፲፫-፲፭። የእግዚአብሔር ሠራዊት የሚባሉት ቅዱሳን መላእክት ናቸው። «ያዕቆብም መንገዱን ሄደ፥ በዓይኖቹም የእግዚአብሔርን ሠራዊት ከትመው አየ፥ የእግዚአብሔር መላእክትም ተገናኙት። ያዕቆብም ባያቸው ጊዜ እነዚህ የእግዚአብሔር

ሠራዊት ናቸው አለ፤» ይላል። ዘፍ ፴፪፥፩-፪። ቅዱስ ዳዊትም፦ «ሠራዊቱ ሁሉ፥ ፈቃዱን የሚያደርጉ አገልጋዮቹ፥ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል፤» ብሏል። መዝ ፩፻፪፥፳፩። የእነዚህም (የእግዚአብሔር ሠራዊት) አለቃቸው ቅዱስ ሚካኤል ነው። ይኽንንም ሐዋርያው ቅዱስ ይሁዳ «የመላእክት አለቃ ሚካኤል» በማለት መስክሮለታል። ይሁዳ ፩፥፲፪።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር !

Eleni Tilahun

11/ ቅዱሳን መላእክት ለእግዚአብሔር የቅርብ አገልጋዮች ናቸው፤ በዙፋኑ ዙሪያ ሆነው ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ እግዚአብሔር እያሉ ዘወትር ያመሰግናሉ። †

በተልዕኳቸውም ፈጣኖች ናቸው፤ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ለተልዕኮ ይወርዳሉ ይወጣሉ፤ የሰው ልጆችንም ይረዳሉ።

(ራእ 4፥9-11)(መዝ 103፥4)(እብ 1፥4)

(ዮሐ 1፥52)

በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ለተልእኮ መፋጠናቸው የሰውን ጸሎት፤ ምጽዋትና መሥዋዕት ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ፤

የእግዚአብሔር ምሕረትና ቸርነት ወደ ሰዎች ማድረስ እንዲሁም ለቅጣት ይላካሉ። (ዳን.9፥20- 22)(ሉቃ 1፥3)(የሐዋ 1፥3-5)

ሰዎች በሞቱ ጊዜ ነፍሳቸውን ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ።

(ሉቃ 13፥22)(ሱቱ ዕዝ 6፥6-20)

(ዳን. 4፥13(ሮሜ 9፥22)

በመከራና በችግር ጊዜ ለተራዳኢነት ይላካሉ።

በፍጻሜ ዘመን ይህ ዓለም በሚያልፍበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ተልከው ታጥአንን ከጻድቃን መለየት እንደሆነ ቅዱስ መጽሐፍ ስለ ቅዱሳን መላእክት በሰፊው ያስረዳል።

(የሐዋ 12፥7- 11)(መዝ. 69፥7)

(ማቴ.2፥31)(ራእ.7፥1-4)

የቅዱሳን መላእክት ፈጣን ተራዳኢነት አይለየን ለዘለዓለሙ አሜን።

Aleph - አሌፍ

12/ ጎንደር 12 ቀን ማጎሌት

እንኳን አደረሰን

በዛሬው ዕለት የምናከብረው በዓል እግዚአብሔር በመልአኩ በቅዱስ ሚካኤል አማካኝነት ሕዝቡን ከግብጽ ከባርነት ቤት በማስወጣት ወደ ተስፋ ሀገረ ወደ ከነዓን እንዲገቡ ማድረጉን እና የእሥራኤል ዘሥጋ ነፃ መውጣትን ፣ ቅዱስ ሚካኤል ዱራታኦስን እና ቴዎብስታን ስለ መርዳቱ ፣ መስፍነ እሥራኤል ኢያሱን ለመርዳት መገለጡን እንዘክራለን።

ይህ የነጻነት በዓል ለአዲሲቷ እሥራኤል፤ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ጉዞ እና ነጻነት ምሳሌ ሲሆን። በዚያ ዘመን እሥራኤል ዘሥጋን በመንፈሰ ረድኤት እየረዳቸው፣ በዕደ መልአኩ እየጠበቃቸው፣ በሙሴ

እየመራቸው፣ ጠላት እያጠፋላቸው፣ ከተስፋዋ ምድር እንዲገቡ እንዳደረጋቸው ሁሉ በግብጽ በተመሰለች በዓለም ያለነው ክርስቶሳውያን ምእመናንንም ዐይን ያላያትን፣ ጆሮ ያልሰማትን፣ የሰው ልብም ያላሰባትን፣ እግዚአብሔር ለባለሟሎቹ ያዘጋጃትን አማናዊት ከነዓን ይህችውም መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ የበቃን ሆነን እንድንገኝ በመልአክህ ኃይል ሰውረን፣ ጠብቀን፣ አድነን በማለት ምሳሌውን በማሰብ አማናዊውን ጉዞ ደግሞ በማስቀጠል በረከት የምናገኝበት በዓል ነው።

የእሥራኤል ረዳታቸው ቅዱስ ሚካኤልም በጥበቃው በጸሎቱ ከእኛ እንዳይለይ ፤ ርግብ በክፍታ ሥፍራ ሆና በምድር የወደቀችውን ቅንጣት ዘር እንደምትመለከት ሁሉ ካለህበት ሥፍራ ከዓለመ መላእክት ሆነህ እያንዳንዳችንን ተመልከተን ፤ ጸሎታችን አሳርግልን ከሰይጣንም ማታለል ጠብቀን በማለት የምንለምንበት የተወደደች ዕለት ናት።

መልክዓ ሥላሴ

1

ሰላም ለጕርኤክሙ ስቴ አንብዓ ሰብእ ዘጎሠሠ፤

ብዑላነ ሞገስ ሥላሴ ኢታንድዩኒ ሞገሰ፤

እመ ትትሄየዩኒሰ ወተጎድጉኒ ጽኑሰ፤

ሚካኤልኑ ለአምጽኡ ሥጋየ ጌሠ

ወእመ አኮ ገብርኤል ወጎበኒ ነፍሰ።

ትርጉም ፦ [አብ ወልደ መንፈስ ቅዱስ ሆይ፤ ስለ ጥልቅ ንስሐ የተነሳሕያንን የንስሐ ዕንባ ስቴን (መጠጥ) ለሚሻ ጉርዔያችሁ ሰላምታ ይገባል፤(ሕዝ 18፡32) ሥሉስ ቅዱስ ሆይ የባለሟልነት ባለጸጋ ናችሁና

ከባለሟልነታችሁ አታውጡኝ። ከባለሟልነት አውጥታችሁ በቸልታ ከተመለከታችሑኝማ ሚካኤል ገስግሶ ሥጋዬን ለማስገኘት ይሆንለታልን ? ወይስ ገብርኤል በክንፉ ከንፎ የነፍስን ሕይወት ሊሰጠኝ ይቻለዋልን ክሂሎት የእናንተ ብቻ ነው።]ጐሥዓ ልብየ ጥበበ ወልቡና ፤

ዚቅ

አመ ይፈጥራ እግዚአብሔር ለምድር፤

ኢዜነዎ ለሰማይ ወኢተማከረ ምስለ መላእክቲሁ፤

ወተከለ ሠለስተ ዕፀ ሕይወት በዲበ ምድር፤

እንተ በምድር ሥረዊሃ ወበሰማይ አዕፀቂሃ፤

ዘሠናየ ጽጌ ደንጐላት ወጥዑመ ይፈሪ ሲሳዮሙ ለቅዱሳን።

ነግሥ

2

ለውዳሴከ ጥዑመ ዜና፤

ቅዱስ ሚካኤል ልማድከ ግብረ ትጎትና ፤

አንተኑ ዘመራሕኮሙ ፍና፤

ወአንተኑ ለእሥራኤል ዘአውረድከ መና፤

ዚቅ

አዝነመ ሎሙ መና ይብልዑ፤

ፀዓዳ ከመ በረድ ወርእየቱ ከመ ተቅዳ፤

ጎብስተ እምሰማይ ወሀቦሙ፤

አውሐዘ ሎሙ ማየ ሕይወት፤

ዘትረ ኬኩሕ ፈልፈለ ነቅዓ ዘኢይነጽፍ ፤

ጎብስተ እምሰማይ ወሀቦሙ።

3

ሰላም ለዝክረ ስምከ ምስለ ስመ ልዑል ዘተሳተፈ፤

ወልደ ያሬድ ጌኖክ በከመ ጸሐፈ ፤

ሶበ እጼውዕ ስመከ ከሚትየ አፈ፤

ረዳኤ ምንዱባን ሚካኤል በከመ ታለምድ ዘልፈ፤

ለረዲኦትየ ነዓ ሰፊሐከ ክንፈ።

ትርጉም ፦ [የያሬድ ልጅ ጌኖክ እንደጻፈው ከልዑል ስም አጠራር ጋር ለተባበረ ስምህ አጠራህ ሰላም እላለሁ።

የእግዚአብሔር የምክሩ አበጋዝ ሆይ የተቸገረቱን የተጨነቁትን ዘውትር እንደምትረዳቸው ሁሉ እኔንም ለመርዳት ክንፍህን ዘርግተህ ፈጥነህ ድረስልኝ።]

ዚቅ

ውእቱ ሚካኤል መልአከ ኃይል ፤ ልዑል ውእቱ ልዑለ መንበር፤

ይሰአል ለነ ረዳኤ ይኩነነ አመ ምንዳቤነ፤

ሰፊሆ ክነፊሁ ይጸልል ዲቤነ።

3

ሰላም ለልሳንከ በነቢበ ጽርፈት ዘኢተሀበለ ፣

በእንተ ሥጋሁ ለሙሴ አመ ምስለ ሰይጣን ተበህለ

ሚካኤል ክብርከ እምክብረ መላእክት ተልዕለ

ቀዊምየ ቅድመ ሥዕልክ ሶበ አወትር ስኢለ

በብሂለ ኦሆ ፍጡነ አስምዐኒ ቃለ።

ትርጉም ፦ [ስለ ሙሴ ሥጋ ከሰይጣን ጋር ክርክር በተደረገ ጊዜ የዘለፋን ቃል ላልተናገረው አንደበትህ ሰላም እላለሁ።ክቡር መልአክ ሆይ ክብርህ ከመላእክት ሁሉ ክብር ከፍ ያለ ነውና፤ በሥዕልህ ፊት ቁሜ ልመናዬን በማቀርብበት ጊዜ ሁሉ እሽ በማለት ፈጥነህ ቃልህን አሰማኝ።]

(የሐዋርያው የቅዱስ ይሁዳ መልእክት ቁ. 9)

ዚቅ

ረሰዮ እግዚኡ ፡ ለውእቱ ሚካኤል ፤

እምኩሎሙ መላእክት ይትሌዓል መንበሩ ።።

4

ሰላም ለሕንብርትከ፡ ሕንብርተ መንፈስ ረቂቅ፤

ዘቱሳሔሁ መብረቅ፤

ነግህ ነግህ አንተ በአዝንሞ መና ምውቅ ፤

በገዳም ዘሴሰይኮሙ ለነገደ ጎሬ ደቂቅ፤

ሴስየኒ ሚካኤል ሕገከ ዘጽድቅ።።

ዚቅ

ባሕረ ግርምተ ፡ ገብረ ዓረፍተ ወበውስቴታ አርአየ ፍኖተ፤

በእደ መልአኩ ዓቀቦሙ በገዳም ለሕዝቡ አርብዓ ዓመተ፤

ወሴሰዮሙ መና ጎብስተ ፡ ኪነ ጥበቡ ዘአልቦ ዘአልቦ መስፈርተ።።

5

አምኃ ሰላም አቅረብኩ ለመልክእከ ኩሉ፤

ለለ አሐዱ አሐዱ ዘበበክፍሉ፤

ሚካኤል ክቡር ለልዑል መልአከ ኃይሉ፤

ተወኪፈከ አምኃየ እምኑኅ ሰማያት ዘላዕሉ፤

ዕሴተ ጸሎትየ ፈኑ ወአስብየ ድሉ።

ትርጉም ፡- [ሚካኤል ሆይ ለእያንዳንዱ በየ ክፍሉ ለተነገሩ መልኮችህ ሁሉ የምስጋና እጅ መንሻ አቀርባለሁ። ልዑል መልአክ ሆይ እግዚአብሔር ኃይሉን የሚገልጽብህ ኃያል መልአክ ነህና የምስጋናዬን እጅ መንሻ ተቀብለህ ከላይ ከኢየሩሳሌም ሰማያዊት የጸሎቴን ዋጋ እጥፍ ድርብ አድርገህ ላክልኝ።]

ዚቅ

ተወከፍ ጸሎተነ ውስተ ኑኃ ሰማይ፤

ወስእለተነ ከመ መዓዛ ሠናይ፤

ተወከፍ ጸሎተነ ውስተ ኑኃ ሰማይ።

+++

ምልጣን

ውእቱ ሚካኤል መልአክ ኃይል ፤ ልዑል ውእቱ ልዑለ መንበር፤

ይሰአል ለነ ረዳኤ ይኩነነ አመ ምንዳቤነ፤

ሰፊሆ ክነፊሁ ይጸልል ዲቤነ።

እስመ ለዓለም

ሠርዓ ለነ ሰንበተ ለዕረፍተ ዚአነ፤

ከመ ናዕብያ ወናክብራ ለዕለተ ሰንበት፤

መላእክተ ሰማይኒ ወኩሉ ፍጥረት ፤

እለ ውስተ ሲኦል፡ እለ ውስተ ደይን ፡ ያዕርፉ ባቲ ፤

እስመ ቀደሳ አዕበያ ወአልዓላ ለዕለተ ሰንበት፤

መኑ ከማከ ስቡሕ እግዚኦ በውስተ ቅዱሳን ፤

መንክር ስብሐቲከ እግዚኦ ወትረ እሴብሐከ።

ሰላም

መልአከ ሰላምነ ሊቀ መላእክት ሚካኤል፤

ሰአል ወጸሊ በእንቲአነ አዕርግ ጸሎተነ ቅድመ መንበሩ ለንጉሥ ዓቢይ።

መዝሙር

ሃሌ (፰)

ኢተዘኪሮ አበሳ ዚአነ ፤ ኢጎደገነ ፍጹመ ንማስን ኄር እግዚአብሔር፤

አዘዞሙ ሙሴ ለሕዝቡ ያክብሩ ሰንበተ በጽድቅ ።

(ቸር የሆነ እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ባለማሰብ [ይቅር በማለት]፤ እንጠፋ ዘንድ ፈጽሞ አልተወንም። (ያለ መተው ማሳያውም ሰንበትን በማክበር ከሚገኘው ጸጋ ተሳታፊ እንሆን ዘንድ ፤ በቃል ምክር ወደ በጎነት ይመራን ዘንድ) ሙሴ በእውነት ሰንበትን ያክብሩ ዘንድ ሕዝቡን አዘዛቸው፤ አስተማራቸው)።

ወይም (በቤተልሔም)

ፈጽም ለነ ሠናይተከ እንተ እምኀቤነ

እግዚኦ ለሰንበት ወአቡሃ ለምሕረት፤

ሀሉ ምስሌነ ፀወንነ ወኃይልነ ፤

ረዳኤ አመ ምንዳቤነ ኩነነ እግዚኦ።

የሰንበት ጌታ የምሕረት አባት ሆይ በአንተ ዘንድ ያለችውን በጎነት ፈጽምልን፤

(ሀብተ ዉልድናን ወይም ልጅነትን እንደ ሰጠኸን ሁሉ ለመንግሥትህ

አብቃን)

ኃይላችን እና መጠጊያችን ሆይ አንተ ከእኛ ጋር ሁን፤ ከእኛ አትለይ፤

አቤቱ በችግራችን ጊዜ ረዳት ሁነን።

+++

የቅዱስ ሚካኤል ልመናው እና አማላጅነቱ አይለየን፤ መልካም በዓል።

Jemal Hassen Ali Yimer

አንድ አምላክ በሚሆን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አሜን

13/ ጎንደር 12- ከጽንፍ እስከ ጽንፍ የሚበር ንሥረ አርያም የሚባል ውዳሴው እንደ ማር የጣፈጠ ንዑድ ክቡር የሆነ ለፍጥረቱ ሁሉ የሚማልድ የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል የተሾመበት ዓመታዊ በዓሉ ነው። ዳግመኛም ዛሬ የጻዲቁ ንጉሥ የበእደ ማርያም ዕረፍታቸው ነው። እንዲሁም የመጥምቁ ዮሐንስ በደብረ ማህው የታየችበት ዕለት ነው። በረከታቸው በሁላችን ላይ ይደርብን በጸሎታቸው ይማረን።

ሚካኤል ማለት በዕብራይስጥ ቋንቋ ሚ-መኑ' ካ-ከመ' ኤል-አምላክ ማለት ሲሆን በአንድነት ሲነበብ ‹‹መኑ ከመ አምላክ-እንደ እግዚአብሔር ያለ ማን ነው›› ማለት ነው። አንድም ለእግዚአብሔር አሸናፊ ድል አድራጊ የቸርነትና የርህራሄ መገኛ መዝገብ ማለት ነው።

ገናናው መልአክ ቅዱስ ሚካኤል ዲያብሎስን ወደ ጥልቁ ጥሎት በእርሱ ምትክ ከሁሉ የበላይ ሆኖ በተሾመበት በዚህ ዕለት በበዓሉ መታሰቢያ በጎንደር 12 ቀን የክብር ባለቤት በሆነ በእግዚአብሔር ፈቃድ ክንፎቹን ወደ ሲኦል

ያወርዳል፣ ኃጥአንንም ወደ አዲሲቱ ምድር ያወጣቸዋል ይኸውም የመላእክት አለቃ የሚካኤል ሠራዊት ይሆናሉ። ይቅርታ የተደረገላቸውና ምሕረት አግኝተው በአንድ ጊዜ በክንፉ ያወጣቸው ስፍር ቁጥር የላቸውም። ቅዱስ ሚካኤል በየዓመቱ በጎዳር 12 ቀን እንዲህ እያደረገ እልፍ ነፍሳትን ያወጣል። የቤተ ክርስቲያን ወገኖች የሆኑትን ሁሉ እንደሥራቸው ወደ ምሕረት ቤት ወደ ሰማያዊት ኢየሩሳሌም ይወስዳቸዋል። ከዚህም በኋላ ወደ አብ መጋረጃ ውስጥ ይገባል፣ በዚህች ዕለት ምድራዊትና ሰማያዊት ስለሆነች ምሕረቱም ከመንበሩ በታች ይሰግዳል። ስለውኃ ምንጮች፣ ስለ ወይን ቦታዎች፣ ስለ ምድር ፍሬዎች በምድርም ላይ ስለሚኖሩ ስለ ሰው ልጆች ነፍስ ሁሉ፣ ስለ እንስሳትም፣ ስለ ሰማይ ወፎችም፣ ስለ ባሕር ዓሣዎችም፣ በምድር ላይና በባሕር ውስጥ ስለሚንቀሳቀሱ ሁሉ የምሕረት ባለቤት ከሆነ ከአብ ዙፋን በታች ሁልጊዜ በማመስገን ይሰግዳል፤ ልመናውንም እስኪሰማውና የምሕረትንም ቃል እስኪያስተላልፍለት ድረስ ከእግረ መንበሩ ሥር አይነሣም።

ለዚህ ዓለም ምሕረትን የሚለምኑ ቅዱሳን መላእክትም በየዓመቱ ጎዳር 12 ቀንበእግዚአብሔር የዙፋኑ ዓውደ ምሕረት ዙሪያ ተሰብስበው ስለ ሰውና ስለ እንስሳትም ሁሉ ምሕረትን የሚለምን ቅዱስ ሚካኤል ከአብ መጋረጃ ውስጥ በወጣ ጊዜ ቸርና መሐሪ አብ ለቅዱስ ሚካኤል የሰጠው ልብሱን እነዚያ መላእክት ይመለከታሉ፣ ይቅርታን የማግኘት ምልክታቸው ነውና። ስለዚህ እነዚህ ቅዱሳን መላእክት በምድር ላይ ምሕረት እንደተደረገ ሰውንም እንስሳትንም ይቅር እንዳለ በዚህ ዓለምም የሚሆነውን ሁሉ አይተው ቅዱስ ሚካኤል በለበሰው ልብስ አምሳል ያውቁታል።

ስንክሳሩ እንደሚለው ይህ እጅግ የከበረ ገናና መልአክ ቅዱስ ሚካኤል ‹‹ከቅዱሳን ሰማዕታት ጋራ በመሆን ገድላቸውን እስኪፈጽሙ ድረስ የሚያጽናናቸውና የዘወትር ጠባቂአቸው ሆኖ የሚራዳቸው እርሱ ነው።›› የብዙዎቹንም ቅዱሳን ገድል ስንመለከት የዘወትር ጠባቂያቸው ቅዱስ ሚካኤል ነው።

ቅዱስ ሚካኤል አቡነ ሀብተ ማርያምን እንደ ጓደኛ ሆኖ ዘወትር ይጎበኛቸው ነበር። ሌለች ቅዱሳን አባታችንን ሊጎበኟቸው መጥተው ከደጅ ቆመው እንደሆነ ቅዱስ ሚካኤል አባታችንን ‹‹እከሌ ጉዳዩ እንዲህ ነው እንዲህ ብለህ ተናገረው...›› እያለ ያማክራቸው ነበር። እሳቸውም ቅዱስ ሚካኤል ካዘዛቸው በቀር ምንም አይሠሩም ነበር። ቅዱሳት መጻሕፍትንም ባነበቡ ጊዜ ኃይለ ቃሉን እየተረጎመ ምሥጢራትን ይነግራቸዋል፤ የተሰወረውንም ይገልጥላቸዋል።››

አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወደ አቡነ ኢየሱስ ሞዐ መጥተው በሐይቁ ዳር ቆመው ሳለ ይህ ጋናመልአክ ቅዱስ ሚካኤል ተገልጦላቸው ነው በእግሩ በውኃው ላይ እየሄደ እያሳያቸው ተከትለውት እንዲሄዱ የነገራቸው። አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖትም መልአኩን ተከትለው ሐይቁን በእግራቸው ተራምደው ተሻግረው አቡነ ኢየሱስ ሞዐን አገኟቸው። እርሳቸውም አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወደ እርሳቸው እየመጡ እንደሆነ በመንፈስ ዐውቀው ነበርና ሲያገኟቸው በጣም ተደስተው ከተቀበሏቸው በኋላ አመነኩሰዋቸዋል።

ከዕለታትም በአንደኛው ቀን እናታችን ክርስቶስ ሠምራ ዕለተ ሞቷን እያሰበች በጣና ባሕር ውስጥ ቆማ ስታለቅስና ስትጸልይ ሣለች ዲያብሎስ

በሊቀ ጳጳሳት ተመስሎ እጅግ አስደናቂና ግሩም በሆነ አርአያ ወደ እርሷ መጣ። እርሷም ልትሰግድለት ወደደች፣ ከኃዘኗ ያረጋጋት ዘንድ ከቅዱሳን አንዱ የመጣ መስሏት ነበርና። ነገር ግን የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ፈጥኖ ደረሰና ‹‹ይህ ሰይጣን እንጂ ጳጳስ ወይም ከቅዱሳን አንዱ አይደለምና አትስገጂለት›› ብሎ ወደኋላዋ መለሳት። ዳግመኛም ‹‹አሁንም እንደልማድሽ ሂጂና ጠይቂው ማን እንደሆነ ይነግርሻል›› አላት። በዚህን ጊዜ ወደ እርሱ ሂደችና ‹‹እሰግድልህ ዘንድ አንተ ማን ነህ?፣ ስምህስ ማን ይባላል?›› ስትል ጠየቀችው። እርሱም ‹‹የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ነኝ›› አላት። የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ከእርሷ ጋር እንዳለ አላወቀም ነበርና። እርሱ በእርሷ ላይ ተንኮል ለመሥራት እንደተራቀቀ ሁሉ እርሷም ነቃችበት ተራቀቀችበት።

በሌላም ጊዜ ይህች ቅድስት እናታችን ክርስቶስ ሠምራ ጌታችንን ‹‹አቤቱ ፈጣሪዬ ፈቃድህስ ቢሆን የአዳም ልጆች ከስቃይ ከኩነኔ ይድኑ ዘንድ ዲያብሎስን ይቅር ትለውና ትምረው ዘንድ እለምንሃለሁ፣ የኃጥእን መመለሱን እንጂ ጥፋቱን አትወድምና። የምለምንህ ወድጄው አይደለም ነገር ግን እርሱ ከተማረ በአዳም ልጆች ላይ ሥቃይና ኩነኔ ሊኖር አይችልም ብዬ በመገመት ነው እንጂ›› አለችው። ይህንንም ባለችው ጊዜ ጌታ በጥያቄዋ ተገርሞ ‹‹ሌሎች ካንቺ በፊት የነበሩ ካንቺም በኋላ የሚነሡ የማያስቡትን እጅግ የሚያስደንቅ ልመና ለመንሽኝ›› ብሎ ካደነቃት በኋላ ቅዱስ ሚካኤልን ጠርቶ ‹‹ሳጥናኤል እሺ ካላት ታወጣው ዘንድ ወደ ሲኦል ይዘሃት ሂድ›› ብሎ አዘታል። በዚያም ሄዳ እንኳን እርሱ ሊመለስላት ይቅርና እርሷንም ከሲኦል ወረወራት ነገር ግን ይጠብቃት የነበረው መልአክ

በእሳት ሰይፉ ዲያብሎስን በመቅጣት እርሷን መዞ ሲያወጣት በዚህ ጊዜ በቅዱስ ሚካኤልና በእርሷም ክንፍ ተጣብቀው ዓሥር ሺህ ነፍሳት ሊወጡ ችለዋል። እርሷም በዚህ እጅግ ተደስታ ወደ ፈጣሪዋ ሄዳ <<አቤቱ ፍርድህ የቀና ምሕረትህ የበዛ ነው>> እያለች ለጌትነቱ ክብር ሰግዳለች።

ከዕለታትም በአንደኛው ቀን መልአኩ ቅዱስ ራጉኤል አንዱን ሰው በመብረቅ ቀሰፈውና ቅዱስ ሚካኤል ሄዶ ቅዱስ ራጉኤልን ሲከራከረው አባታችን ተመለከቱ። ቅዱስ ሚካኤል <<የእኔ አገልጋይ ነውና ለምን ገደልከው?>> ሲለው ቅዱስ ራጉኤልም <<ሰንበት ሳይለይ ዝሙትን መሥራት የለመደ ሥራውም ዝሙት ስለሆነ በፈጣሪዬ ታዝዤ ነው የገደልኩት። ኃጥአንን ሊያጠፋ እንጂ ጻድቃንን ለመቅጣት መብረቅ እንዳይታዘዝ አንተስ ታውቅ የለም እንዴ?>> አለው። ይህንንም ተባብለው ከሥላሴ ፊት ሰግደው ቅዱስ ሚካኤል የተገባለትን ቃልኪዳን በማሳሰብ ምልጃውን አቀረበ። እግዚአብሔርም በጎና ክፉ ሥራዋን ባስመዘነ ጊዜ በጎ ሥራዋ ስለበለጠ ቅዱስ ሚካኤል ያችን ነፍስ ታቅፎ ወስዶ ለቅዱስ ገብርኤል ሰጠው። ሰባቱም ሊቃነ መላእክት እየተቀባበሉ ወስደው ከመስቀል ዘንድ አደረሷት። ለቅዱስ መስቀልም ካሰገዷት በኋላ አሳልመዋት በቅዱስ ሚኤካል አማላጅነት ወደ ገነት አስገቧት። አቡነ ሀብተ ማርያምም ይህን በተመለከቱ ጊዜ ቅዱስ ሚካኤልን <<መስቀል ታሳልሚት ዘንድ ያችን ነፍስ ወደ መስቀል ለምን ወሰዳችኋት?>> ብለው ጠየቁት። መልአኩም <<በትልቅም በትንሽም ነገር ክርስቲያናዊትን ነፍስ የሚቃወም ቢመጣባት ድል የምትነሳበትን በመስቀል ፍርድ ይታይላታልና ስለዚህ ነው። የሚከራከራት ቢኖር ግን እንዳየኸው ወደ መስቀል ባደረሷት ጊዜ

የሚቃወማት ሰይጣን ፈጥኖ ይርቅላታል ዳግመኛም ሊከራከራት አይችልም›› አላቸው።

ቅዱሳን በሕይወት ሳሉ ይህ ገናና መልአክ ቅዱስ ሚካኤል ረዳትና የዘወትር ጠባቂ፣ እንደጓደኛም አማካሪ ሆኖ የተበቃቸውን ስንቱን ቅዱሳን ዘርዝረን እንቸላለን። እርሱ ያልረዳው ቅዱስ የለም። መከራውን ያላስታገሰው ሰማዕት የለም። ለቅዱሳኑ እንዲህ እንደጓደኛቸው ሆኖ ሲጠብቃቸው ይኖራል። ነገር ግን ቅዱስ ሚካኤል ለኃጥአንና አምላካቸውን ለካዱ ሰዎች ደግሞ በቁጣ ለመቅሰፍት ይመጣባቸዋል። ሰናክሬም በእግዚብሔር ላይ ክፉ በመናገሩ በአንዲት ሌሊት ብቻ 185,000 (መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ) ሠራዊቱን ቅዱስ ሚካኤል በብርሃን ሰይፉ ፍጅቷቸው አድሯል። 2ኛ ነገ 19፡35፣ ኢሳ 37፡36።

እግዚአብሔርን ለሚወዱና እርሱንም ለሚያከብሩት መታሰቢያውንም ለሚያደርጉለት ግን ከሚፈልጉት ነገር ከቶ አያሳጣቸውም፣ ዘወትርም ይጠብቃቸዋል፣ በኋላም በአማላጅነቱም ከሲኦል እሳት ያድናለቸዋል። እነሆ ይህ ገናና ክቡር መልአክ ቅዱስ ሚካኤል ያደረገው ተአምር ይህ ነው፡-

‹‹የእግዚአብሔር ወዳጅ የሆነ ስሙ ዱራታዎስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ። የሚስቱም ስም ቴዎብስታ ነው። እነርሱም ሁልጊዜ ያለማቋረጥ የዚህን የከበረ መልአክ የቅዱስ ሚካኤልን የበዓሉን መታሰቢያ ያደርጉ ነበር። ከዚህም በኋላ በሀገር ውስጥ ችግር በሆነ ጊዜ ገንዘባቸው አለቀ። ለቅዱስ ሚካኤልም ለበዓሉ መታሰቢያ የሚያደርጉትን እስኪያጡ ድረስ ቸገራቸው። ዱራታዎስም ሸጦ ለመልአኩ በዓል መታሰቢያ ያደርገው ዘንድ የእርሱንና የሚስቱን ልብስ ይዞ ወጥቶ ሄደ።

የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤልም በታላቅ መከንን አምሳል ለዱራታዎስ ተገለጠለትና ወደ ባለጸጎች ሄዶ በእርሱ ዋስትና በአንድ ዲናር አንድ በግ እንዲወስድ፣ ሁለተኛም ወደ ባለ ስንዴ ዘንድ ሄዶ በእርሱ ዋስትና ስንዴን እንዲወስድ ዳግመኛም ወደ ዓሣ አጥማጅ ዘንድ ሄዶ አንድ ዓሣ እንዲወስድ ነገር ግን ወደቤቱ ሳይርስ የዓሣውን ሆድ እንዳይቀድ አዘዘው። ዱራታዎስም እንደታዘዘው አደረገ። ወደቤቱም በተመለሰ ጊዜ ቤቱ ሁሉ በበረከት ተመልቶ አገኘው። እርሱም እጅግ ተደስቶ የዚህን የክበር መልአክ የመታሰቢያውን በዓል አደረገ። ጦም አዳሪዎችንና ድኆችን ጠርቶ አጠገባቸው።

ከዚህም በኋላ ለዱራታዎስና ለሚስቱ ቅዱስ ሚካኤል ሁለተኛ ተገለጠላቸው። ዱራታዎስንም የዓሣውን ሆድ እንድሰነጥቅ አዘው። በሰነጠቀውም ጊዜ 300 የወርቅ ዲናር በዓሣው ሆድ ውስጥ ተገኘ። ቅዱስ ሚካኤል ዱራታዎስንና ሚስቱን ቴዎብስታን እንዲህ አላቸው፡- ‹‹ከዚህ ዲናር ወስዳችሁ ለባለ በጉ፣ ለባለ ዓሣውና ለባለ ስንዴው ዕዳችሁን ክፈሉ። የቀረውም ለፍላጎታችሁ ይሁናችሁ እግዚአብሔር አስቧችኋልና በጎ ሥራችሁን፣ መሥዋዕታችሁንና ምጽዋታችሁን አስቦ በዚህ ዓለም አሳመረላችሁ፣ በኋለኛውም መንግሥተ ሰማያትን አጀጋጀላችሁ›› አላቸው።

እነርሱም ይህን ነገር ሲሰሙ ደነገጡ። የከበረ ገናናው መልአክም ‹‹ከመከራችሁ ሁሉ ያዳንኳችሁ የመላእክት አለቃ እኔ ሚካኤል ነኝ፣ መሥዋዕታችሁንና ምጽዋታችሁን ወደ እግዚአብሔር ፊት ያሳረግሁ እኔ ነኝ። አሁንም በዚህ ዓለም ከበጎ ነገር እንድታጡ አላደርጋችሁም››

አላቸው። ይህንንም ከነገራቸው በኋላ ወደ ሰማያት ወጣ። እነርሱም በፍርሃትና በክብር ሰገዱለት።››

የኃይላት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ከበዓሉ ረድኤት በረከት ይክፈለን። ጥበቃውና አማላጅነቱ ሁላችን የምናምነውን ይጠብቀን።

(ምንጭ፡- ድርሳነ ቅዱስ ሚካኤል፣ ስንክሳር ዘወርሃ ጎዳር፣ ከገድላት አንደበት)

Miko ZE Ethiopia

14/ ቅዱሳን መላእክት ፦

መላዕክት ምህረትንና ቁጣን ከእግዚአብሔር

ወደ ምድር ልመናንና ፀሎትን ወደ እግዚአብሄር

የሚያሳርጉ በእግዚአብሔር የተፈጠሩ ረቂቃን

ፍጥረታት ናቸው። የመላዕክት ቁጥራቸው

እልፍ አእይላፋት ነው። ኢዮ 2÷53፣ ኤር

33÷22፣ ዳን 7÷10፣ ሄኖ 10÷1፣

ራዕ 5÷11

መላዕክት በሚፈራቸው ሰዎች ዙሪያ

ይሰፍራሉ፣ ይብቋቸውማል፣ ከመከራም ሁሉ

ያወጧቸዋል መዝ

3÷37፣ሐዋ 5÷19-20፣ ዳን

6÷22፣ ዳን 10÷13፣ መዝ

90÷11-12

መላዕክት አብሳሪያን ናቸው

ዘፍ 16÷11፣ ሉቃ 1÷13፣

ሉቃ 1÷19፣ሉቃ 1÷30-31፣

ሉቃ 2÷10-11፣

መላእክት በጭቀት ጊዜ ይደርሳሉ

ዘፍ 16÷7-8፣ዘፍ 21÷16-17፣ማቴ

28÷5-6፣ ዩሃ 20÷12-13

መላዕክት ያፅናናሉ ይመክራሉ ዘፀ

23÷20፣ ዳን 9÷21-22፣ ሀዋ

8÷26፣ ሃዋ 27÷23፣ ዕብ 1÷14

ስግደት ለመላእክት፦

መስገድ የሚለው ቃል መዋረድ፣ ማጐንበስ፣

መንበርከክ፣ መደፋት፣ በግንባር መውደቅ፣

ግንባርን ምድር አስነክቶ መሬት ስሞ መመለስ

ነው በማለት የአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ

መዝገበ ቃላት ያትታል። በቤተ

ክርስቲያናችን ስግደት የአምልኮና የጸጋ ተብሎ

ይከፈላል። የአምልኮ ስግደት ለእግዚአብሔር

ብቻ የሚቀርብ ሲሆን የጸጋ ስግደት ደግሞ

እግዚአብሔር ላከበራቸው ቅዱሳን ሰዎችና

መላእክት የሚቀርብ ነው።

ለቅዱሳት መላእክት የምናቀርበው ስግደት

ከላይ እንደተገለጸው የጸጋ ስግደት ነው።

ጸጋ የሚለው ቃል በቁሙ ሲተረጎም ሀብት፣

መልካም ሥጦታ፣ ዕድል ፈንታ፣ ትምህርት፣

ብዕል፣ ክብር፣ ሞገስ የቸርነት ሥ፣ራ አለዋጋ

የሚሰጥና የሚደረግ ማለት ነው። የጸጋ

ስግደት ስንል እግዚአብሔር የሰጣቸውን ክብርና

ሞገስ አምኖ መንበርከክ ነው። ይህም ራስን

ለእግዚአብሔር ከማስገባት የሚመነጭ ነው።

ሰዶምና ገሞራን በእሳት ለማቃጠል የተላኩት

መላእክት ወደ ሎጥ ቤት በገቡ ጊዜ ሎጥ

በግምባሩ ተደፍቶ ለመላእክቱ እንደሰገደ

ተጽፏል (ዘፍ 19፡1)።

ኢያሱ ወልደ ነዌ የመላእክት አለቃ ቅዱስ

ሚካኤል በተገለጠለት ጊዜ በግምባሩ ተደፍቶ

ለመልአኩ ሰግዶለታል። በዚህ ጊዜ ቅዱስ

ሚካኤል የተቃውሞ አነጋገር አልተናገረም።

‹‹የቆምክባት ሥፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና

ጫማህን ከእግርህ አውጣ›› ከማለት በስተቀር

(መጽ ኢያሱ 5፡13)።

የእሥራኤል ንጉሥ የነበረው ነቢየ እግዚአብሔር

ዳዊት ከእሥራኤል ሽማግሌዎች ጋር ከመሬት ከፍ
ብሎ ሰይፉን ዘርግቶ ለተገለጠላቸው
ለእግዚአብሔር መልአክ ሰግደውለታል (ዜና
መዋዕል ቀዳ 21፡16)።
ነቢየ እግዚአብሔር ዳንኤል መልአኩ ቅዱስ
ገብርኤል በአባል ወንዝ አጠገብ በተገለጠበት
ጊዜ ለመልአኩ ለቅዱስ ገብርኤል ራሱን ዝቅ
አድርጐ በግንባሩ ወድቆ ሰግዶለታል።
በዚሁም ላይ የግርማውን አስፈሪነት እና
አስደንጋጭነት ጠቅሷል (ዳን 8፡15)።
መሳ 13÷15-28 ‹‹ .... በምድርም
በግንባራቸው ታደፉ....›› ማኑኤልና ሚስቱ
በፊታቸው ለነበረ የእግዚአብሔር መላዕክ
የፀጋ ስግደት እንደሚገባው ተረድተው በፊቱ
ተደፉ ሰገዱም።
ዘፍ 19÷1 ‹‹ ሁለቱም መላዕክት በመሸ ጊዜ
ወደ ሶደም ገቡ ሎጥም በሰደም በር ተቀምጦ
ነበር። ሎጥም ባያቸው ጊዜ ሊቀበላቸው ተነሳ
ፊቱንም ደፍቶ ወደምድር ሰገደ›› ለቅዱሳን
መላዕክት ስግደት እንዲገባ ሎጥ ሰገደ።
ብዙዎች ሰው መስለውት ነው የሰገደው የሚሉ
አሉ፣ ታዲያ ለሰው ከሰገደ ለመላዕክት እንዴ

አይሰግድ? ተሳስቶ ነው የሠገደው የሚሉም

አሉ። ይህ ከሆነ በመፅሀፍ ቅዱስ የተሳሳተ

ነገር እንዴት ይፃፋል?

ዘፀ 22÷31 ‹‹ እግዚአብሔርም የበለአምን

አይኖች ..... ሰገደም በግንባሩም ወደቀ››

በለአም ስለመላዐኩ ክብር በግንባሩ ተደፍቶ

ሰገደ ይህ ግን የአምላኮ ስግደት አይደለም

ኢያ 5÷14 ‹‹ እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት

አለቃ ሆኜ አሁን መጥቻለሁ አለ። ኢያሱም

ወደ ምድር በግምባሩ ተደፍቶ ሰገደና ....››

የምመልኩትን ዛሬ ምረጡ እኔና ቤቴ ግን

እግዚአብሔርን እናመልካለን ያለው እያሱ

ተሳስቶ እንዳልሰገደ ለሁላችንም ግልጽ ነው

ስለዚህ ኢያሱ እንኳን ሰግዷል የጸጋ

ስግደትን።

ዳን 8÷16-17 ‹‹ .... እርሱም ወደቆምሁበት

ቀረበ በመጣም ጊዜ ፈርቼ በግምባሬ ተደፋሁ››

በብሉይ ኪዳን የፀጋ ስግደት ለፃድቃንና

መላዕክት እንዲገባ በብዙ ቦታ ተፅፎ

ይገኛል። ወደ ሃዲስ ኪዳን ሐደን አንድ

ሁለት ምሳሌ ደግሞ እንይ።

ሐዋ 16÷25-31 ‹‹ ..... መብራትም ለምኖ

ወደ ውስጥ ሮጠ እየተንቀጠቀጠም ከጳውሎስና

ከሲላስ ፊት ተደፋ...›› ታዲያ ለጳውሎስና

ለሲላስ የሠገደው የወህኒ ቤቱ ጠባቂ

ለመላእክት የጸጋ ስግደት ቢሠግድ ምኑ ላይ

ይሆን ስህተቱ? የወህኒ ቤቱ ጠባቂ በግንባሩም

ተደፍቶ የህይወትን መንገድ ጠየቀ ይህም

ለነርሱ የአክብሮትንና የፍቅርን ስግደት

ሰገደ

ከላይ የተገለጹት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች

የሚያስገነዝቡን ለመላእክት ቅዱሳን ሰዎች

እንዴት አክብረው እንደሰገዱላቸው ነው።

ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ

‹‹የእግዚአብሐርን ቃል የተናገሩአቸሁን

ዋሃቻችሁን አስቡ የኑሮአቸውንም ፍሮ

እየተመለከታችሁ በእምነታቸው

ምሰሉአቸው›› (ዕብ 13፡7) እንዳለው

የቅዱሳን አባቶቻችንና ሕይወት አኗኗር ዛሬ

ለእኛ መመሪያ ሊሆነን ይገባል። እነርሱ

አድርገው የተጠቀሙበትን ሁሉ እኛም

እናደርገዋለን። እነርሱ ለቅዱሳን መላእክት

ያላቸውን ፍቅርና አክብሮት በስግደት

እንደገለጹ እኛም እግዚአብሔር ላከበራቸው

ቅዱሳን መላእክት ፍቅራችንንና አክብሮታችንን
በሥዕላቸው ፊት በመንበርከክ በመስገድ
እንገልጻለን።
መላእክት ቢገለጡም ባይገለጡም ሕልውናቸው
የተረጋገጠ ነውና ክብራቸው ያው ነው።
ምናልባት አንዳንድ ሰዎች ሲገለጡ እንጂ
ካልተገለጡ ሊሰገድላቸው አይገባም ሊሉ
ይችላሉ። በዓይን ዓይቶ በእጅ ዳብሶ ከማመን
ሳያዩ የሚያምኑ ብጹዓን እንደሆኑ ጌታችን
አስተምል (ዮሐ 2 ዐ፦29)።
ስለዚህ እነዚህ ቅዱሳን አባቶች በዓይናቸው
ዓይተው፣ በጆሯቸው ሰምተው ያደረጉትን እና
ያመኑትን ለእኛ በማስተላለፋቸው እኛም
የእነርሱን ዓይን ዓይን አድርገን ማእነርሱ
አይተዋቸው የሰጡትን ክብር እንሰጣቸዋለን።
መገለጣቸውና አለመገለጣቸው በእግዚአብሔር
ዘንድ ያላቸውን ክብር አይጨምረውም
አይቀንሰውምና ክብራቸው አንድ ነው።
ስለዚህ ይሰገድላቸው ዘንድ የሚገባ ከሆነ
ሲገለጡ ሳይገለጡ የሚል ሁኔታ መፈጠር
የለበትም። ለእግዚአብሔር በመንፈስ
የአምልኮት ስግደት እንደምንሰግድ ሁሉ (ዮሐ

4፦24) እግዚአብሔር ባለበት ቦታ ሁሉ
አብረው ለሚገኙት ቅዱሳን መላእክትም የጸጋ
ስግደት በእምነት ማቅረብ ይገባል።
እነርሱም እግዚአብሔር ባለበት ቦታ ሁሉ
አሉና።
ራእ 19፦10 (‹‹አትስገድልኝ››)
አንዳንዶች ተጠራጣሪዎች ደግሞ ለመላእክት
ሲገለጡም ሆነ ሳይገለጡ ምንም ዓይነት ስግደት
አይገባቸውም በማለት ራእ 19፦10
(‹‹አትስገድልኝ››) ላይ ያለውን ይጠቅሳሉ።
በመሠረቱ ይህ ጥቅስ ለመላእክት የጸጋ ስግደት
መስግድ እንደሚገባን እንጂ መስገድ
እንደማይገባን የሚገልጽ አይደለም።
ወንጌላዊውና ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ
ለመልአኩ መስገዱ ሳያውቀው ሳይረዳው
ያደረገው ድርጊት እንዳልሆነ እንድናምን
ማንነቱና ሕይወቱ ያስገነዝበናል።
ምክንያቱም የጥበብ፣ የማስተዋል፣ የዕውቀት
ጸጋን የሚያድል መንፈስ ቅዱስ አድሮበት እያለ
ሳያውቀው አደረገው ብሎ መናገርና ማመን
መንፈስ ቅዱስን እንደ መጽረፍ /መስደብ/
ነው። በመንፈስ ቅዱስ የተቃኘ ሰው

የሚያመልከውንና የሚሠራውን ሁሉ የሚያውቅ
ነው። በተለይ ቅዱስ ዮሐንስ አካል ከሕልውና
ተገልጾለት ምሥጢረ መለኮትን የተናገረ ታላቅ
ሰው ሆኖ ሳለ ትንሿ ጉዳይ ተሰውራው ለመልአኩ
ሳያውቅ ሰግዶ ተግሳጽ ደረሰበት ብሎ ማመን
ሞኝነት ብቻ ሳይሆን ክህደትም ጭምር ነው።
የመንፈስ ቅዱስን ሰላም ማቃለል ነው።
መንፈስ ቅዱስ የሰደበ ደግሞ ኃጢአቱ
አይሠረይለትም። (ማቴ 12፡31-32)።
የመልአኩ አነጋገር ታዲያ እንዴት ይተረጎማል?
መልአኩ ቅዱስ ዮሐንስን አትስገድልኝ ማለቱ
ስለ ሁለት ነገር ነው።
1ኛ, ስለ ትኅትና
ዲያብሎስ ከሥልጣኑ የተሻረው ከክብሩ
የተዋረደው በትዕቢቱ እንደሆነ የታወቀ
ነው። ቅዱሳን መላእክት ግን ትሕትናን
ገንዘብ ያደረጉ በመሆናቸው እንደ ሰይጣን
ስገዱልን የሚሉ አይደሉም። ዳሩ ግን
እግዚአብሔር ይከበሩ ዘንድ ፈቃዱ በመሆኑ
የእግዚአብሔር ሰዎች እንዲወዷቸውና
እንዲያከብ å ቸው አድርጓል። ለዮሐንስ
በሰገደለት ጊዜ አትስገድልኝ ማለቱ

በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ከአምልኮተ

እግዚአብሔር የሚያወጣ ለጣኦት እንደመስገድ

የሚያስቆጥር ሆኖ ሳይሆን መልአኩ ራሱን

በዮሐንስ ፊት ዝቅ ከማድረጉ የተነሣ ስለ

ትሕትና የተናገረው ነው። አንድ ሰው ሌላውን

ሰው አክብሮ እጅ ቢነሣው /ከመቀመጫው ሲነሳና

ሲቀበለው/ ኖር አይገባም እንደሚለው ሁሉ

ማለት ነው። ለዚሁም ማረጋገጫ የሚሆነን

(ለትሕትና የተናገረ መሆኑን) በምዕራፍ 19

የሰጠውን ማስጠንቀቂያ በምዕራፍ 21 ላይ

መድገሙ ነው። ለትሕትና የተናገረው መሆኑን

ያወቀው ዮሐንስ ለመልአኩ ክብር መስጠት

እንዳለበትና መስገድ እንደሚገባው ዐውቆ ድጋሚ

ሲገለጥለት በድጋሚ ሰግዶለታል።

2 ኛ, ስለ ሥልጣነ ክህነት ክብር ሲል

የቤተ ክርስቲያን የአጥቢያ ኮከብ ቅዱስ

ጳውሎስ የካህናትን ሥልጣን አስመልክቶ

ሲያስተምር ካህናት ሰውን ሁሉ እንደሚዳኙ

አታውቁምን? እናንተ ሰውን ሁሉ የምትዳኙ

ከሆናችሁ ይህን ትንሹን ነገር ልትፈርዱ

አይገባችሁምን? የዚህንስ ዓለም ዳኝነት

ተውትና መላእክትን ስንኳ እንድንገዛ

አታውቁምን? (1 ቆሮ 6፡2-3) ብሏል።

ከዚህ ትምህርቱ የምገነዘበው ካህናት

በሥልጣናቸው መላእክትን ስንኳ ሳይቀር

እንደሚያዙ ነው። ይህንንም ከቅዱስ ዮሐንስ

አፈወርቅ ትምህርት እንረዳለን። በ 344

ዓ.ም. በአንጾኪያ ከተማ የተወለደው ሊቁ ቅዱስ

ዮሐንስ አፈወርቅ እምነትንና ፍቅርን፣

ትዕግሥትንና ትሕትናን፣ በአንድነት ገመድ

አስሮ ሕዝቡን ለ 7 ዓመት ወንጌልን ሰብኳል።

በ 387 ዓ.ም በአንጾኪያ ከተማ ፖትርያርክነት

ተሾሞ ሳለ አንድ ጉዳይ ይገጥመዋል።

ንጉሡ አርቃድዮስና ንግሥቲቱ አውዶክያስ ልጅ

እየወለዱ እየሞተባቸው አላድግ ስላላቸው

የዚህን ምክንያት ቢጠይቁ ደግ ሰው ክርስትና

ባያነሣላችሁ ይሆናል ስላሏቸው ከዮሐንስ

አፈወርቅ የበለጠ ደግ ሰው በዘመናችን አለን?

በማለት ሴት ልጅ በወለዱ ጊዜ መጥተህ

ክርስትና አንሣልን ብለው ላኩበት እርሱም

ጥሪውን አክብሮ ሲሆድ በመንገድ

ከእግዚአብሔር ዘንድ ከተላከ መልአክ ጋር

ይገናኛል። የበቃ ነውና ረቂቁን መልአክ

ሊያየው ችሏል። ዮሐንስም መልአኩን <<ወዴት

ትሄዳለህ?›› ብሎ ጠየቀው መልአኩም

ሲመልስለት ‹‹አሁን አንተ የምትሄድባትን

ብላቴና ነፍሷን ከሥጋዋ ለይተህ አምጣ ብሎኝ

የታዘዝኩትን ለመፈጸም ወደዚያ መሄዴ ነው››

ይለዋል። ዮሐንስም ‹‹ቆየኝ በጥምቀት ሀብተ

ውልድና፣ ስመ ክርስትና ከተሰጣት በኋላ

የታዘዝከውን ትፈጽማለህ። እስከዚያው ግን

ከዚሁ አትንቀሳቀስ›› ብሎት በሥልጣነ ክህነቱ

ገዝቶት ሄደ። መልአኩም የዮሐንስን ግዝት

ጠብቆ ባለበት ቆመ። ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ

ልጅቷን ካጠመቃት በኋላ ንግቶት በሌላ መንገድ

ተመለሰ።

የካህናት ሥልጣናቸው የማይናቅ፣ ትእዛዛቸውም

ክብር የሚገባው መሆኑን ስለሚያውቅ ያ መልአክ

ወደ ላይም ወደታችም ሳይል አሥር ዓመት

ከዚያው ሥፍራ ቆሞ ኖረ። አሥር ዓመት

ሲሆናት ለባል ታጨች ያጠመቀካት ብላቴና እነሆ

ለአቅመ ሔዋን፣ ባል ልታገባ ነውና መጥተህ

ባርከህ ስደዳት ብለው ለዮሐንስ አፈወርቅ

ላኩበት። እርሱም በጥሪው መሠረት ከዛሬ

አሥር ዓመት ልጅቱን ሊያጠምቅ ሲሔድ በሄደበት

መንገድ መልአኩን ቆሞ አገኘው። ምነው ከዚህ

ቆመሃል? አለው። መልአኩም ሲመልስለት

የካህናት ማዕረጋቸው የከበረ ነውና መኾ ወዲያ

ወዲህ ያሰኛል። ቃልህን አክብሬ አንተ ቆይ

ካልከኝ ወዲያና ወዲህ ብዬ አላውቅም አለው

ቅዱስ ዮሐንስም በዝንጉዕነቱ ራሱን ወቅሶ

መልአኩን የታዘዘውን ያደርግ ዘንድ

አሰናብቶታል።

ከላይ በተገለጸው ታሪክ ብናይ በፍጥሞ ደሴት

መልአኩ ለዮሐንስ ወንጌላዊ አትስገድልኝ

ማለቱ ዮሐንስ ካህንም ነውና ሥልጣኑ ሊያከብር

እንደሚገባው ለመግለጽ ሽቶ ነው። በክብር

ዮሐንስ ከመልአኩ ይበልጣልና።

የቅዱሳን መላእክት ተራዳይነትና

አማላጅነታቸው አይለየን።አሜን!!

Mazi Adissu

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አሜን ።

✞✞

15/ እንኳን ለሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል መታሰቢያ ክብረ በዓል

በሰላም አደረሳችሁ

✞

☞ቅዱስ ገብርኤል በብሉይ ኪዳን በቅድስና ሕይወት ለተጋውና በገዢዎች ዘንድ የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ ያደረበት ሰው(ዳን 5:11)ተብሎ ለተመሰገነው ለነቢዩ ዳንኤል ማስተዋልንና ጥበብን የሰጠ መልአክ ነበር። ለዚህ ነቢይ እግዚአብሔር አምላክ የሰው ልጆችን ከሰይጣንና ከሞት ባርነት ነጻ ያስተማረው መልአክ ነው።(ዳን.9:21-22)

አሁንም ነቢዩ ዳዊት "አቤቱ እርዳታው ከአንተ ዘንድ የሆነለት በልቡም የላይኛውን መንገድ የሚያስብ ሰው ብፁዕ ነው። በልቅሶ ሸለቆ በወሰንኸቸው ስፍራ የሕግ መምህር በረከትን ይሰጣልና።(መዝ.83:5-6)እንዳለው በቅድስና ሕይወት በመጽናታቸው ምክንያት ቅዱስ ገብርኤል መምህር የሆናቸው ቅዱሳን ብዙዎች ናቸው። የእኛ እውቀት በሰማያት ከትመው ካሉት ቅዱሳን መላእክት እውቀት ጋር ሲነጻጸር እኛን እንደ ሕፃናት ያደርገናል ።

እኛ የእነሱን እውቀት ገንዘባችን የምናደርገው በትንሣኤ ነው። ስለዚህም ቅዱስ ጳውሎስ

"ዛሬ በመስታወት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን ያን ጊዜ ግፊ ለፊት እናያለን። አሁን በከፊል ዕሊ ግን እንደተገለጠልኝ መጠን ሁሉን አውቃለሁ "(1 ቆሮ.13:12)ብሎ አስተማረ። ስለዚህም እውቀታችን የተሟላ እንዲሆንና ሰይጣንን ለመቃወም እንድንበቃ የቅዱሳን መላእክት የእውቀት ድጋፍ በእጅጉ ያስፈልገናል፤ ምክንያቱም ከእኛ ይለቅ ሳጥናኤልን የሚያውቁት እነርሱ ናቸውና።

እንዲረዱን ስለሆነ ጌታችን በእውቀታቸው እኛን እንዲረዱን ለእያንዳንዳችን ጠባቂ መልአክትን ሰጠን።(ማቴ.18:10 ሉቃ .13:6-9

ከመስቀሉ ስር ነው አድራሻዬ with Tigist Mehari and 3 others.

(ትንቢተ ዳንኤል ምዕ. 12)

16/ 1፤ በዚያም ዘመን ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል፤ ሕዝብም ከሆነ ጀምሮ እስከዚያ ዘመን ድረስ እንደ እርሱ ያለ ያልሆነ የመከራ ዘመን ይሆናል፤ በዚያም ዘመን በመጽሐፉ ተጽፎ የተገኘው ሕዝብህ ሁሉ እያንዳንዱ ይድናል።

2፤ በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉቱ ብዙዎች ይነቃሉ፤ እኩሌቶቹ ወደ ዘላለም ሕይወት፥ እኩሌቶቹም ወደ እፍረትና ወደ ዘላለም ጕስቍልና።

3፤ ጥበበኞቹም እንደ ሰማይ ፀዳል፥ ብዙ ሰዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ።

4፤ ዳንኤል ሆይ፥ አንተ ግን እስከ ፍጻሜ ዘመን ድረስ ቃሉን ዝጋ፥ መጽሐፉንም አትም፤ ብዙ ሰዎች ይመረምራሉ፥ እውቀትም ይበዛል።

5፤ እኔም ዳንኤል አየሁ፤ እነሆም፥ ሁለት ሌሎች ቆመው ነበር፥ አንዱ በዚህ በወንዙ ዳር፥ ሌላውም በዚያ በወንዙ ዳር።

6፤ አንዱም ከወንዙ ውኃ በላይ የነበረውን በፍታም የለበሰውን። የዚህ

ድንቅ ፍጻሜ እስከ መቼ ነው? አለው።

7፤ ከወንዙም ውኃ በላይ የነበረው በፍታም የለበሰው ሰው ቀኝና ግራ እጁን ወደ ሰማይ አንሥቶ። ለዘመንና ለዘመናት ለዘመንም እኩሌታ ነው፤ የተቀደሰውም ሕዝብ ኃይል መበተን በተጨረሰ ጊዜ ይህ ሁሉ ይፈጸማል ብሎ ለዘላለም ሕያው ሆኖ በሚኖረው ሲምል ሰማሁ።

8፤ ሰማሁም ነገር ግን አላስተዋልሁም፤ የዚያን ጊዜም። ጌታዬ ሆይ፥ የዚህ ሁሉ ፍጻሜ ምንድር ነው? አልሁ።

9፤ እርሱም እንዲህ አለኝ። ዳንኤል ሆይ፥ ቃሉ እስከ ፍጻሜ ዘመን ድረስ የተዘጋና የታተመ ነውና ሂድ፤

10፤ ብዙ ሰዎች ሰውነታቸውን ያጠራሉ ያነጡማል ይነጥሩማል፤ ክፉዎች ግን ክፋትን ያደርጋሉ፤ ክፉዎችም ሁሉ አያስተውሉም፥ ጥበበኞች ግን ያስተውላሉ።

11፤ የዘወትሩም መሥዋዕት ከቀረ ጀምሮ፥ የጥፋትም ርኩሰት ከቆመ ጀምሮ ሺህ ሁለት መቶ ዘጠና ቀን ይሆናል።

12፤ የሚታገሥ፥ እስከ ሺህ ሦስት መቶ ሠላሳ አምስት ቀንም የሚደርስ ምስጉን ነው።

13፤ አንተ ግን እስከ ፍጻሜው ድረስ ሂድ፤ አንተም ታርፋለህ፥ በቀኑም መጨረሻ በዕጣ ክፍልህ ትቆማለህ።

Tizita Geberkidan added 5 new photos .

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።

17/ እንኳን ለሊቀ መልአክ ቅዱስ ሩፋኤል ዓመታዊ በዓል (ጳጉሜን 3) አደረሳችሁ:: ለዛሬ ይዤላችሁ የቀረብኩት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የቅዱስ ሩፋኤል አጣጣል ምን እንደሚመስል እና በቤተመቅደስ የቅዱስ ሥዕሉን አቀማመጥ ነው።

መግቢያ

ጳጉሜን 3 የመላአክት አለቃ የከበረ መልአክ የቅዱስ ሩፋኤል መታሰቢያ ነው ። ይኸውም ትጉሃን ቅዱሳን ሰማያውያን ከሚሆኑ ከመላአክት አለቆች ከቅዱስ ሚካኤልና ከቅዱስ ገብርኤል ቀጥሎ 3 ተኛ ነው።

ጳጉሜን 3 ለምን የቅዱስ ሩፋኤል በዓል ይከበራል?

በጳጉሜን 3 ዕለት ተዝካሩ መደረጉ ስለ 2 ነገር ነው የመጀመሪያው በዓለ ሢመቱ ስለሆነ ነው።

ዳግመኛም የእስክንድርያው ሊቀጳጳሳት አባ ቴዎፍሎስ መሬት ውስጥ 3 ድስት ሙሉ ወርቅ አግኝቶ በአንዱ በድስት ሙሉ ወርቅ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት አሰርቷል። ከእንዱም አንዲቱ ከእስክንድርያ ውጭ በአለች ደሴት ላይ በቅዱስ ሩፋኤል ስም ቤተክርስቲያን አሰርቶ ስራዋን ጨርሶ እንደዛሬይቱ በአለች ቀን ቀደሳት።

ቅዱስ ሩፋኤልና ዓሣ አንበሪው

ምእመናን ከቤተክርስቲያን ውስጥ እየፀለዩ ሳሉ እንሆ ቤተክርስቲያኒቱ ተንቀጠቀጠች ተናወጠች ታወከች ። በመረመሩም ጊዜ ከባህር አንባሪዎች

በአንዱ ታላቅ ዓሣ አንባሪ ላይ ተሰርታ አገኙዋት። ዓሣ አንባሪውም ከቦታው ሳይንቀሳቀስ ኑሮ ነበር። በላዩ የሰው ሁሉ እግር በበዛና በከበደው ጊዜ ቤተክርስቲያኒቱን ያፈርሳት ዘንድ ሰይጣን አወከው።

ምእመናንና ጳጳሱ ወደ እግዚአብሔር ቢያመለክቱ ቅዱስ ሩፋኤል ተልኮ ፥ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ጸንትህ ቁም ከቦታህም አትንቀሳቀስ ብሎ ዓሣውን በጥር ወጋው። ያን ጊዜም ዓሣ አንባሪው በቦታው ጸንቶ ቆመ አልተንቀሳቀሰም። በዚችም ቤተክርስትያን ብዙ ውስጥ ብዙ ድንቅ ተአምራት ተደረገ።

የዋህ የምህረትና የረድኤት መልአክ ቅዱስ ሩፋኤል ከስራዎቹ አንፃር በተለያየ ስም ይጠራል ለአብነት ያክል

“ፈታሂ ማህጸን” ይባላል። እናቶች ሲወልዱ ምጥ እንዳይበዛባቸዉ የሚራዳ መልአክ ስለሆነ አያሌ ክርስቲያኖች ማርገዛቸዉን ካወቁ ጀምሮ ድርሳኑን በማንበብ መልኩን በመድገም ጠበሉን በመጠጣት ሰዉነታቸዉን በመቀባት ይለምኑታል።እንደ እምነታቸዉ ጽናት ይደረገላቸዋል።

“ዐቃቤ ኖኅቱ ለአምላክ” ይባላል። ሰማያዉያን መዛግብት በእጁ የሚጠበቅ በመሆኑ ።

“መራሔ ፍኖት” ይባላል። ጥቢትን በቀና መንገድ መርቶታልና።

“መላከ ክብካብ” ይባላል። ጥቢያና ሣራን ያጋባ ጋብቻቸዉን የባረከ በመሆኑ።

የቅዱስ ሩፋኤል ሥዕል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን

ቅዱስ ሩፋኤል በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በዓበይት ከሚጠቀሱና በሥዕል ከተገለጡ የሠራቸው ተአምራት መካከል ለጥቢት

ዓይኑን ሲያበራለት፣ ወለተ ራጉኤልን ተቆራኝቷት የነበረውን ጋኔን እንዳስወጣ እና ዓሣ አንበሪውን በመስቀል ባለበት እንዲጸና ሲያደርግ ይሣላል። በስፋት ባይሆንም አንዳንድ ጊዜ ቅዱስ ሩፋኤል በምስለ ፍቁር ወልዳ ሥዕል ላይ ከቅዱስ ሚካኤልና ከቅዱስ ገብርኤል ጋር ተደምሮ ይሣላል።

የቅዱስ ሩፋኤል ሥዕል በቤተመቅድስ አቀማመጥ

ቅዱስ ሩፋኤል በቤተመቅድስ የመቅደሱን በስተደቡብ ምዕራብ የሚገኘውን መግቢያ ላይ ከቅዱስ ሚካኤል ፊርኦንና ሠራዊቱን ሲያሰምጥ ከሚታየው ሥዕል አጠገብ ይሣላል። በዚህ መግቢያ ላይም የሚሣለው ዓሣ አንበሪውን በመስቀሉ ኃይል ሲያቆመውና ካህናተ እግዚአብሔር በቤተክርስቲያኑ ውስጥ እያሉ ይሣላል። ይህም የቤተክርስቲያን ጠባቂነቱን ያመለክታል። የቤተመቅደሱ በር ትልቅ ከሆነ ደግሞ ከላይ ከተገለጸው ጭብጥ በተጨማሪ የጦቢትን ዓይን ሲያበራለት የሚያሳየው ታሪክ ሊጨምር ይችላል።

በዚህ ዕትም ደግሞ በተለያዩ ዘመናት በቤተክርስቲያን ሠዓሊያን ቅዱስ ሩፋኤልን የሣሉትን ሥዕል ከሥር ለአብነት ቀርቧል።

ቅዱስ ሩፋኤል ቆርቆር ማርያም ትግራይ፣ በ 13/14 መ.ክ.ዘ. Rufael 13 or 14 wall painting Qorqor Maryam large

ቅዱስ ሩፋኤል ቆርቆር ማርያም ትግራይ ክልል ውስጥ የሚገኝ አንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኝ ሥዕል። ሥዕሉ ላይ ቅዱስ ሩፋኤል የካህናት ልብስ ለብሶ እና አኪልል ተጎናጽፎ ይታያል። ሥዕሉ በ 13/14 መ.ክ.ዘ. እንደተሣለ ይገመታል።

Rufael dangelat Church of Virgin Mary 17th C.

Rufael dangelat Church of Virgin Mary 17th C.

በዳንግላት በሚገኘው የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ቤተክርስቲያን ውስጥ የመቅደሱ በስተደቡብ ምዕራብ በኩል የሚገኝ የቅዱስ ሩፋኤል ሥዕል። ሥዕሉ የተሣለው የተፈጥሮ ቀላማትን አዋሕደው በመጠቀም በጨርቅ ላይ በ 17 ኛው መ.ክ.ዘ. ነበር።

ቅዱስ ሩፋኤል የምስለ ፍቁር ወልዳ ሥዕል ላይ ከቅዱስ ሚካኤልና ከቅዱስ ገብርኤል ጋር። Rafael with Micheal and Gabriel in the Icon Virgin Mary 20 C. large

ቅዱስ ሩፋኤል የምስለ ፍቁር ወልዳ ሥዕል ላይ ከቅዱስ ሚካኤልና ከቅዱስ ገብርኤል ጋር። ሥዕሉ የገበታ ሥዕል ሲሆን የተሠራው በ 20 ኛው መ.ክ.ዘ. ነው።

ሊቀ መልአክ ቅዱስ ሩፋኤል ዓሣ አንበሪውን በመስቀል ባለበት እንዲጸና ሲያደርግ 20 መ.ክ.ዘ.

ቅዱስ ሩፋኤል ዓሣ አንበሪውን በመስቀል ባለበት እንዲጸና ሲያደርግ። ሥዕሉ የተሠራው በ 20 ኛው መ.ክ.ዘ. በመቐለ አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ ቤተክርስቲያን ነው።

*** ማሳሰቢያ ከላይ የተገለጡት የቅዱስ ሩፋኤል ሥዕሎች እና የአቀማመጥ ሐይት ብቻ እንዳልሆነ አንባቢው እንዲገነዘብ እጠይቃለሁ። ***

የከበረ የመላእክት አለቃ የሩፋኤል ይቅርታ ልመናውና በረከቱ ከእኛ ጋር ይኑር ለዘለዓለሙ አሜን።

ረድኤተ እግዚአብሔር አይለየን።

Diacon Ankets Tekola

Rodas Tadese Abebe

“አነ ውእቱ ገብርኤል ዘእቀውም ቅድመ እግዚአብሔር” (እኔ 18/ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ) (ሉቃ 1፡19)

...ከመጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ታደሰ...

ቅዱስ ገብርኤል ከሊቃነ መላእክት አንዱ ሲኾን፤ የሚኖርበት ሰማይም ኢዮር ሲባል አርባብ በተባለ ነገድ ላይ የተሾመ ከሰባቱ ሊቃነ መላእክት ቀጥሩ በኹለተኛነት የሚገኝ ነው፤ ይኽ መልአክ በባቢሎን በእሳት ውስጥ የተወረወሩትን ሦስቱን ሕፃናት የታደገ መልአክ ሲኾን በተለይም ለቅድስት ድንግል ማርያም የአምላክን ሰው መኾን ያበሠረ መልአክ ስለኾነ መጋቤ ሐዲስ በመባል ይታወቃል። ሦስቱ ሕጻናትን እንዴት እንደተራዳ ስናየው፤ ነቢዩ ዳንኤል ለንጉሡ ለናቡከደነጾር ሕልሙን ከተረጐመለት በኋላ ዳንኤልንና ሠለስቱ ደቂቅን በባቢሎን አውራጃ ላይ ከፍተኛ ሹመትን በየደረጃቸው ሾሟቸዋል (ዳን ፪፥፵፰-፵፱)።

ኾኖም ግን ናቡከደነጾር ቁመቱ ስሳ ክንድ ወርዱ ስድስት ክንድ የኾነውን የወርቁን ምስል አሠርቶ በባቢሎን አውራጃ በዱራ ሜዳ ላይ በማቆም ኹሉም ላቆመው ምስል ምረቃ ተሰብስበው ሳሉ፤ ዐዋጅ ነጋሪው የዘፈን ድምፅ ሕዝቡ ሲሰሙ ንጉሡ ላቆመው ምስል ተደፍተው እንዲሰግዱ

ትእዛዝን የማይቀበሉ ግን በሚነድደው እሳት እቶን እንደሚጣሉ ሲናገር ሕዝቡም አሕዛቡም ለምስሉ ይሰግዱ ይረበረቡ ዝመር (ዳን ፫፥፭-፯)።

ሦስቱ ሕፃናት አናንያ ዘዛርያ ሚሳኤል ግን አንሰግድም በማለታቸው "እሉ እደው ዘሜምኮሙ ለግብረ በሐውርተ ባቢሎን አበዩ ሰጊደ ለምስል ዘወርቅ ዘገበርከ" በባቢሎን አውራጃ ሥራ ላይ የሾምካቸው እነዚኽ ሰዎች ወንዶች ላቆምኸው ምስል አይሰግዱም በማለት ነገሩት፤ ናቡከደነጾርም በብስጭትና በቁጣ እንዲመጡ በማዘዙ፤ መጥተው ከፊቱ ሲቆሙ "ላቆምኹት ለወርቁ ምስል አለመስገዳችኑ እውነት ነውን? ባትሰግዱ በሚነድድ እሳት እቶን ውስጥ ትጣላላችኑ፤ ከእጄስ የሚያድናችኑ አምላክ ማን ነው?" በማለት ሲናገራቸው የሚያመልኩት አምላክ ከሚነድደው እሳት ሊያድናቸው እንደሚችል ገለጹለት፤ ርሱም በቁጣ የእቶኑ እሳት ከሚነደው ይልቅ ሰባት እጥፍ ማለት ፸፯ ክንድ አድርገው እንዲያነዱ በማዘዝ አናንያ፣ አዛርያ፣ ሚሳኤል፣ ታሥረው እንዲጣሉ በሰራዊቱ ውስጥ ላሉት ጎያላን መመሪያ ስላስተላለፈ፤ ወርዋሪዎቹም ከሰናፊላቸውና ከቀሚሳቸው ከመጐናጸፊያቸው ጋር በእሳቱ ላይ ሲጥሏቸው ከወላፈኑ ከፍተኛነት የተነሣ ወታደሮቹ ተቃጥለዋል (ዳን ፫፥፻፫-፳፫)።

ያን ጊዜ "ወወረደ መልአከ እግዚአብሔር ወዘበጦ ለነበልባለ እሳት ወረሰዮ ከመ ነፋስ ቆሪር ዘጊዜ ጽባሕ" ይላል መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ወርዶ በበትረ ብርሃን ቢመታው እንዳረረ ውርጭ ኾኗል፤ ያን ጊዜ ወአንሰሶሰዉ ማእከለ እሳት ወአእኰቱ እግዚአብሔርሀ ወባረክዎ ይላል በእሳቱ ጕድጓድ መኻከልም በመመላለስ እግዚአብሔርንም ፈጽመው

አመስግነውታል (መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ ቁ ፮)።
ይኽም ከእሳቱ መኻከል ሳሉ የተገለጸላቸው አስደናቂ ምስጋና ልዩ የኾነ የነገረ ሥጋዌ ምስጢርን የያዘ እንደኾነ የነገረ ነቢያት ሊቃውንት አስተምረዋል፤ ይኸውም በእሳቱ መኻከል ኾነው ለስድስት ጊዜ ብቻ “ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም” (የአባቶቻችን ፈጣሪ እግዚአብሔር ይመስገን፤ የተመሰገነ ነው፤ ለዘለዓለሙም የከበረ ነው) በማለት ካመሰገኑ በኋላ (መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ ቁ ፷፯-፸፪) ለሠላሳ ሦስት ጊዜ በመደጋገም “ይባርክዎ ኵሉ ግብረ እግዚእ ለእግዚአብሔር ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም” (እግዚአብሔር የፈጠራቸው ፍጥረቶች ኹሉ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል፤ ርሱ የተመሰገነ ነው ለዘላለሙም ከፍ ከፍ ያለ ነው) እያሉ “ያመሰግኑታልን” ለ ፸፫ ጊዜ ያኽል ተናግረዋል (መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ ቁ ፸፫-፹፭)።
በሊቃውንቱ ትንታኔ ሠለስቱ ደቂቅ ስድስት ጊዜ መላልሰው መናገራቸው ከ፯፪ ዘመናት በኋላ ምስጉን የኾነው የባሕርይ አምላክ ከሰማየ ሰማያት መውረዱን ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱን ማጠየቃቸው ሲኾን፤ ከዚያው ቀጥለው ደግሞ ሠላሳ ሦስት ጊዜ “ያመሰግኑታል” እያሉ ቃሉን ደጋግመው ማለታቸው፤ ምስጉን የኾነው አምላክ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከተወለደ በኋላ ሠላሳ ሦስት ዓመት በዚኽ ዓለም የሚኖር እንደኾነ ተገልጾላቸው የተናገሩ መኾኑን አስተምረዋል። ይኽነንም ምስጢር ቀደምት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ሲተነትኑ

“ወኢለከፎሙ እቶነ እሳት ግሙራ ወረሰዮ ለእቶነ እሳት ከመ ማይ ቆሪር በጊዜ ጽባሕ ወበውእቱ ሰዓት ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር እንዘ ይብሉ ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም፤ ወተነበዩ ስድስተ ጊዜያተ ለአጠይቆ ከመ እምድኅረ ስድስቱ ምእት ዓመት ይትወለድ ክርስቶስ። ወእምድኅሬሁ ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር እንዘ ይብሉ ይባርክዎ ኩሉ ግብረ እግዚእ ለእግዚአብሔር ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም ዘንተኒ ተነበዩ ሠላሳ ወሠለስተ ጊዜያተ ለአጠይቆ ከመ እምድኅረ ተወልደ ክርስቶስ ይነብር ውስተ ዓለም ሠላሳ ወሠለስተ ጊዜያተ ለአጠይቆ” (የሚነድደው እሳት ፈጽሞ አልነካቸውም የሚነድደውን እሳት እንደ ውሃ የቀዘቀዘ አድርጎታልና፤ በዚያን ሰዓት እግዚአብሔርን እንዲኽ እያሉ አመሰገኑት፤ የአባቶቻችን ፈጣሪ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን፤ ለዘለዓለሙ ክቡር ምስጉን ነውና፤ እንዲኽ እያሉ ስድስት ጊዜ ተናገሩ፤ ከስድስት መቶ ዘመን በኋላ ክርስቶስ እንዲወለድ ለማጠየቅ፤ ከዚኽም በኋላ እንዲኽ እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ፤ እግዚአብሔርን ፍጥረቱ ኹሉ ያመሰግኑታል ክቡር ምስጉን ነውና ለዘላለሙ ይክበር ይመስገን እያሉ፤ ይኽንንም ሠላሳ ሦስት ጊዜ ተናገሩ፤ ክርስቶስ ከተወለደ በኋላ በዚኽ ዓለም ሠላሳ ሦስት ዓመት እንዲኖር ለማጠየቅ) በማለት ልዩዉን ምስጢር አስተምረውናል። ንጉሡ ናቡከደነጾርም ባለመቃጠላቸውና በእሳት ውስጥ ኾነው በማመስገናቸው ተደንቆ አማካሪዎቹን “ሦስት ሰዎች አስረን በእሳት ውስጥ ጥለን አልነበረም? እነሆ እኔ የተፈቱ በእሳቱም መኻከል የሚመላለሱ አራት ሰዎች አያለኁ፤ የአራተኛውም መልክ የአማልክትን

ልጅ ይመስላል" በማለት፤ ስማቸውን ጠርቶ እናንተ የልዑል አምላክ ባሪያዎች ውጡ ሲላቸው ሦስቱ ሕፃናት ከእሳቱ ወጡ፤ ያን ጊዜ መሳፍንቱ ኹሉ የራሳቸው ጠጕር እንዳልተቃጠለ፤ ሰናፊላቸው እንዳልተለወጠ፤ የእሳቱ ሽታ እንኳ እንዳልደረሰባቸው አዩ።

ያን ጊዜ ንጉሡ "በርሱ የታመኑ ባሪያዎቹን ያዳነ የሲድራቅ የሚሳቅ የአብደናጎም አምላክ ይባረክ" በማለት ምስጋናውን አቅርቧል (ዳን ፫፥፺፭-፹)። እነዚኽ ሦስቱ ሕፃናት አናንያ፣ አዛርያ፣ ሚሳኤል በእቶነ እሳት

ቢጣሉም እንኳ፣ ስለ እምነታቸው ብርታት ምስጢር ተገልጾላቸው በሺኛ ዘመን አምላክ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ፴፫ ዓመት በዚኽ ዓለም ኖሮ ነፍሳትን ከሲኦል እሳት ነጻ እንደሚያወጣ የተገለጸላቸውን ልዩ ምስጋና፣ ዛሬ ኹላችን በቃል ኪዳኗና በምልጃዋ ከገሃነመ እሳት ከምንድንባት ከምትራራልን እናት ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ፈጽሞታና፤ ታላቁ ሊቅ አባ ጊዮርጊስ በኖኅተ ብርሃን የነገረ ማርያም መጽሐፉ ላይ "መሃኪቶሙ እምውስተ እቶነ እሳት ለአናንያ ወአዛርያ ወሚሳኤል በእደ ቅዱስ ገብርኤል" (በቅዱስ ገብርኤል እጅ አናንያን፣ አዛርያን፣ ሚሳኤልን በእቶን እሳት ውስጥ የራራሺላቸው አንቺ ነሽ) በማለት ምስጢሩን እንደወርቅ አንከብሎ እንደ ሸማ ጠቅልሎ ገልጾታል።

ነገረ ማርያም በብሉይ ኪዳን ክፍል 2 ከሚለው መጽሐፌ የተወሰደ

የመልአኩ በረከት ይደርብን

Micah Alaye celebrating 19 St Gabriel "ገብርኤልን" ብያለሁ!!!

ቅዱስ ገብርኤል

19/ ቅዱሳን መላእክት እግዚአብሔር በእለተ እሁድ

ከፈጠራቸው ፍጥረታት ውስጥ የሚቆጠሩ ሲሆኑ ኩፋሌ

2 ፥ 6-8 ተፈጥሮ አቸውም ከምንም የተፈጠሩ ወይም

ለመፈጠራቸው ምንም ምክንያት የሆነ ነገር

የሌላቸውናቸው። አፈጣጠራቸውም በአንድ ጊዜ የተፈጠሩ

በየጊዜው የማይባዙ ሲሆን ነባብያን(የሚናገሩ)፣

ለባውያን(የሚያስቡ)፣ ሕያዋን(ሕይወት ያላቸው) እና

በፀጋቸው ሞት የለባቸው;ያልንም ናቸው

፤ቁጥራቸውምየማይወሰን እናበፈጣሪ ህሊና ብቻ የታወቀ

የተወሰነ ነው።

ከላይ እንደተገለፀው የቅዱሳን መላዕክት ቁጥር

የማይወሰን ቢሆንም በአምላክ ሕሊና የሚታወቀው

ባዛታቸው በአስር ነገድ በአስር የነጋድ አለቃ ይከፈላሉ።

እኛምከአስሩ የመላዕክት ነገድ አለቆችም ውስጥ አንዱ

የሆነው መላክ ቅዱስ ገብርኤል ዛሬም ስለመለአኩ አጭር

ነገር እና በዛሬዋ እለት ያደረገውን የተራዳኢነት

አገልግሎቱን በጥቂቱ እናያለን

ቅዱስ ገብርኤል

ገብርኤል ማለት በዕብራይስጥ ‹‹ኃይል የእግዚአብሔር ነው›› ማለት ነው።/Holman Bible Dictionary/ መጽሐፈ ሄኖክ ‹‹በአበቦች ላይ በገነትም ባሉ ጻድቃን ላይ በኪሩቤልም ላይ የተሾመ ከከበሩ መላእክት አንዱ ገብርኤል ነው›› ይለዋል።ሄኖክ 6፥7።በሌላም በኩል በዚህ ዓለም የሚኖሩ በመላእክት ጌታበኢየሱስ ክርስቶስም አምነው ስለሚለምኑ ሰዎች የሚማልድ መሆኑን ይገልጻል።ሄኖክ 10፥7።ለነቢዩ ዳንኤልም ያጽናናውና ራእዩን ይተረጉምለት የነበረው ቅዱስ ገብርኤል ነው። ‹‹አስቀድሞ በራእይ አይቼው የነበረው ሰው ገብርኤል እነሆ እየበረረ መጣ። በማታም መሥዋዕት ጊዜ ዳሰሰኝ። አስተማረኝም።›› ትን. ዳን. 9፥22፤ ትን. ዳን. 8፥15።ሌላው ማንዘነጋው ቅዱስ ገብርኤል አብሣሪ መላእክ ነው። ለዘካርያስ የመጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስን መወለድ ለእመቤታችን የመድኃኔዓለምን መወለድ ያበሠረ እርሱ ነው።ሉቃ. 1፥8-9፣ 26-56። ይህ መለአክ ከቅዱስ ሚካኤል ጋርም በመሆን ሰዶምን ያጠፋ/ዘፍ. 18፥2/፣ እመቤታችንን ይዞ ወደ ግብጽ የሸሸ፣ ሄሮድስ ከሞተም በኋላ ወደ ሀገሩ እንዲመለስ ለዮሴፍ የተናገረ፣በጉዞአቸውም ጠባቂ የነበረ፣ይህ ቅዱስ ገብርኤል ነው። ማቴ.2፥13-19።ለጣዖት አንሰግድም በማለታቸው በናቡከደነፆር ትዕዛዝ ወደ እሳት የተጣሉትን

ሠለስቱ ደቂቅን ከእሳት ያወጣቸው ነቢዩ ዳንኤል<<ሰው>>
በማለት እንደገለጸው ሁሉ ናቡከደነፆርም <<የአማልክት
ልጅ>> በማለት የተናገረለት ይህ ቅዱስ ገብርኤል ነው።
ትን. ዳን. 3፥24-27።
ዲያብሎስ ም በመላእክት በሰማያት ሁከት ባስነሣ ጊዜ
<<አምላካችንን እስክናውቅ ድረስ ጸንታችሁ ቁሙ>>
በማለት መላእክትን ያረጋጋ፣ ነቢዩ ዳንኤልም በአንበሳ
ጉድጓድ ውስጥ በተጣለ ጊዜፈጥኖ በመድረስ የአናብስቱን
አፍ የዘጋ ቅዱስ ገብርኤል ነው/ ትን. ዳን. 6፥23/
ክብሩም እጂግ ገናና ሀያል ነው ነቢዩ ዳንኤል
“ዐይኖቼንም አነሣሁ” ካለ በኋላ
አስከትሎ “እነሆም በፍታ የለበሰውን ጥሩም የአፈዝን
ወርቅ በወገቡ ላይ የታጠቀውን ሰው አየሁ። አካሉም
እንደ ቢረሌ ይመስል ነበር፤ ፊቱም እንደ መብረቅ አምሳያ
ነበረ፤ ዐይኖቹም እንደሚንበለበል ፋና፣ ክንዶቹና
እግሮቹም እንደ ጋለ ናስ፣ የቃሉም ድምፅ እንደ ብዙ
ሕዝብ ድምፅ ነበረ።... ይህንም ታላቅ ራእይ አየሁ፤
ኀይልም አልቀረልኝም፤ ክብሬም ወደ ውርደት
ተለወጠብኝ ኀይልም አጣሁ። የቃሉንም ድምፅ ሰማሁ፤
የቃሉን ድምፅ በሰማሁ ጊዜ ደንግጬ በምደር ላይ
በግምባሬ ተደፋሁ” ዳን.10፥5-9 እንዲል
ነቢዩ ዳንኤል እንዲህ ብሎ የተናገረው የመላእክት አለቃ

የቅዱስ ገብርኤልን አስፈሪ ግርማ በተመለከተ ጊዜ ነበር።

የቅዱስ ገብርኤል ምልጃና በረከት አይለየን!!!

ወስብሀት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር!!!

@Micah Alaye

Tsion Berhanu.

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አሜን

20/ እንኳን ለመልአኩ ለቅዱስ ሚካኤል ክብረ በዓለ በሰላም አደረሳችሁ

አሜን አሜን አሜን

(መልክአ ሚካኤል)

ለዝክረ ስምክ፦ሚካኤል ሆይ የያሬድ ልጅ ጌኖክ እንደጻፈው ከልዑል ስምአጠራርህ ሰላም እላለሁ የእግዚአብሔር የምክሩ አበጋዝ ሆይ የተቸገሩትን የተጨነቁትን ዘወትር እንደምትረዳቸው ሁሉ እኔንም ለመርዳት ክንፍህን ዘርግተህ ፈጥነህ ድረስልኝ።

ለስእረተ ርእስከ፦ሚካኤል ሆይ ከፈጣሪህ በቀር ስነ ባህርዩን ማንም

ተመራምሮ ለማይደርስበት ነበልባላዊ ስርአት ርእስህ ሰላም እላለሁ የእግዚአብሔር ባለሟል ሆይ በእግዚአብሔር ፊት በጉ መዓዛ ያለውን መስዋዕት የምታሳርግ አንተ ሚካኤል ነህና ከኀዘንና ከለቅሶ እርጅና እንዳይጫነኝ ሰውነቴ ባዘነችና በተከዘች ጊዜ ልቦናዬን ታረጋጋት ዘንድ ፈጥንህ ድረስላት።

ለርእስከ፦ሚካኤል ሆይ መብረቅን ለተጎናፀፈ መልአካዊ ረቂቅ ርእስህ ሰላም እላለሁ ተፈጥርአቸው ከእሳት የሆነ የሰማያውያን የመላእክት ሠራዊት አለቃቸው የምትሆን ሚካኤል ሆይ በኃጢአት ተሠናክዬ ወድቄ እንዳልፍገመገም አንተን ድጋፍ አድርጌያለሁና ፍጹም የማዳንህ ትድግና በኔ ላይ ትገልጽ ዘንድ በስተቀኜ ቁመህ አለሁልህ በለኝ እንጂ በሩቅ ሆነህ አትመልከተኝ።

ለገጽከ፦ሚካኤል ሆይ መሬት እና ውሃ ያልተቀላቀለበት ከንፋስና ከእሳት ብቻ ለተፈጠረው መልአካዊ ገፅታህ ሰላም እላለሁ የምህረት መልአክ ሆይ የሊባኖስ ዛፎች በአዕፁቃቸው ታጅበው በልምላምያቸው አሸብርቀው እንደታዩ ልመናዬን በማቀርብበት ጊዜ ሁሉ መጭውን ዘመኔን በክንፈ ረድኤትህ ተንከባክበህ በቸርነት ጌጥ አስጊጠኝ።

ለቀራንብቲከ፦ሚካኤል ሆይ እንቅስቃሴያቸው የቸርነት የየዋህነት ለሆነ ቀራንብትህ ሰላም እላለሁ የእግዚአብሔር የቸርነቱ ጉዳይ አስፈጻሚ ሚካኤል ሆይ ችግረኛን ለመርዳት በሁሉ ቦታ የምትገኝ አንተ ነህና የተለመደውን ቸርነትህን በልቤ አውጣለሁ አወርዳለሁ ስለዚህም ትድግናህን ተስፋ አደርጋለሁ።

ለአዕይንቲከ፦ሚካኤል ሆይ ለሰው ልጅ ይቅርታን ለማስገኘት ወደ ልዑል

እግዚአብሔር አሸቅበው ለሚማልዱ ዐይኖችህ ሰላምታ ይገባል ሚካኤል ሆይ በጠላት ተማርከው ለሚጨነቁትና ለሚሰቃዩት ዋስ ጠበቃቸው አንተ ነህና በኔ ላይ የሚተበትቡትን የጠላቶቼን የምክር መረብ በጣጥሰህ ጣልልኝ ነፍሴንም ሥጋየንም ለአንተ አደራ ሰጥቻለሁና።

ለአእዛኒከ፦ሚካኤል ሆይ የችግረኛውን ሁሉ ጽሎት ፈጥነው ለሚሰሙ ጆሮዎችህ ሰላምታይገባል የይቅርታ መልአክ ሆይ ችግሬን አቅልልኝ ጭንቀቴንም አስወግድልኝ ምክርን ትለግሰኝ ዘንድ ጥበብንም ታስተምረኝ ዘንድ አባት እንዳደረግሁህ አንትም ልጅ አድርገኝ።

ለመላትሒከ፦ሚካኤል ሆይ ፈጽሞ የሚያንጸባርቅ የፈገግታ የሽቱ ጠል ለረበረባቸው ጉንጮችህ ሰላምታ ይገባል መሰልቸት የሌለብህ መልአክ ሆይ የተለመደው ቸርነትህን አታጓድልብኝ በችግሬ ጊዜ በትእምርተ መስቀል እዴን አመሳቅዬ በምጸልይበት ጊዜ ትረዳኝ ዘንድ ፈጥነህ ድረስልኝ እንጂ።

ለአእናፊከ፦ሚካኤል ሆይ ካህናተ ሰማይ ሱራፌል ከአንተ ጋር መስዋት በሚያቀርቡ ጊዜ የጽርሐ አርያምን መዓዛ ለተሞሉ አእናፍህ ሰላምታይገባል ቸር ጠባቂ መልአክ ሆይ የነገደ እሥራኤል/ያዕቆብ/ጠባቂ አንተ ነህና ጓደኞችህ መላአክትን እኔን አገልጋይህን ኑ ወዳጄን ጎብኙ ብልህ ጋብዛቸው በአንዱ ፍቅር ሌላው ሁሉ ይሳባልና።

ለከናፍሪከ፦ሚካኤል ሆይ የሰማያውያን የንጉስ ክርስቶስን የምስጋና ቃል ከመናገር ቸልታና ዝምታ ለሌለባቸው ከናፍርህ ሰላምታ ይገባል ተወዳጁ መልአክ ሆይ የምስጋናህ ድምጽ ቃና ያማረ የተወደደ ነውና የውዳሴህ መታሰብያ የወርቅ ማርዳ ይሁንኝ ጽንዓ ፍቅርህ ከማር ከወተት ይልቅ ጥሞኛል።

ለአፋከ፦ዳኒኤል በእምሳለ አናብስት ምሳሌ ያየውን ስውሩን ራእይ አብራርቶና ግልጥልጥ አድርጎ ለተረጎመለት አንደበትህ ሰላምታ ይገባል የሰላም መልአክ ሆይ የምስጋናን መሥዋት የምታዘጋጅ እንተ ነህና ጠላት ዲያብሎስ ተረማምዶ በእደ ፃዕር ሞት እንዳያፍነኝ በአፌ ላይ ጥበቃህን አጠንክር።አሜን አሜን አሜን

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

Nardos Gezawu

ቅዱስ ሚካኤል

21/ ቅዱስ ማለት ልዩ፣ ክቡር ማለት ነው፤ ሚካኤል ማለት ደግሞ «መኑ ከመ አምላክ፣ እንደ እግዚአብሔር ያለ ማነው?» ማለት ነው። ሚካኤል የሚለው ስም ቃሉ የዕብራይስጥ ነው፤ ሚ - የሚለው «መኑ» ማለት ነው፣ ካ - የሚለው «ከመ» ማለት ሲሆን፣ ኤል - ማለት ደግሞ «አምላክ» ማለት ነው። ይህን ማለትም የቅዱስ ሚካኤልን ስም በጠራን ቁጥር የምንመሰክረው ስለ እግዚአብሔር ነው፤ በመሆኑም እግዚአብሔርን በባሕርይ የሚመስለው፣ በሥልጣንም የሚተካከለው፣ በምድርም በሰማይም

እንደሌለ የሚናገር ልዩ፥ ክቡር ስም ነው። የነቢያት አለቃ ሙሴ ባሕረ ኤርትራን ለሁለት ከፍሎ ሕዝቡን ያሻገረለትንና ፈርዖንን ከነሠራዊቱ ያሰጠመለትን አምላክ እግዚአብሔርን በመዝሙር ሲያመሰግን፥ «አቤቱ በአማልክት መካከል (በስም አማልክት ከሚባሉ፥ በስመ አማልክት ከሚጠሩ፥ አንድም አማልክት ዘበጸጋ ከተባሉ ከነቢያት ከካህናት መካከል) አንተን የሚመስል ማነው? በቅዱሳንም ዘንድ እንደ አንተ የከበረ ማነው?» ብሏል። ዘጸ ፲፭፥፲፩። ቅዱስ ዳዊትም፦ «አቤቱ፥ ከአማልክት የሚመስልህ የለም፤» ብሏል። መዝ ፹፭፥፰።

፩፥፩፦ «ስሜ ድንቅ ነውና ለምን ትጠይቃለህ?» መሳ ፲፫፥፲፯

የእስራኤል ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ክፉ በመሥራታቸው፥ እግዚአብሔር በፍልስጥኤማውያን እጅ ለአርባ ዓመት አሳልፎ ሰጥቷቸው ነበር.። በዚህ ዘመን ከዳን ወገን ማኑሄ የሚባል አንድ ሰው ነበረ፥ ሚስቱም መካን ስለነበረች ልጅ አልወለደችም ነበር። የእግዚአብሔር መልአክ ተገልጦ እንደምትፀንስ፥ ወንድ ልጅም እንደምትወልድ፥ ልጁም ከእናቱ ማኅፀን ጀምሮ ለእግዚአብሔር የተለየ ናዝራዊ እንደሚሆን ነገራት። የሚያሰክር መጠጥ እንዳትጠጣ፥ የረከሰም ነገር እንዳትበላ፥ በልጁም ራስ ላይ ምላጭ እንዳይደርስ (ፀጉሩን እንዳትላጨው) አስጠነቀቃት። እርሷም ተመልሳ የሆነውን ሁሉ ለባሏ ነገረችው፤ «የእግዚአብሔር ሰው ወደ እኔ መጣ፥ መልኩም እንደ እግዚአብሔር መልአክ እጅግ የሚያስደነግጥ ነበረ፤ ከወዴትም እንደመጣ ጠየቅሁት፥ እርሱም ስሙን አልነገረኝም፤» አለችው።

ማኑሄም፥ «ጌታ ሆይ፥ ወደ እኛ የላክኸው የእግዚአብሔር ሰው እባክህ

እንደገና ወደ እኛ ይምጣ፤ ለሚወለደውም ልጅ ምን እንደምናደርግ ያስገንዝበን፤» ብሎ ወደ እግዚአብሔር ለመነ። እግዚአብሔርም የማኑሄን ቃል ሰማ፤ የእግዚአብሔርም መልአክ በእርሻ ውስጥ ሳለች እንደገና ወደ ሴቲቱ መጣ፥ እርሷም ፈጥና ባሏን ጠራችው፥ «እነሆ፥ አስቀድሞ ወደ እኔ የመጣው ያ ሰው ደግሞ ተገለጠልኝ፤» ብላ ነገረችው። እርሱም፦ «ከሚስቴ ጋር የተነጋገርህ አንተ ነህን?» ብሎ ቢጠይቀው «እኔ ነኝ፤» ሲል መለሰለት። ማኑሄም፦ «እነሆ ቃልህ በደረሰ ጊዜ የልጁ ነገር፥ ግብሩስ ምንድነው?» ብሎ ዳግመኛ ጠየቀ። መልአኩም ለሴቲቱ ነግሯት የነበረውን ሁሉ መልሶ ነገረው። ማኑሄ ለመልአኩ የፍየል ጠቦት ለማዘጋጀት ቢፈልግም፦ «አንተ የግድ ብትለኝ እህልህን አልበላም፥ የሚቃጠለውንም መሥዋዕት ብታደርግ ለእግዚአብሔር አቅርብ፤» አለው። ምክንያቱም ቅዱሳን መላእክት ቅድሚያ የሚሰጡት ለእግዚአብሔር ክብር ነው። እነርሱን ግን እግዚአብሔር ራሱ እንደሚያከብራቸውእንደሚያ

ስከብራቸውም ያውቃሉ።

ማኑሄ የተገለጠላቸው የእግዚአብሔር መልአክ እንደሆነ አላወቀም፥ ሚስቱም አላወቀችም። በመሆኑም፦ «ነገርህ በደረሰ ጊዜ እንድናከብርህ ስምህ ማን ነው?» በማለት ጠየቀው። የእግዚአብሔርም መልአክ፥ «ስሜ ድንቅ ነው፥ ለምን ትጠይቃለህ?» ብሎታል። ማኑሄም የፍየሉን ጠቦትና የእህሉን ቍርባን በድንጋይ ላይ ለእግዚአብሔር አቀረበ። መልአኩም ተአምራት አደረገ፥ ማኑሄና ሚስቱም ይመለከቱ ነበር። ነበልባሉም ከመሠዊያው ላይ ወደ ሰማይ በወጣ ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ በመሠዊያው ነበልባል ውስጥ ወደ ሰማይ ዐረገ፥ ማኑሄና ሚስቱም

ተመለከቱ፥ በምድርም በግንባራቸው ወደቁ። (ሰገዱለት)። ይህ መልካም የምሥራችን የተናገረ፥ የተለያዩ ተአምራትን ያደረገ፥ መሥዋዕታቸውንም ወደ ሰማይ ያሳረገ፥ የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ሚካኤል ነው። ሚካኤል ማለት በሁለተኛ ትርጉሙ «የእግዚአብሔር ነገሩ ዕፁብ ድንቅ ነው፤» ማለት ነውና። መሳ ፲፫፥፩-፳። በዚህም የስሙ ትርጓሜ ነገረ እግዚአብሔር መሆኑን እንረዳለን።

፩፥፪- የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ፤ ኢያ ፭፥፲፬

ከነቢያት አለቃ ከሙሴ በኋላ በእርሱ እግር ተተክቶ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የመራው ኢያሱ ነው። የመረጠውም ሰው ሳይሆን እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔርም፦ «በሕይወትህ ዘመን ሁሉ የሚቋቋምህ የለም፤ ከሙሴ ጋር እንደነበርሁ እንዲሁ ከአንተ ጋር እሆናለሁ፥ አልጥልህም፥ ቸልም አልልህም፤» ብሎታል። ኢያ ፩፥፭። ይህ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የሆነለት ታላቅ ሰው ኢያሱ የቅዱሳን መላእክት ተራዳኢነት አስፈልጎታል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ለመሆኑ ምልክቱ ቅዱሳን መላእክት ናቸውና። እግዚአብሔር ባለበት ቅዱሳን መላእክት አሉ፥ ቅዱሳን መላእክትም ባሉበት እግዚአብሔር አለ። ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደባት ሌሊት የምሥራቹን «እነሆ፥ ለእናንተና ለሕዝቡ ሁሉ ደስታ የሚሆን ታላቅ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ፤ እነሆ፥ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት ተወልዶላችኋል፤ ይኸውም ቡሩክ ጌታ ክርስቶስ ነው።» በማለት ለእረኞች የነገሯቸው ቅዱሳን መላእክት ናቸው። እረኞቹም፦ «እስከ ቤተልሔም እንሂድ፥ እግዚአብሔርም የገለጠልንን ይህን ነገር እንወቅ፥ አሉ።» ሉቃ ፪፥፮-፲፭።

በዚህም ቅዱሳን መላእክት የገለጡላቸውን ምሥጢር እግዚአብሔር ገለጠልን ብለዋል።

ኢያሱ ወልደ ነዌ፥ ሕዝቡን እየመራ በኢያሪኮ አጠገብ ሳለ ዐይኑን አንሥቶ ቢመለከት እነሆም የተመዘዘ ሰይፍ በእጁ የያዘ ሰው በፊቱ ቆሞ አየ። ወደ እርሱም ቀርቦ «ከእኛ ወገን ወይስ ከጠላቶቻችን ወገን ነህን?» አለው። እርሱም «እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ነኝ፤ አሁንም ወደ አንተ መጥቻለሁ፤» ብሎታል። ኢያ ፭፥፲፫-፲፭። የእግዚአብሔር ሠራዊት የሚባሉት ቅዱሳን መላእክት ናቸው። «ያዕቆብም መንገዱን ሄደ፥ በዓይኖቹም የእግዚአብሔርን ሠራዊት ከትመው አየ፥ የእግዚአብሔር መላእክትም ተገናኙት። ያዕቆብም ባያቸው ጊዜ እነዚህ የእግዚአብሔር ሠራዊት ናቸው አለ፤» ይላል። ዘፍ ፴፪፥፩-፪። ቅዱስ ዳዊትም፦ «ሠራዊቱ ሁሉ፥ ፈቃዱን የሚያደርጉ አገልጋዮቹ፥ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል፤» ብሏል። መዝ ፻፫፪፥፳፩። የእነዚህም (የእግዚአብሔር ሠራዊት) አለቃቸው ቅዱስ ሚካኤል ነው። ይኽንንም ሐዋርያው ቅዱስ ይሁዳ «የመላእክት አለቃ ሚካኤል» በማለት መስክሮለታል። ይሁዳ ፩፥፱።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር !

ማርያም እመ ብዙኃን

22/ ሊቀ መልአኩ ቅድስ ሚካኤል ይጠብቃችሁ

ምልጃው ፣ረዴት በረከቱ ተራዳይነቱ አይለያችሁ አይለየን...አሜን...

++++++++++++++++++++

“ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ” እንዳለ (ዳን 10፥13)

++++++++++++++++++++

በሰዶምና በገዎራ ጥፋት ጊዜ ሎጥን ሁለት እጁን ይዘው ከመዓት አድነውታል። (ዘፍ 19፥12-22)

++++++++++++++++++

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስንም ከወኅኒ ቤት የታደገው የእግዚአብሔር መልአክ ነበር። (ሐዋ 12፥6-17)

++++++++++++++++++

“የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ስፍራ ይሰፍራል ያድናቸውማል።” (መዝ 33፥7) በማለት ነቢዩ ዳዊት እንደተናገረው ከተመዘዘ ሰይፍ ፥ ከተወረወረ ጦር ፥ ከተቃጣ መዓት የሚያከብሯቸውንና የሚያምኑባቸውን ያድኑ ዘንድ ዘወትር ከእነርሱ አይለዩም። (ዘፍ 48፥16)

++++++++++++++++++++

“ከልጅነቴ ጀምሮ የጠበቀኝ ያዳነኝም መልአክ... “ እንዲል ይጠብቃሉ

“በመንገድህ ይጠብቅህ ዘንድ ወዳዘጋጀውትም ስፍራ ያገባህ ዘንድ በዚያ እኔ መላአኬን በፊት እሰዳለሁ” (ዘጸ 23፥20)

++++++++++++++++++++

ራእይ 12፥ 7፤ በሰማይም ሰልፍ ሆነ፤ ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉ። ዘንዶውም ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ፥ አልቻላቸውምም፥

የመላኩ የቅዱስ ሚካኤል ረድኤትና በረከት እንዲሁም ምልጃና ፀሎት ከምናምነው ጋር ይሁን አሜን።

Konjit Rooney Ronaldo and 48 others .

አንብበው እንዲጨርሱት በቅዱስ ሚካልኤ ስም እንጠይቃለን ስታበቁም ሼር በማድረግ የ በረከቱ ተካፋይ ይሁኑ።

በስመአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አሃዱ አምላክ አሜንንንን

23/ መጀመሪያ እንኳን ለሀያሉ እና ገናናው መላዕክ ቅዱስ ሚካኤል ወረሀዊ በአል አደረሳችሁ አደረሰን።መላዕኩ ቅዱስ ሚካኤል በጥንት ዘመን ባርህ ከፍሎ እስራኤላዊያንን ሲያሻግር ባህራንን የሞት ደብዳቤውን ወደ ህይወት የቀየረ መላዕክ ዛሬም እኛን በተለያየ ሀገር በፀበሉ ድህነትን ሲያሳይ እንመለከታለን ከዚህም ከፀበሉ ፈዋሽነት አንዱ በሰሜን ሸዋ ሀገረ ስብከት የሸንቁሩ ደብረ መድህኒያለም ቅዱስ ሚካኤል ፀበል የተለያዩ አጋንትን፣ መተት፣አይነስውር ሲያበራ ይህ ነው ብለን የማንዘረዝረውን በሽታ እየፈወሰ ይገኛል።ይህ የፀበል ቦታ በራሱ በቅዱስ ሚካኤል አጥማቂነት ምንም አይነት ከካህን እርዳታ ሳይፈልግ ህዝቡን ከዳቢሎስ ባርነት በማውጣት ይገኛል።ለስንቱ የደረሰ መላዕክ ዛሬም ለሁላችንም ይድረስልን

አሜንንንንን!!!!ይህን ታላቅ እና ገናና ቦታ ከታች በምስሉ እንደምትመለከቱ ዘንድሮ መሰረቱ ተጥሎ ስራ ለመጀመር የምዕመናኑ እጅ ይጠብቃል።ይህን ቤተ ክርስቲያን ዲዛይኑን የነደፈው ሰው እኔ በአካል ተገኝቼ እንደሰማሁት የቤተ ክርስቲያኑን ዲዛይን በመሳል ላይ እያለው ቅዱስ ሚካኤል በአካል ተገልጦ እራሱ ፀበሉን እንደሚያጠምቅ ሁሉ የቤተ ክርስቲያኑንም ዲዛይን በራሱ እጅ ነድፎ እንደጨረሰው ተናግሯል።ካዲያ ይህን በረከት ባለንበት ቦታ በውጪም ሆነ በሀገር ውስጥ ያላችሁ ምዕመናን በሙላ የበረከት ተካፋይ ትሆኑ ዘንድ ቤተ ክርስቲያኗ ትጋብዛለች።ብዙቻችን ገንዘባችንን ባልባሌ ቦታ ከምንበትነው ይህን ታላቅ ቦታ ብንረዳበት መልካም ነው ብዬ በማሰብ ነው ያየሁትን በረከት ላካፍላችሁ የወደድኩት።ይህ ቤተ ክርስቱያን ከኢትዮጵያም ሆነ ከአፍሪካ አንደኝነትን(1ኛ) ይዞ ይገኛል ይህ በረከት አያብልጠን።

በዚህ ታላቅ ቦታ ከ2002 ዓ.ም እስከ 2005 ዓ.ም ድረስ ከልዩ ልዩ በሽታ የተፈወሰ ሰዎች ዝርዝር.....

-ከኤች አይ ቪ ኤድስ.....915

-ከካንሰር በሽታ.....314

-ከመተት.....8773

-ከቡዳ.....3516

-ከኪንታሮት.....130

-ከአይምሮ ጭንቀት.....4452

-ከጨንጉራ.....6715

-ከስኳር 8051

-ከዕጢ.....225

-ከሚጥል በሽታ.....153

-ከአስም.....565

-ከአይነ ስውርነት.....5

-ከለምፅ.....15

-ከሽባነት.....65።

ድምር.....37029

ይህ ምህረት ለቅዱስ ሚካኤል ምንም ማለት አይደለም።ከዚያም በላይ እያደረገ ስለሚገኝ።አምላክ ይህን ታላቅ ቦታ እንድንረግጠው ያብቃን የበረከት ተካፋይ ያድርገን አሜንንንንንንንን

አነሳስቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስፈፀመን ለልኡል እግዚአብሄር ክብር ምስጋና ይግባ አሜንንንንንን

ሰላም የማርያም ልጅ

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ጀዱ አምላክ አሜን።

24/ +እንኳን # ለመላአኩ_ለቅዱስ_ገብርኤልክብረ በዓል በሰላም አደረሳችሁ ።

፨ # ቅዱስ_ገብርኤል__ከሊቃነ_መላእክት አንዱ ሲኾን፤ የሚኖርበት ሰማይም ኢዮር ሲባል አርባብ በተባለ ነገድ ላይ የተሾመ ከሰባቱ ሊቃነ መላእክት ቀዳጥሩ በኹለተኛነት የሚገኝ ነው፤ ይኽ መልአክ በባቢሎን በእሳት ውስጥ የተወረወሩትን ሦስቱን ሕፃናት የታደገ መልአክ ሲኾን በተለይም ለቅድስት ድንግል ማርያም የአምላክን ሰው መኾን ያበሠረ መልአክ ስለኾነ መጋቤ ሐዲስ በመባል ይታወቃል። ሦስቱ ሕጻናትን እንዴት እንደተራዳ ስናየው፤ ነቢዩ ዳንኤል ለንጉሡ ለናቡከደነጾር ሕልሙን ከተረጐመለት በኋላ ዳንኤልንና ሠለስቱ ደቂቅን በባቢሎን አውራጃ ላይ ከፍተኛ ሹመትን በየደረጃቸው ሾሟቸዋል (ዳን ፪÷፵፰-፵፱)።

ኾኖም ግን ናቡከደነጾር ቁመቱ ስሳ ክንድ ወርዱ ስድስት ክንድ የኾነውን የወርቁን ምስል አሠርቶ በባቢሎን አውራጃ በዱራ ሜዳ ላይ በማቆም ኹሉም ላቆመው ምስል ምረቃ ተሰብስበው ሳሉ፤ ዐዋጅ ነጋሪው የዘፈን ድምፅ ሕዝቡ ሲሰሙ ንጉሡ ላቆመው ምስል ተደፍተው እንዲሰግዱ ትእዛዝን የማይቀበሉ ግን በሚነድደው እሳት እቶን እንደሚጣሉ ሲናገር ሕዝቡም አሕዛቡም ለምስሉ ይሰግዱ ይረበረቡ ዝመር (ዳን ፫÷፭-፯)።

ሦስቱ ሕፃናት አናንያ ዘዛርያ ሚሳኤል ግን አንሰግድም በማለታቸው “እሉ እደው ዘሜምኮሙ ለግብረ በሐውርተ ባቢሎን አበዩ ሰጊደ ለምስል ዘወርቅ ዘገበርከ” በባቢሎን አውራጃ ሥራ ላይ የሾምካቸው እነዚኽ ሰዎች ወንዶች ላቆምኸው ምስል አይሰግዱም በማለት ነገሩት፤ ናቡከደነጾርም በብስጭትና በቁጣ እንዲመጡ በማዘዙ፤ መጥተው ከፊቱ ሲቆሙ “ላቆምኹት ለወርቁ

ምስል አለመስገዳችኁ እውነት ነውን? ባትሰግዱ በሚነድድ እሳት እቶን ውስጥ ትጣላላችኁ፤ ከእጁስ የሚያድናችኁ አምላክ ማን ነው?" በማለት ሲናገራቸው የሚያመልኩት አምላክ ከሚነድደው እሳት ሊያድናቸው እንደሚችል ገለጹለት፤ ርሱም በቀጣጣ የእቶኑ እሳት ከሚነደው ይልቅ ሰባት እጥፍ ማለት ፸፯ ክንድ አድርገው እንዲያነዱ በማዘዝ አናንያ፣ አዛርያ፣ ሚሳኤል፣ ታሥረው እንዲጣሉ በሰራዊቱ ውስጥ ላሉት ጎያላን መመሪያ ስላስተላለፈ፤ ወርዋሪዎቹም ከሰናፊላቸውና ከቀሚሳቸው ከመጐናጸፊያቸው ጋር በእሳቱ ላይ ሲጥሏቸው ከወላፈኑ ከፍተኛነት የተነሣ ወታደሮቹ ተቃጥለዋል (ዳን ፫፥፲፫-፳፫)።

ያን ጊዜ "ወወረደ መልአከ እግዚአብሔር ወዘበጦ ለነበልባለ እሳት ወረሰዮ ከመ ነፋስ ቆሪር ዘጊዜ ጽባሕ" ይላል መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ወርዶ በበትረ ብርሃን ቢመታው እንዳረረ ውርጭ ኾኗል፤ ያን ጊዜ ወአንሰሶሰዉ ማእከለ እሳት ወአእኰቱ እግዚአብሔርሀ ወባረክዎ ይላል በእሳቱ ጕድጓድ መኻከልም በመመላለስ እግዚአብሔርንም ፈጽመው አመስግነውታል (መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ ቁ ፭)።

ይኽም ከእሳቱ መኻከል ሳሉ የተገለጸላቸው አስደናቂ ምስጋና ልዩ የኾነ የነገረ ሥጋዌ ምስጢርን የያዘ እንደኾነ የነገረ ነቢያት ሊቃውንት አስተምረዋል፤ ይኸውም በእሳቱ መኻከል ኾነው ለስድስት ጊዜ ብቻ "ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም" (የአባቶቻችን ፈጣሪ እግዚአብሔር ይመስገን፤ የተመሰገነ ነው፤ ለዘለዓለሙም የከበረ ነው) በማለት ካመሰገኑ በኋላ (መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ ቁ ፶፯-፷፪) ለሠላሳ ሦስት ጊዜ በመደጋገም "ይባርክዎ ኩሉ ግብረ

እግዚእ ለእግዚአብሔር ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም” (እግዚአብሔር የፈጠራችው ፍጥረቶች ኹሉ እግዚአብሔርን ያመሰግኑታል፤ ርሱ የተመሰገነ ነው ለዘላለሙም ከፍ ከፍ ያለ ነው) እያሉ “ያመሰግኑታልን” ለ ፴፫ ጊዜ ያኽል ተናግረዋል (መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ ቁ ፴፫-፴፭)።

በሊቃውንቱ ትንታኔ ሠለስቱ ደቂቅ ስድስት ጊዜ መላልሰው መናገራቸው ከ፮፪ ዘመናት በኋላ ምስጉን የኾነው የባሕርይ አምላክ ከሰማየ ሰማያት መውረዱን ከቅድስት ድንግል ማርያም መወለዱን ማጠየቃቸው ሲኾን፤ ከዚያው ቀጥለው ደግሞ ሠላሳ ሦስት ጊዜ “ያመሰግኑታል” እያሉ ቃሉን ደጋግመው ማለታቸው፤ ምስጉን የኾነው አምላክ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከተወለደ በኋላ ሠላሳ ሦስት ዓመት በዚኽ ዓለም የሚኖር እንደኾነ ተገልጾላቸው የተናገሩ መኾኑን አስተምረዋል። ይኽነንም ምስጢር ቀደምት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ሲተነትኑ

“ወኢለከፎሙ እቶነ እሳት ግሙራ ወረሰዮ ለእቶነ እሳት ከመ ማይ ቆሪር በጊዜ ጽባሕ ወበውእቱ ሰዓት ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር እንዘ ይብሉ ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም፤ ወተነበዩ ስድስተ ጊዜያተ ለአጠይቆ ከመ እምድኅረ ስድስቱ ምእት ዓመት ይትወለድ ክርስቶስ። ወእምድኅሬሁ ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር እንዘ ይብሉ ይባርክዎ ኵሉ ግብረ እግዚእ ለእግዚአብሔር ስቡሕኒ ውእቱ ወልዑልኒ ውእቱ ለዓለም ዘንተኒ ተነበዩ ሠላሳ ወሠለስተ ጊዜያተ ለአጠይቆ ከመ እምድኅረ ተወልደ ክርስቶስ ይነብር ውስተ ዓለም ሠላሳ ወሠለስተ ጊዜያተ ለአጠይቆ” (የሚነድደው እሳት ፈጽሞ አልነካቸውም የሚነድደውን

እሳት እንደ ውሃ የቀዘቀዘ አድርጎታልና፤ በዚያን ሰዓት እግዚአብሔርን እንዲኽ እያሉ አመሰገኑት፤ የአባቶቻችን ፈጣሪ እግዚአብሔር ይክበር ይመስገን፤ ለዘለዓለሙ ክቡር ምስጉን ነውና፤ እንዲኽ እያሉ ስድስት ጊዜ ተናገሩ፤ ከስድስት መቶ ዘመን በኋላ ክርስቶስ እንዲወለድ ለማጠየቅ፤ ከዚኽም በኋላ እንዲኽ እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ፤ እግዚአብሔርን ፍጥረቱ ኹሉ ያመሰግኑታል ክቡር ምስጉን ነውና ለዘላለሙ ይክበር ይመስገን እያሉ፤ ይኽንንም ሠላሳ ሦስት ጊዜ ተናገሩ፤ ክርስቶስ ከተወለደ በኋላ በዚኽ ዓለም ሠላሳ ሦስት ዓመት እንዲኖር ለማጠየቅ) በማለት ልዩዉን ምስጢር አስተምረውናል።

ንጉሡ ናቡከደነጾርም ባለመቃጠላቸው፤ በእሳት ውስጥ ኾነው በማመስገናቸው ተደንቆ አማካሪዎቹን “ሦስት ሰዎች አስረን በእሳት ውስጥ ጥለን አልነበረም? እነሆ እኔ የተፈቱ በእሳቱም መኻከል የሚመላለሱ አራት ሰዎች አያለኁ፤ የአራተኛውም መልክ የአማልክትን ልጅ ይመስላል” በማለት፤ ስማቸውን ጠርቶ እናንተ የልዑል አምላክ ባሪያዎች ውጡ ሲላቸው ሦስቱ ሕፃናት ከእሳቱ ወጡ፤ ያን ጊዜ መሳፍንቱ ኹሉ የራሳቸው ጠጕር እንዳልተቃጠለ፤ ሰናፊላቸው እንዳልተለወጠ፤ የእሳቱ ሽታ እንኳ እንዳልደረሰባቸው አዩ።

ያን ጊዜ ንጉሡ “በርሱ የታመኑ ባሪያዎቹን ያዳነ የሲድራቅ የሚሳቅ የአብደናጎም አምላክ ይባረክ” በማለት ምስጋናውን አቅርቧል (ዳን ፫፥፺፭-፺)። እነዚኽ ሦስቱ ሕፃናት አናንያ፣ አዛርያ፣ ሚሳኤል በእቶነ እሳት ቢጣሉም እንኳ፣ ስለ እምነታቸው ብርታት ምስጢር ተገልጾላቸው በሺኛ ዘመን አምላክ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ

ሺኛ ዓመት በዚኽ ዓለም ኖሮ ነፍሳትን ከሲኦል እሳት ነጻ እንደሚያወጣ የተገለጸላቸውን ልዩ ምስጋና፣ ዛሬ ኹላችን በቃል ኪዳኗና በምልጃዋ ከገሃነመ እሳት ከምንድንባት ከምትራራልን እናት ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ፈጽሞታና፤ ታላቁ ሊቅ አባ ጊዮርጊስ በጥሩኅ ብርሃን የነገረ ማርያም መጽሐፉ ላይ “መሃኪቶሙ እምውስተ እቶነ እሳት ለአናንያ ወአዛርያ ወሚሳኤል በእደ ቅዱስ ገብርኤል” (በቅዱስ ገብርኤል እጅ አናንያን፣ አዛርያን፣ ሚሳኤልን በእቶን እሳት ውስጥ የራራሺላቸው አንቺ ነሽ) በማለት ምስጢሩን እንደወርቅ አንከብሎ እንደ ሽማ ጠቅልሎ ገልጾታል።

ነገረ ማርያም በብሉይ ኪዳን ክፍል 2 ከሚለው መጽሐፍ የተወሰደ

የመልአኩ በረከት ይደርብን

Nardos Gezawu

25/ የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል፤ ያድናቸውማል/መዝ. 33÷7/

እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ቸርነቱን የሚገልጠው በመላእክት ተራዳኢነት ለሰው ልጅ በሚፈጽመው የማዳን ተግባር ነው። መላእክት የሚያገለግሉት በእግዚአብሔር ፈቃድና ትእዛዝ መሠረት መሆኑም ግልጽ ነው። የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል ያድናቸውማል፣ እግዚአብሔር ቸር እንደሆነ ቅመሱት፤ እወቁም (መዝ. 33÷7-11) በማለት ቅዱስ ዳዊት እንደጠቀሰው ጥልቅ መልእክት እንዳለው እንረዳለን። ከታሪክ እንደምንረዳውም እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ቸርነት ቀምሰው ያወቁት በጭንቀታቸው ጊዜ መልአኩን ልኮ በፈጸመላቸው የማዳን ተግባር ነው።

መላእክት አገልግሎታቸው ብዙ ነው። መንፈሱ የተራቆተውን፣ በችግር ላይ የወደቀውን፣ በፍርሀት የተዋጠውንና ተስፋ የቆረጠውን አጽናንተዋል፣ ከክፉ ነገር ሁሉ ጠብቀዋል። በትንቢተ ዘካርያስ ምእራፍ 3÷4 ላይ “እነሆ በደልህን አስወግጄልሀለሁ አዲስ የክብር ልብስም አለብስሃለሁ” ተብሎ የተገለጸውን ማገናዘብና መረዳት ያስፈልጋል፣ ቃሉም ቃለ መልአክ እንደሆነ ተገልጿል።

መላእክት የእግዚአብሔር ሕግና ትእዛዝ ጠብቆ ለሚማጸንባቸው ሁሉ ፈጥነው የሚደርሱና የሰውንም ወገን በማንኛውም መንገድ የሚራዱ መሆናቸው ቢታወቅም የመላእክትን እርዳታ ለማግኘት በቅድሚያ ራስን በእምነት ማዘጋጀት ተገቢ ነው። የመላእክት ተራዳኢነትን በብሉያትም ሆነ በሐዲሳት የምንረዳበት መንገድ ብዙ ቢሆንም ለግንዛቤ ያህል፡-

ሀ. አጋር ከሣራ በደረሰባት ግፍና በደል ምክንያት ከቤት ወጥታ በበረሃ በችግር ላይ ሳለች የእግዚአብሔር መልአክ ወደ አጋር ቀርቦ እንዳጽናናትና

እንዳገለገላት በዘፍ. 16÷1-16 ላይ ዝርዝር ታሪኩ ተገልጿል።

ለ. ሕዝበ እስራኤልን ወደ ምድረ ርስት በመምራት ላይ የነበረው ኢያሱ በእግዚአብሔር መልአክ እየተረዳ ጠላቶቹን ድል አድርጓል፤ ሊደረግ የሚገባውንም መልአኩ እየነገረው ይሠራ እንደነበረ በመጽሐፈ ኢያሱ 5÷13-35 ላይ ታሪኩ ተጽፏል።

ሐ. መላእክት ለመዓትም ለምሕረትም ይላካሉ። (ሮሜ 9÷22-23) በየዋህነት፣ በቅንነት፣ የሚሠሩትን፣ በእግዚአብሔር የሚያምኑትን ይረዳሉ። ከልዩ ሥቃይ ይታደጋሉ፣ በአንጻሩም በትዕቢትና በጠማምነት የሚኖሩትን፣ ለእግዚአብሔርና ለሕጉ የማይታዘዙትን ለመቅጣት ይታዘዛሉ። ለምሳሌ ሕዝበ እስራኤል ከጭቆና አገዛዝ ከግብጽ ሲወጡ ቀን በደመና፣ ሌሊት በእሳት ብርሃን እየመራ የመገባቸው፣ ባሕር ከፍሎ ያሻገራቸው የእግዚአብሔር መልአክ ነው። ለእስራኤላውያን መልአክ ምሕረት ሆኖ ባሕርን ከፍሎ ያሻገረ፤ ለግብጻውያን ደግሞ መልአክ መዓት በመሆን ስጥመት እንዲፈጸም ያደረገው መልአክ እግዚአብሔር ነው። (ዘጸ.14÷15-25)

መ. ለሰናክሬምና ሠራዊቱ መልአክ መዓት፣ ለሕዝቅያስና ለወገኖቹ መልአክ ምሕረት ሆኖ የሕዝቅያስን እምነት፣ የሰናክሬምን ትዕቢት ተመልክቶ ተገቢውን ግዳጅ የፈጸመ መልአክ እግዚአብሔር እንደሆነ በ2 ነገሥ. 19÷35 ላይ ተመዝግቧል።

ሠ. ከእቶነ እሳት ጉድጓድ ተጥለው የነበሩትን ሦስት ወጣቶች ከሞት የታደገ መልአክ እግዚአብሔር ነው፣ (ዳን.3÷1-25)

ረ. አናብስት ከሚጠበቁበት ሥፍራ በግፍ ተጥሎ የነበረውን ነቢየ

እግዚአብሔር ዳንኤልን ከአፈ አናብስት የታደገ መልአክ እግዚአብሔር ነው። (ዳን. 6÷13-22) “በመንገድህ ሁሉ እንዲጠብቁህ እግዚአብሔር መላእክቱን ያዝዛል” (መዝ. 90÷1-22) እንዲል። እንዲሁም “ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ” ሲል የቅዱስ ሚካኤልን ተራዳኢነት ይገልጣል (ዳን. 10÷13)።

ሰ. እስራኤላውያን ከግብጽ ሲወጡ ፈርዖን ሲያሳድዳቸው እግዚአብሔር የሕዝቡን ችግር ተመልክቶ “በመንገድህ ይጠብቅህ ዘንድ ወደ አዘጋጀሁትም ስፍራ ያገባህ ዘንድ እነሆ እኔ በፊትህ መልአክን እሰድልሀለሁ” ሲል ለሙሴ ቃል እንደገባለትና በኋላም በዚህ ቃል ኪዳኑ መሠረት የተላከው የእግዚአብሔር መልአክ በፊትና በኋላ እየሆነ ይመራቸውና ይጠብቃቸው እንደነበር ቅዱስ መጽሐፍ ይናገራል (ዘፀ.14÷19፤23÷20፤33÷2)።

ቤተ ክርስቲያን ስለ ተራዲኢነትና ጠባቂነት ለምእመናኖቿ የምታስተምረውም ይህንን የቅዱስ መጽሐፍ ቃል አብነት በማድረግ ነው። በዚህ ትምህርት መግቢያ ላይ የተጠቀሰው “የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል፤ ያድናቸውማል” የሚለው ቃል የሚያመለክተውም የዚህ ትምህርት ትክክለኛነት ነው።

መላእክት በዕለተ እሁድ ከተፈጠሩ ፍጥረታት አንዱ ክፍል ናቸው። መላእክት አንድ ጊዜ የተፈጠሩ እና በየጊዜውም የማይባዙ ናቸው:: መላእክት በተፈጥሮአቸው ነባብያን፤ ለባውያን፣ ሕያዋን፣ ኃያላንም ናቸው፤ እንደ ደቂቀ አዳም ሕመምና ሞት የለባቸውም። የመላእክት ቁጥር በአጎዝ አይወሰንም የብዙ ብዙ ናቸው፤ መላእክት በነገድ አለቃ እና

በከተማ ይከፋፈላሉ፤ በነገድ መቶ፤ በከተማ ዐሥር፡:

ሀ. አገልግሎታቸው፡-

ቅዱሳን መላእክት ለእግዚአብሔር የቅርብ አገልጋዮች ናቸው፤ በዙፋኑ ዙሪያ ሆነው ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ እያሉ ዘወትር ያመሰግናሉ። በተልዕኮአቸውም ፈጣኖች ናቸው፤ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ለተልዕኮ ይወርዳሉ ይወጣሉ፤ የሰው ልጆችንም ይረዳሉ። (ራዕ.4÷9-11፤መዝ.103÷4፤ ዕብ.1÷4፤1÷14፤÷ዮሐ.1÷52)

በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ለተልእኮ መፋጠናቸው፡-

• የሰውን ጸሎት፤ ምጽዋትና መሥዋዕት ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ፣

• የእግዚአብሔር ምሕረትና ቸርነት ወደ ሰዎች ማድረስ እንዲሁም ለቅጣት ይላካሉ። (ዳን.9÷20- 22፤ሉቃ. 1÷13፤ የሐዋ. 1÷3-5)

• ሰዎች በሞቱ ጊዜ ነፍሳቸውን ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ።

(ሉቃ. 13÷22፤ሱቱ. ዕዝ. 6÷6-20፤ ዳን. 4÷13፤ ሮሜ 9÷22)

• በመከራና በችግር ጊዜ ለተራዳኢነት መላክ፣

• በፍጻሜ ዘመን (ይህ ዓለም በሚያልፍበት ጊዜ) ከእግዚአብሔር ተልከው ኃጥአንን ከጻድቃን መለየት እንደሆነ ቅዱስ መጽሐፍ ስለ ቅዱሳን መላእክት በሰፊው ያስረዳል። (የሐዋ. 12÷7- 11፤ መዝ. 69÷7፤ ማቴ. 2÷31፤ ራእ. 7÷1-4)

ለ. አማላጅነታቸው፡-

የቅዱሳን መላእክት አማላጅነትና ተራዳኢነት፣ የሰዎችን ጸሎትና ምጽዋት

ወደ እግዚአብሔር ለማቅረብ በተሰጣቸው ባለሟልነት ይፈጽማሉ። ከቅዱስ መጽሐፍ በሰፊው እንደምንረዳው የብዙዎችን ሰዎች ጸሎት መሥዋዕትና ምጽዋት ወደ እግዚአብሔር እያቀረቡ የሚፈልጉትን መልካም ነገር ሁሉ ያሰጣሉ። ማጽናናትና የምሥራች መንገርም ከእግዚብሔር የተሰጣቸው ልዩ ጸጋ ነው። (ዘፍ. 48÷16፤ ዳን÷16፤ ዳን.16÷10÷10-2፤ሉቃ. 1÷13፤ 10÷29-32፤ ይሁዳ.9) መመልከት ይቻላል።

የቅዱሳን መላእክት አማላጅነት በቅዱሳት መጻሕፍት በስፋት ተጽፏል፣ በተለይም በመጽሐፈ ሄኖክ 10÷7 እና በትንቢተ ዘካርያስ 1÷12፤ በዘፀአ. 23÷20-23፤ መዝ.33÷7 የተቀመጡትን ጥቅሶች በግልጥ ያስረዳሉ። ቅዱሳን መላእክት ንስሓ ገብተው በተመለሱ ሰዎች ደስታ እንደሚያደርጉ በሉቃስ ወንጌል 15÷10 ላይ የተጻፈው ስለ ሰው ልጆች ደኅንነት ያላቸውን ፍቅርና አማላጅነት ያስገነዝባል።

ሐ. ክብራቸው፣

ቅዱሳን መላእክት በእግዚአብሔር ፊት የሚቆሙ ባለሟሎች ስለሆኑ ለአምላካቸው ቀናዕያን፣ ለነፍሳት ቀዋምያን ስለሆኑ፣ ለምሕረትም ለመዓትም ስለሚላኩ፣ ሰዎችን በችግራቸው ጊዜ ስለሚረዱና ስለሚያማልዱ ቤተ ክርስቲያን ታከብራቸዋለች። በስማቸው ጽላት ቀርጻ፣ ቤተ ክርስቲያን አሳንፃ፣ ድርሳናቸውን አጽፋ፣ እንዲመሰገኑ እንዲከብሩ ታደርጋለች። የጸጋና የአክብሮት ስግደትም ይሰገድላቸዋል። (ዳን.8÷15-18፤ ዘፍ. 22÷31 ዘጸ. 22÷31፤ኢያ.5÷13-15

መላእክት ሰውን የሚራዱት በእግዚአብሔር ፈቃድና ትእዛዝ ስለሆነ የመላእክት ተራዳኢነት የእግዚአብሔር ቸርነት መገለጫም ናቸው።

ከቅዱሳት መጻሕፍት ቃል መረዳት እንደሚቻለው ዘካርያስና ኤልሳቤጥ በሐዲስ ኪዳን ዘመን መጀመሪያ ላይ የተነሡ የብሉይ ኪዳን ዘመን ባልና ሚስት ሲሆኑ ሁለቱም በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ። በእግዚአብሔር ሥርዐትና በትእዛዙም ሁሉ ያለ ነውር የሚሄዱ ነበሩ። ልጅም አልነበራቸውም። ዘመናቸውም ያለፈ ነበር። ዘካርያስ የዘመነ ኦሪት ሊቀ ካህናት እንደመሆኑ በቤተ መቅድስ በአገልግሎት ላይ ሳለ የእግዚአብሔር መልአክ ታየው። "እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ። ይህንንም እነግርህና አበሥርህ ዘንድ ወደ አንተ ተልኬአለሁ።" (ሉቃ.1÷11-21) ሲል መልአኩ ተናገረው።

መልአኩም ለዘካርያስ የተገለጠው ልጅ እንደሚወልድ ለማብሠር ነበር። ዘካርያስ ግን ይህን ብሥራት የሰማው ከጥርጣሬ ጋር ነበር። ምክንያቱም እሱም ሆነ ሚስቱ ኤልሳቤጥ በዕድሜ የገፉችና የመውለጃ ጊዜያቸውም ያለፈ መሆኑን ስለሚያውቅ ነበር። ካሁኑ ዘካርያስ የተነገረውን ብሥራት በመጠራጠሩ የተነገረው ብሥራት እስከሚፈጸም ድረስ አንደበቱ እንደሚዘጋና መናገርም እንደማይችል ነገረው። ይህንም ያደረገው ለቅጣት ሳይሆን ለተነገረው ብሥራት እውነትነት ምልክት እንዲሆነው ለማድረግ ነበር።

በመልአኩ እንደ ተነገረውም ኤልሳቤጥ የመውለጃ ጊዜዋ ካለፈ በኋላ ፀነሰች። ወንድ ልጅም ወለደች፤ እሱም መጥምቁ ዮሐንስ ነበር። ዮሐንስም እንደ ተወለደ ዘካርያስ ተዘግቶ የነበረው አንደበቱ ተከፍቶ መናገር ጀመረ። መጥምቁ ዮሐንስም አስቀድሞ በመልአኩ ቃል እንደተነገረው መንፈስ ቅዱስ የሞላበት የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥን ሁሉ የማይጠጣ

ከእሰራኤል ብዙዎችን ወደ እግዚብሔር ወደ አምላካቸው የሚያቀረብ፤ የአባቶች ልብ ወደ ልጆች፤ የከሃድያንንም ሐሳብ ወደ ጻድቃን እውነት የሚመልስና ሕዝብንም ለእግዚአብሔር ማደሪያ የተዘጋጀ የሚያደርግ ካህን፤ ነቢይ፤ ሐዋርያና ሰማዕት ሆኖ ዓለምን ለማገልገል የበቃ የእግዚብሔር መልእክተኛ ሆነ። በዚህም ምክንያት የመጀመሪያው የሐዲስ ኪዳን “ቅዱስ” ተባለ።

መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ጣዖት አናመልክም በማለታቸው ምክንያት ወደ እቶነ እሳት የተጣሉትን ሦስት ወጣቶችን ማዳኑን በቅዱስ መጽሐፍ ከምናገኛቸው ታሪኮች አንዱ ነው። ሦስቱም ወጣቶች ወደ ባቢሎን ተማርከው ከተወሰዱት እስራኤላውያን መካከል የሚገኙ የእግዚአብሔር ሰዎች ነበሩ። እነዚህ አማንያን ወደ እሳት እንደተጣሉ የእግዚአብሔር መልአክ ከሦስቱ ሰዎች ጋር ወደሚነድደው የእሳት ምድጃ ወርዶ እሳቱን ስለመታው የእሳቱ ነበልባል እንደ ጠፋና ሦስቱም ሰዎች ምንም ጉዳት ሳይደርስባቸው ከሚነድደው እሳት እንደወጡ፤ በዚህም ለእግዚአብሔር ጥልቅ ምስጋና እንዳቀረቡ በትንቢተ ዳንኤል ታሪካቸው በስፋት ተገልጧል (ዳን. 3÷26)። ይህም እግዚአብሔር በመላእክት ተራዳኢነት ለሰው ልጅ የሚያደርገውን ቸርነት አጉልቶ የሚያሳይ ነው። ቤተ ክርስቲያናችንም በታላቅ በዓል ታከብረዋለች።

“ከእናቴ ማኅፀን የመረጠኝና የለየኝ እግዚአብሔር በጸጋው ጠራኝ” (ገላ.1÷15-17) እንዲል ልዑል እግዚአብሔር ከማኅፀን ጀምሮ ለመልካም አገልግሎት ሰዎችን እንደሚመርጥና እንደሚያዘጋጅ በቅዱሳት መጻሕፍት ተመዝግቦ እናገኛለን። ከእነዚህም ውስጥ በቅደም ተከተል

ማየትና መመርመር እንዲሁም መረዳት ተገቢ ነው።

ለምሳሌ በብሉይ ኪዳንና በሐዲስ ኪዳን፦

ሀ. የማኑሄ ልጅ ሶምሶን በብሥራተ መልአክ እንደተፀነሰና ተወልዶ ካደገም በኋላ ምን ማድረግ እንዳለበት አስቀድሞ በልዑል እግዚአብሔር እንደታጨና እንደተመረጠ በመጽሐፈ መሳፍንት ምዕራፍ 13 ከቁጥር 1-25 የተመዘገበውን፤

ለ. ነቢየ እግዚአብሔር ኤርምያስ “ገና በእናትህ ማኅፀን እንድትፀነስ ከማድረጌ በፊት መርጬሃለሁ፤ ከመወለድህም በፊት አንተን በመለየት ለሕዝቦች ሁሉ ነቢይ አድርጌ ሾሜሃለሁ” ተብሎ እንደታጨና እንደተመረጠ በምዕራፍ 1÷4-5 የተመዘገበውን፤

ሐ. መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ በብሥራተ መልአክ “ዘካርያስ ሆይ! አትፍራ፤ ጸሎትህ ተሰምቶልሃል፤ ሚስትህ ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች፤ ስሙንም ዮሐንስ ብለህ ትጠራዋለህ፤ የእርሱ መወለድ ለአንተ ተድላና ደስታ ይሆንልሃል፤ ብዙዎችም በመወለዱ ደስ ይላቸዋል (ሉቃ.1÷13-14) ተብሎ ተገልጿል።

መ. በጌታ እንደታጨና እንደተመረጠ ሁሉ ንዋይ ኅሩይ የተሰኘው ቅዱስ ጳውሎስም በመሪ ጥቅሱ እንደተገለጸው ”ከእናቴ ማኅፀን የመረጠኝና የለየኝ እግዚአብሔር በጸጋው ጠራኝ” ብሎ ምርጫውና ጥሪው ከእግዚአብሔር መሆኑን ያበሥራል።

“ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን ስንኳ እንዳትንቁ ተጠንቀቁ፤ መላእክት ዘወትር በሰማያት ያለውን የአባቴን ፊት ያያሉ እላችኋለሁና።” (ማቴ.18÷10-12) በማለት ጌታችንና መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ

በዚህ ዓለም በሚያስተምርበት ወቅት ሕፃናትን ከትልልቆቹ ለይቶ አላያቸውም። በፍቅሩ ወደ እርሱ ያቀርባቸው ነበር፤ ወደ እርሱ እንዲመጡ እንዳይከለክሏቸው ደቀመዛሙርቱንም አዝዞአቸዋል። ይቀጥላል.. .....

1. ቅዱሳን መላእክት ለእግዚአብሔር የቅርብ አገልጋዮች ናቸው
2. ጎዳር 12 ቀን ማጎሌት
3. ጎዳር 12- ከጽንፍ እስከ ጽንፍ የሚበር ንሥረ
4. ቅዱሳን መላእክት
5. እንኳን ለሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል መታሰቢያ ክብረ በዓል በሰላም አደረሳችሁ
6. በዚያም ዘመን ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል
7. እንኳን ለሊቀ መልአክ ቅዱስ ሩፋኤል ዓመታዊ በዓል
8. (እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ) (ሉቃ 1፥19)
9. ቅዱሳን መላእክት እግዚአብሔር በእለተ እሁድ
10. እንኳን ለመልአኩ ለቅዱስ ሚካኤል ክብረ በዓለ በሰላም አደረሳችሁ
11. ቅዱስ ማለት ልዩ፥ ክቡር ማለት ነው፤
12. ሊቀ መልአኩ ቅድስ ሚካኤል
13. መላዕክ ቅዱስ ሚካኤል ወረሀዊ በአል

14. ለመላአኩ_ለቅዱስ_ገብርኤልክብረ በዓል
15. የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል